# መጽሔተ ፡ ስብከት



www.ethiopianorthodox.org

D.N Solomon Yohannes

# መጽሐፈ ፡ ስብከት ።

ተተረጐመ ።

ከዮሐንስ ፡ ረዳ ፡ ጻድቅ ።

በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዘኢትዮጵያ ፡ በ፴፪ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ። ቍ ፡ 7378

www.ethiopianorthodox.org

D.N. Solomon Yohannes

# ማውጫ ።


| አርእስት ፡ | | | ገጽ ። |
|---|---|---|---|
| መቅድም ፡ | | | 7 |
| መግቢያ ፡ | | | 11 |
| ምዕራፍ ፡ | ፩ ፡ | የስብከት ፡ ትርጓሜ ፡ | 15 |
| ” | ፪ ፡ | የስብከት ፡ አከፋፈል ፡ (አመዳደብ ፡) | 21 |
| ” | ፫ ፡ | የስብከት ፡ አተረጓጎም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ | 33 |
| ” | ፬ ፡ | የስብከቱ ፡ መግቢያ ፡ | 43 |
| ” | ፭ ፡ | ክፍለ ፡ መደቦች ፡ | 55 |
| ” | ፮ ፡ | መደምደሚያ ፡ | 67 |
| ” | ፯ ፡ | ስብከትን ፡ በጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ፡ | 77 |
| ” | ፰ ፡ | ጠቅላላ ፡ አሰባበክ ፡ | 83 |
| ” | ፱ ፡ | ሰባኪው ፡ እንደ ፡ ተማሪ ፡ | 91 |
| ” | ፲ ፡ | የአደባባይ ፡ ስብከት ፡ | 95 |
| ” | ፲፩ ፡ | ሰባኪው ፡ እንደ ፡ ጸሎት ፡ ሰው ፡ | 109 |




www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም ።

ይህን ፡ መጽሔተ ፡ ስብከት ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሌሎች ፡ ይህንኑ ፡ ከመሳሰሉት ፡ መጻሕፍቶች ፡ በመረዳት ፡ በአስተዋጽዖ ፡ ዓይነት ፡ ለማዘጋጀት ፡ ከጀመርኩ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ አልፈዋል ። ይህንኑ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ያሳሰቡኝ ፡ ምክንያቶች ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ቢሆኑም ፥ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እጠቅሳቸዋለሁ ።

፩ ፥ ታላቁ ፡ መሪያችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብርሃን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የመንግሥቱ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ እንዲሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከተመረጠበት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ውዲቱ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በብሔራዊ ፡ አስተዳደር ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ እንደ ፡ ደከመላትና ፡ እንደሚደክምላት ፡ ሁሉ ፥ በመንፈሳዊ ፡ ኑሮዋና ፡ በሃይማኖቷም ፡ ከእውነተኛው ፡ የወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ እንደሚስማማ ፡ ሆኖ ፥ ከፍተኛውን ፡ የፓትርያርክነት ፡ ደረጃ ፡ አግኝታ ፥ ከሌሎች ፡ ታላላቅ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪዎች ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ መብት ፡ እንዲኖራት ፡ አድርጎ ፥ ለቤተ ፡ ክርስቲያንዋ ፡ መሪዎች ፡ የመጨረሻውን ፡ ከፍተኛ ፡ የፓትርያርክነት ፡ ማዕረግ ፡ ስላጐናጸፋቸው ፤ ለሥራቸውም ፡ ቀና ፡ ይሆን ፡ ዘንድ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በተስተካከለ ፡ አማርኛ ፡ ታርሞና ፡ ተጣርቶ ፡ እንዲታተም ፡ ስላደረገ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ የሐዋርያነትን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ እ



www.ethiopianorthodox.org

ንጂ ፣ ሌላ ፡ ምንም ፡ ስላልቀረ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ደጋፊ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

፱ ፣ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ በበዛበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክፍለ ፡ አገሮች ፣ በአገሪቱ ፡ ክርስትና ፡ ከገባለት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ ከቦታው ፡ እንዳይለቅና ፡ በተቻለም ፡ መጠን ፡ ከክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ የራቀ ፡ ባዕድ ፡ ሃይማኖትና ፡ አረመኔነት ፡ በሚበዛባቸው ፡ ክፍለ ፡ አገሮች ፣ የክርስቲያን ፡ ገዳማት ፡ እየተመሠረቱ ፡ የወንጌልን ፡ ብርሃን ፡ ጮራ ፡ ሲያስገቡ ፡ የኖሩ ፡ ብዙ ፡ መነኮሳትና ፡ ምዕመናን ፡ እንዳለፉና ፡ እስካሁንም ፡ እንዳሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሆኖም ፣ ይህን ፡ የወንጌል ፡ ስብከት ፡ በሚያስፋፉበት ፡ ጊዜ ፡ በአንዳንድ ፡ ትጉኃን ፡ ሊቃውንት ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ በተጻፉ ፡ የጸሎትና ፡ የትርጒም ፡ መጻሕፍቶች ፡ እየተደገፉ ፣ አብዛኛውንም ፡ በቃል ፡ እያጠኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድካም ፡ በማድረግ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ተያይዞ ፡ ሲወርድም ፡ በልማድ ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጥር ፡ ግቢና ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ የሚሰብኩ ፡ ካህናትና ፡ መነኮሳት ፡ ወጣቶችም ፡ ሰባኪዎች ፡ እናያለን ፤ ሆኖም ፣ ስለ ፡ አሰባበኩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርትና ፡ ዝግጅት ፡ ስለሚጐድልባቸው ፡ የሚያውቁትን ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከፍጥረት ፡ ጀምረው ፡ ነቢያትን ፡ ሐዲሳትን ፡ እስከ ፡ ራእይ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ስብከት ፡ ለአድማጮቻቸው ፡ ለማስረዳት ፡ ሲታገሉ ፡ ስለሚታይ ፣ ለዚህ ፡ አንድ ፡ መደበኛ ፡ መሪ ፡ የሚሆን ፡ በአጭር ፡ የተዘጋጀ ፤ ለሸክም ፡ የማይከብድ ፤ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፤ የክርስቶስን ፡ እውነተኛ ፡ መ



ድኃኒትነት ፡ ለመስበክ ፡ ለሚወድ ፡ ለማናቸውም ፡ ምዕመን ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ።

፲ ፣ እንዲሁም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ትምህርት ፡ ከሙሴ ፡ ታሪክ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ዓይነተኛ ፡ ጥቅሙ ፣ በአጭር ፡ ተጠቃልሎ ፣ የሚከተሉትን ፡ መሠረታውያንና ፡ ጠቃሚ ፡ ነገሮችን ፡ በመያዙ ፤ እነዚህም ፣

ሀ) እግዚአብሔር ፡ አምላክህን ፡ ብቻ ፡ አምልክ ፤ የጥበብ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነውና ፤ ዘርህ ፡ የተባረከ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፤

ለ) ባልንጀራህን ፡ እንደ ፡ ራስህ ፡ ውደድ ፡ (አፍቅር ፡) ወይም ፡ ሊያደርጉብህ ፡ የማትወደውን ፡ በሌላ ፡ አታድርግ ፡ ዕድሜህ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፤

ሐ) ከአገርህና ፡ ከወገንህ ፡ ተለይተህ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ከመባል ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ አገርህና ፡ ወገንህ ፡ ተበቀል ፤ ተሰዋ ፤ በትክክለኛ ፡ አምላካዊ ፡ ሕግ ፡ ለሚያስተዳድርህ ፡ ንጉሥ ፡ ተገዛ ፤ ለተሾመው ፡ መኰንን ፡ ታዘዝ ፤ ክብርህና ፡ ባለ ፡ ጸግነትህ ፡ ይበዛ ፡ ዘንድ ፤

መ) ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አምላክ ፡ መሆኑን ፡ አምነህ ፡ ትምህርቱን ፡ በሙሉ ፡ ተቀበል ፤ የነፍስህ ፡ ቤዛ ፡ ነውና ፡ የዘለዓለም ፡ ድኅንነት ፡ በእርሱ ፡ ታገኝ ፡ ዘንድ ፤



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን ፡ ትእዛዛት ፡ በአስተዋይነትና ፡ በትዕግሥት ፡ ብትፈጽም ፡ በዚህ ፡ ምድራዊ ፡ ሕይወትህ ፡ ማናቸውንም ፡ ፈተና ፡ ድል ፡ ከማድረግህም ፡ በላይ ፡ የሚያስፈልግህን ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ ራሱ ፡ ይጨምርልሃል ፤ የሰማይ ፡ መንግሥቱንም ፡ ትወርሳለህ ፣ የሚለውን ፡ ተስፋ ፡ የያዘውን ፡ ትምህርት ፡ በመያዙ ፣ ከፍተኛውን ፡ ጥበብ ፡ የሚጨምር ፡ መሆኑን ፡ በመረዳቴ ፣ የሰው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ትምህርት ፡ እንዲወድና ፡ አምኖ ፡ እንዲቀበለው ፡ በማለት ፣ ይህን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የስብከት ፡ ትምህርት ፡ እንዳዘጋጅ ፡ አሰብኩ ።

ስለዚህ ፡ ይህች ፡ መጽሔት ፣ የጌታችን ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ በቤትም ፡ በደጅም ፣ በከተማም ፣ በበረሃም ፣ በባሕርና ፡ በአየርም ፡ ጕዞ ፤ በሰላምም ፤ በጦርነትም ፡ ጊዜ ፡ ለመስበክ ፡ የማትሰለች ፡ ረዳት ፡ ሆና ፣ የታማኝ ፡ ሰባኪዎችን ፡ ሁሉ ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ ትጠቅም ፡ ዘንድ ፡ ምኞቴ ፡ ነው ። አሜን ።

ዮሐንስ ፡ ረዳ ፡ ጻድቅ ።



# መግቢያ ።

በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ በ፩ኛው ፡ ክፍል ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፣ በሚከተሉት ፡ ገጾች ፡ ስለ ፡ ስብከት ፡ አሠራር ፡ የሚደረገውን ፡ ስነ ፡ ጥበብ ፡ (የስብከት ፡ ሳይንስ ፡) ልንነጋገርበት ፡ ነው ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ስብከቶችና ፣ የአንድ ፡ ስብከት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፣ የስብከቱ ፡ ዝግጅትና ፡ አሰጣጡ ፣ አቀራረቡ ፣ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ ለማስረዳት ፡ እንሞክራለን ።

የስብከት ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ (ሳይንስ ፡) በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ቢሠራበት ፡ ምን ፡ ውጤት ፡ እንደሚያስገኝ ፣ ወይም ፡ ባይሠራበት ፡ ምን ፡ እንደሚያጐድል ፡ ማስተዋል ፡ ጠቃሚና ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ። ለምሳሌ ፣ አንድ ፡ የወታደር ፡ ማስተማሪያ ፡ መጽሐፍ ፣ እራሱ ፡ ጥሩ ፡ ወታደር ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መጽሐፍ ፡ ለአገር ፡ ታማኝ ፡ መሆንን ፣ ድፍረትን ፣ ድል ፡ ለማግኘት ፡ የሚደረገውን ፡ ቈራጥነት ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ። ሆኖም ፣ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሲታሰብ ፡ ደግሞ ፣ የዚህ ፡ ማስተማሪያ ፡ ትክክለኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በመጕደሉ ፣ ምክንያት ፡ በጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በከንቱ ፡ ወድቀው ፡ እንደቀሩና ፡ ብዙ ፡ ጦርነቶችም ፡ ድል ፡ እንደሆኑ ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። ከአጕል ፡ ሱፍ ፣ ጥሩ ፡ ኮት ፡ ለመስፋት ፡ አይቻልም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ደግሞ ፡ ሱፉ ፡ እጅግ ፡ ጥሩ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ቢሆንም ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ ካልተፈተለና ፡ ካልተሠራ ፡ ጨርቁም ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ ጥሩ ፡ ቀዳጅ ፡ በሚገባ ፡ ካልቀደደውና ፡ ካልሰፋው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ኮት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለ ፡ አይሁድ ፡ ሲናገር ፡ «መልካም ፡ ቅንዓት ፡ ይቀኑ ፡ ዘንድ ፡ መሰከርኩላቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእውቀቴ ፡ አይደለም ፡ ይላል ።» (ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፪ ፡) እንደዚሁም ፡ ጥሩ ፡ አናጢ ፡ መልካሙን ፡ መሣሪያ ፡ አይንቅም ፤ በመጥፎ ፡ መሣሪያ ፡ ከሚሠራ ፡ ይልቅም ፡ በጥሩ ፡ መሣሪያ ፡ በሥራ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ዕቃ ፡ እንደሚሆንለት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ስብከቶች ፡ በሥርዓት ፡ ካለመዘጋጀታቸው ፡ ምክንያት ፡ ግማሽ ፡ ኃይላቸውን ፡ ያጣሉ ። በስብከት ፡ ጊዜ ፡ ንቃት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ቢሆንም ፡ በሥርዓት ፡ ላልተዘጋጀ ፡ ስብከት ፡ እጅግ ፡ ሲነቁበት ፡ ቢውሉ ፡ ረብ ፡ የለውም ። ስለዚህ ፡ በመደብ ፡ በመደቡ ፡ በሥርዓት ፡ የተዘጋጀና ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ መጽሔት ፡ በማቅረብ ፡ የሚደረግ ፡ ስብከት ፡ ለአድማጮቹ ፡ ቶሎ ፡ ሊታወስ ፡ ይቻላል ።

አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለችሎት ፡ የሚሆነውን ፡ ንግግሩንና ፡ ክርክሩን ፡ ተጠንቅቆ ፡ እንደሚያዘጋጅና ፡ «ለኋላ ፡» የሚባል ፡ ነገር ፡ እንደማይተው ፡ እናውቃለን ። ማናቸውም ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ለአንድ ፡ ለተወሰነ ፡ መደበኛ ፡ ውጤት ፡ እንደሚደከምበት ፡ ማወቅ ፡ አለ ። ጥሩ ፡ ንግግር ፡ ለሕግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ለሕዝባዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ ሊወስኑ ፡ አይገባም ። ይበልጡን ፡ በአትሮኖስ ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ግብ ፡ እንዲበቃ ፡ አንድ ፡ ሰባኪ ፡ የክርክሮችን ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የታላላቅ ፡



ሰባኪዎችንም ፡ በመጽሐፍ ፡ የተዘጋጁትን ፡ ስብከቶች ፡ በየጊዜው ፡ ማንበብና ፡ ማጥናት ፡ በጣም ፡ ይጠቅመዋል ። አንዳንዶቹ ፡ እንደ ፡ ማስረጃ ፡ ሆነው ፡ በሚከተሉት ፡ ምዕራፎች ፡ ተጠቅሰዋል ።

በመግቢያው ፡ የሚታወስ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ የወንጌል ፡ ስብከት ፡ አንድ ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ መሆኑንና ፡ የክርስቶስን ፡ ጥሪ ፡ ሰምተው ፡ የተቀበሉ ፡ ብቻ ፡ እውነተኞች ፡ ሰባኪዎች ፡ እንደሚሆኑን ፡ ነው ። ማደሪያ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ የስብከቱን ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሙያ ፡ የሚቈጥረው ፡ ሰው ፡ በትክክለኛው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ባለመቆሙ ፡ ከእውነተኛ ፡ ግብ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ እንደሚወድቅና ፡ «እረኛ ፡» መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ «ብንደኛ ፡» መሆኑን ፡ ይገልጽበታል ። የሚከተሉት ፡ ምዕራፎች ፡ በእውነቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዚህ ፡ ለተቀደሰ ፡ አገልግሎቱ ፡ እንደ ፡ ጠራቸው ፡ ለሚያምኑና ፡ የተቻለቸውን ፡ ያህል ፡ ከልብ ፡ ሊደክሙለት ፡ ለሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ተዘጋጅተዋል ።

የወንጌል ፡ ስብከት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ እንደያዘ ፡ አንገምት ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በተመላለሰበት ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜውን ፡ ወይም ፡ የሥራውን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ያሳለፈበት ፡ ታላቅ ፡ ተግባር ፡ በመሆኑ ፡ በሰማይ ፡ ላለው ፡ ላባቱ ፡ ስለ ፡ ሐዋርያቱ ፡ የጸለየው ፡ ያስገነዝበናል ፡ «ወደ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ላክኋቸው ።» (ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።)



www.ethiopianorthodox.org

በስብከት ፡ ሞኝነት ፡ የሚያምኑትን ፡ ሊያድን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖአልና ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፥ ፳፩ ።)

አሜን ።

ዮ ፡ ረ ፡ ጸ ፡

---



# መጽሔተ ፡ ስብከት ።

## ምዕራፍ ፡ አንድ ።

## <u>የስብከት ፡ ትርጓሜ ።</u>

ስብከት ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ትርጒም ፡ የያዘ ፡ መንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ ነው ። በአንድ ፡ ስብከት ፡ ውስጥም ፡ አምስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ዓምዶች ፡ ሊኖሩት ፡ ይገባል ። እነዚህም ፤ ፩ ፥ የስብከቱ ፡ አቅዋም ፡ ወይም ፡ መሠረቱ ፤ ፪ ፥ አከፋፈሉ ፡ ወይም ፡ አመዳደቡ ፤ ፫ ፥ አበጣጠሩ ፡ ወይም ፡ አተረጓጎሙ ፤ ፬ ፥ አሠራሩ ፤ ፭ ፥ አጠቃለሉ ፤ አሰባሰቡ ፡ ወይም ፡ ዓላማውና ፡ አስተሣሰሩ ፡ ናቸው ። የአንድ ፡ ስብከት ፡ አቅዋም ፡ እነዚህን ፡ መሠረታውያን ፡ ምድቦች ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፥ ለአድማጩ ፡ የለዘበ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምግብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ በመመገብ ፡ መንፈሱን ፡ ጸጥ ፡ አድርጎ ፡ ነፍሱን ፡ ያረካለታል ።

ስብከት ፡ በአድማጩ ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀረጽ ፡ ሆኖ ፥ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተውጣጣ ፡ የሃይማኖት ፡ እውነት ፡ የያዘ ፡ ነፍስን ፡ ከሥጋ ፡ አጣምሮ ፡እንዲማርክ ፡ ሆኖ ፡ በጥንቃቄ ፡ የተዘጋጀ ፡ መንፈሳዊ ፡ የቃል ፡ ንግግር ፡ ነው ።

፩ ፥ <u>የቃል ፡ ስብከት</u> ፤ የቃል ፡ ስብከት ፡ ማለት ፡ በጨዋ ፡ ሰውነትና ፡ በመልካም ፡ አንደበት ፡ ለሌሎች ፡ሰ



www.ethiopianorthodox.org

ዎች ፡ በመንገር ፡ እውነትን ፡ የማስተላለፍ ፡ ዘዴ ፡ ወይም ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ነው ። መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም፡ ይህን ፡ መንገድ ፡ መርጦ ፡ በመያዝ ፡ የራሱን ፡ እውነት ፡ ለ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ አስተማረና ፡ እነሱም ፡ እየዞሩ ፡ ይህንኑ ፡ እውነት ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱና ፡ የምሥራቅ ፡ እስያ ፡ የሃይማኖት ፡ መሪ ፡ ጋውታማ ፡ ቡድሀ ፡ እንዲሁም ፡ ሶቅራ ጥስ ፡ የተባለው ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፋ ፡ ትምህርታቸውን ፡ በ ቃል ፡ ስብከት ፡ ብቻ ፡ ለትውልድ ፡ አስተላለፉ ፡ እንጂ ፡ በእጃቸው ፡ የጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ አይገኝም ። መድኃኒታ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ «እኔ ፡ እውነት ፡ ነኝ ፡» ይላል ። ስለዚህ ፡ እውነት ፡ ከተፈጥሮ ፡ ሰውነት ፡ የሚወጣ ፡ አንድ ፡ ኃይል ፡ ነው ። እንደዚህም ፡ ሲሆን ፡ እውነትን ፡ የመናገር ፡ ልማድ ፡ ካለው ፡ ከሕያው ፡ ሰባኪ ፡ ከንፈር ፡ የሚነገር ፡ ከልብ ፡ ስር ፡ የመነጨ ፡ እውነት ፡ «ስብከት ፡» ይባላል ። ይህ ፡ ከሆነም ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ጥሩ ፡ ሰባኪዎች ፡ ሊ ሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ የሚገኙት ፡ ሁለቱ ፡ የአ ዲስ ፡ ኪዳን ፡ ቃሎችም ፡ «መልእክትና ፡» «ምስክርነት ፡» ናቸው ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሰባኪ ፡ ብቅዓት ፡ ያለው ፤ ራሱን፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ የሰጠ ፤ ከእግ ዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ የተላከ ፡ መልእክተኛ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪ ፡ <u>አድማጭ ፡ እንደሚያስተውለው ፡ ሊሆን ፡ ይገ ባል</u> ። አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ሰባኪ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገንና ፡ ዘር ፡ ላሉበት ፡ አድማጮች ፡ ንግግሩን ፡ ያቀርባል ። በጌታችን ፡



በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አድማጮች ፡ መካከል ፡ ታላላቅና ፡ ዝቅተኞች ፤ ባለጸጎችና ፡ ምስኪን ፡ ድሆች ፤ ሊቃውንትና ፡ መሃይሞች ፡ ተቀላቅለው ፡ ይገኙበት ፡ ነበር ። «ብልሆችና ፡ ጭምቶች ፡» የተባሉት ፡ ያቀርቡበት ፡ ለነበረው ፡ ተቃራ ኒና ፡ አሳች ፡ ጥያቄም ፡ ትክክለኛውን ፡ መልስ ፡ በመስጠት ጸጥ ፡ ያደርግ ፡ የነበረውን ፡ ታላቁን ፡ ሰባኪ ፤ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ በደስታ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ። ወደ ፡ አንድ ፡ ጐን ፡ ያዘነበሉ ፡ ብዙ ፡ ሰባኪዎች ፡ አድማጮቻቸውም ፡ ምርጥ ፡ ምርጥ ፡ ሰዎች ፡ እንዲሆኑላቸው ፡ ይፈልጋሉ ። ሐዋርያት ፡ ጥልቅ ፡ ትምህርት ፡ ባይኖራቸውም ፡ በጣም ፡ የተማሩትን፡ አድማጮቻቸውን ፡ ያስደንቁ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ በሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ እናነባለን ። ይህም ፡ የሚያስረዳው ፡ ጥልቅ ፡ ትምህ ርት ፡ ባይኖረውም ፡ እውነትን ፡ የጨበጠ ፡ አንድ ፡ ትሁት ፡ ሰባኪ ፡ «በዚህ ፡ ጉባኤ ፡ ፊት ፡ ቆሜ ፡ እንዴት ፡ ልስበክ ፡» የሚል ፡ የዕፍረት ፡ መንፈስ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ ሊያሳድር ፡ እንደማይገባው ፡ ነው ። እውነተኛ ፡ ስብከት ፡ የሚዘረጋው፡ ዘርና ፡ የወገን ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ ለሰው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ልብና ፡ ሕሊና ፡ ነው ። የሰው ፡ ነፍስ ፡ ከማናቸውም ፡ ልዩ ፡ ወገንና ፡ ነገድ ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እውነተኛ ፡ ስብከት ፡ የወገንና ፡ የጐሣ ፡ ልዩነት ፡ የሌለበት ፡ ያልተወ ሰነ ፡ ስለሆነ ፡ የንባብን ፡ (ሊተርቸር ፡) ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የያዘ ፡ ነው ።

፫ ፡ <u>በሃይማኖት ፡ እውነት ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ ይ ገባል</u> ። እውነት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ነፍስን፡ የሚያድን ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ በሳይንስ ፡ መንገድ ፡ በእውነት ፡ የተ ፈጸሙ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ እንዳሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ግን ፡ ጥቅማቸው ፡ በዚያው ፡ በክፍላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ለነፍስ ፡ ደኅንነት ፡ የሚያገለግሉ ፡ አይሆኑም ። እንዲሁም ፡
ስብከት ፡ ሲባል ፡ ለሕዝብ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ የሃይማኖት ፡
መስመር ፡ ከወጣ ፡ ስብከት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። አትሮ
ኖስ ፡ ስብከት ፡ አይባልም ። ስብከቱ ፡ ግን ፡ አትሮኖስ ፡
ቢባል ፡ ይቻላል ። ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ በአትሮ
ኖስ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ቢነበብም ፡ ስብከት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም፤
እንደዚሁም ፡ የፖለቲክ ፡ ንግግር ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡
ውስጥ ፡ ቢጠቀስለት ፡ ስንኳ ፡ ስብከት ፡ አይሆንም ። ሆ
ኖም ፡ የሳይንስና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበባት ፡ የፖለቲክ ፡ ንግግ
ሮች ፡ ሌላም ፡ ማናቸውም ፡ ኗሪ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሃይማኖት
ን ፡ እውነት ፡ ለመግለጽና ፡ ለማስረዳት ፡ ምሳሌና ፡ መጽ
ሔት ፡ አድርጎ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

፲ ፡ <u>በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደተጻፈ ፡ ብቻ ፡</u> መጥ
<u>ቀስ ፡ ይገባል</u> ። ክርስትና ፡ ያለ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሊኖር ፡
ስለማይችል ፡ የክርስቲያን ፡ ስብከት ፡ ደግሞ ፡ ከመጽሐፍ ፡
ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ስህተት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊገባ ፡ የቻለው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በ
ተናቀ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ፕሮቴስታንቶች ፡ ያደረጉት ፡ የሃይማ
ኖት ፡ መታደስ ፡ የተነሳበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ማርቲን ፡
ሉተርና ፡ ጓደኞቹ ፡ ተረስቶ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ቃልና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ የነበረ
ውን ፡ የተበላሸ ፡ የማዕበል ፡ ሞገድ ፡ ያተረማመሰውን ፡ ት
ምህርት ፡ ስለተመለከቱ ፡ ነው ። የሃይማኖት ፡ እንቅስቃሴ ፡
የተባለው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በመመለስ ፡



የተገኘ ፡ ውጤት ፡ መሆኑ ፡ ሊካድ ፡ አይቻልም ። አንዳንድ ፡
የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የእውነት ፡ ቃሎች ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡
ልብ ፡ ሰርፀው ፡ ሰውዬውን ፡ ገንዘባቸው ፡ ካደረጉትና፡ከገ
ኙት ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲያውጅ ፡ ያስገ
ድዱታል ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ መስበኪያው ፡ አትሮኖሱ ፡
ሳይለያዩ ፡ ሁልጊዜ ፡ ተጣምረው ፡ መገኘት ፡ አለባቸው ።
አንዳቸውን ፡ መናቅ ፡ ሌላውንም ፡ እንደመናቅ ፡ ይቈጠ
ራል ። የተሰቀለውን ፡ ክርስቶስን ፡ ለመስበክ ፡ መጽሐፍ ፡
ቅዱስን ፡ መያዝ ፡ ግድ ፡ ነው ።

፲፩ ፡ <u>በጥንቃቄ ፡ ሊመደብ ፡ ይገባል</u> ፤ አንድ ፡ ስብ
ከት ፡ በጥንቃቄ ፡ የተገጣጠመ ፡ የተወሰኑ ፡ ክፍሎች ፡ ያ
ሉት ፡ አካል ፡ ነው ። ዋናው ፡ ያሁኑ ፡ ትምህርታችን ፡ ስብ
ከታችንን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ የምናዘጋጅበትን ፡ መንገድ ፡
ማጥናት ፡ ነው ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥራ ፡ ፈትነትን ፡
ወይም ፡ ስንፍናን ፡ ከቶ ፡ አያደፋፍርም ። በጥንቃቄና ፡ በረ
ድፉ ፡ የተዘጋጀ ፡ ስብከት ፡ በቀላሉ ፡ ሊታወስ ፡ ይቻላል ።
ይህም ፡ ከሰባኪው ፡ የሚፈለግ ፡ ከፍተኛ ፡ የጥንቃቄ ፡ ፍሬ ፡
ነው ። አንዱን ፡ ስብከት ፡ በብርቱ ፡ ጥንቃቄ ፡ ሳያዘጋጁ ፡
ለመስበክ ፡ መነሣት ፡ የማይቻል ፡ ነው ። እግዚአብሔርም ፡
በታላቅ ፡ ድካምና ፡ በታማኝነት ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ይባ
ርካል ። በሞቀ ፡ አንደበት ፡ የሚደረግና ፡ የሚገፋፋ ፡ ስብ
ከት ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ በተሰበከ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ የተዘጋ
ጀና ፡ የብዙ ፡ ዓመት ፡ የሥራ ፡ ብስል ፡ ፍሬ ፡ መሆኑ ፡ አይ
ጠረጠርም ። ደግሞም ፡ ስብከትን ፡ ለማዘጋጀት ፡ የመንፈ
ስና ፡ የባሕርይ ፡ እርጋታ ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ መሣሪያዎች ፡
ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

፯ ፥ ለማስረዳትና ፡ ለማግባባት ፡ ሊደከምበት ፡ ይገ
ባል ፥ ስብከት ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከተው ፡ ወደዚህ ፡ ዓላማ ፡
ነው ። አንድ ፡ ኤክስፖዚሲዮን ፤ አንድ ፡ ክርክር ፤ አንድ ፡
መጽሔት ፡ የሚቀርቡት ፡ ለራሳቸው ፡ እንዲታዩና ፡ እንዲ
ሰሙ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፥ የአድማጮቹን ፡ ፈቃድ ፡ ቀስቅሶ ፡
እተግባሩ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ለማግባባት ፡ ነው ። የአትሮ
ኖስና ፡ የቲያትር ፡ መጫወቻ ፡ ቦታ ፡ (ስቴጅ ፡) የሚለየው ፡
እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ። የቲያትር ፡ ቦታ ፡ (ስቴጅ ፡) የሰውነት ፡
ውዝዋዜና ፡ የሚሰማው ፡ የአንደበት ፡ ስልት ፡ ተመልካ
ችን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ነው ። ከአትሮኖስ ፡ የሚሰማው ፡
ቃል ፡ ግን ፡ ሰሚዎቹን ፡ ሰዎች ፡ ቀስቅሶ ፡ እንደዚሁ ፡ ካለ ፡
ተግባር ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። አንድ ፡ ስብ
ከት ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ትምህርት ፡ ለመግለጫ ፡ ያኽል ፥ ወ
ይም ፡ የቲያትርን ፡ ውዝዋዜ ፡ የመሰለ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡
ከፍ ፡ ወደ ፡ አለ ፡ ስህተት ፡ ይጥላል ። ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ሰዎች ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ሐሳባቸውን ፡ እን
ዲወስኑበት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። ሰባኪዎች ፡ ዘወትር ፡
ራሳቸውን ፡ «በዚህ ፡ ስብከቴ ፡ ወደ ፡ የትኛው ፡ ዓላማ ፡
ነው ፡ የማመራው ?» ብለው ፡ ቢጠይቁና ፡ ይህም ፡ ልዩ ፡
ጉዳይ ፡ በሐሳባቸው ፡ ሁልጊዜ ፡ ግልጽና ፡ የተወሰነ ፡ ቢሆን ፡
ስንቱን ፡ ያኽል ፡ ያልተወሰነና ፡ የተዘበራረቀ ፡ የማያግባ
ባም ፡ ንግግር ፡ በተወገደ ፡ ነበር ።



ምዕራፍ ፡ ሁለት ።

# የስብከት ፡ አከፋፈል ፡ (አመዳደብ ።)

አንድ ፡ ሰባኪ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ለ
ልዩ ፡ ልዩ ፡ አትሮኖስ ፡ የሚነጋገርባቸውን ፡ ስብከቶች ፡
እንዴት ፡ እንደሚመርጣቸው ፡ እንመልከት ።

ስብከቶች ፡ የሚወሰዱት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥ
ቅስ ፡ ሲሆን ፥ የየጥቅሱን ፡ ሐሳብ ፡ መከተል ፡ ይገባል ።

አንድ ፡ ስብከት ፡ እንደ ፡ ጥቅሶቹ ፡ ሁኔታ ፡ በሦስት ፡
ታላላቅ ፡ ክፍል ፡ ይመደባል ።

፩ ፥ የንግግር ፡ ስብከት ፥ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጥ
ቅስ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ መግቢያ ፡ እንዲሆን ፡ ይወሰ
ዳል ፡ ሆኖም ፡ ንግግሩ ፡ ከዋናው ፡ ጥቅስ ፡ ጋር ፡ ኅብረት ፡
እንዲኖረው ፡ ግዴታ ፡ አይደለም ። እንዲያውም ፡ በዛም ፡
አነሰም ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ የቻለ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። የዚህ ፡
ዓይነት ፡ ስብከት ፡ የጥቅሱ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ ወደሚያመ
ለክተው ፡ ይመሠረታል ፡ እንጂ ፥ ጥቅሱን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡
መውሰድ ፡ አያሻም ። በዚህ ፡ የስብከት ፡ ክፍል ፡ አብዛ
ኛው ፡ ጊዜ ፡ የሚነጋገሩበትን ፡ ጉዳይ ፡ አስቀድሞ ፡ መመ
ደብና ፡ ቀጥሎም ፡ ለዚሁ ፡ የሚስማማውን ፡ ጥቅስ ፡ ማግ
ኘት ፡ ነው ። ለዚህ ፡ የስብከት ፡ ክፍል ፡ ከአንድ ፡ የመጽ
ሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅስ ፡ ይልቅ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ቢወሰድ ፡



www.ethiopianorthodox.org

የተሻለ፡ነው።አንዳንድ፡ልዩ፡ልዩ፡አጋጣሚ፡ጉዳዮች፡የንግግር ፡ ስብከት ፡ ይደረግባቸዋል ። ለምሳሌ ፡ ለወንጌል ፡ መልእክተኛነት ፡ ሲመረጡ ፤ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ማዕረግ ፡ ሲባረኩ ፤ የምስጋና ፡ ቀን ፤ ከመጥፎ ፡ አሮጌ ፡ ባሕርይ ፡ በተወሰኑ ፡ ጊዜ ፤ በቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፤ በአዲስ ፡ ዘመን ፡ መለወጫ ፡ ቀን ፤ በሰንበት ፡ ቀንና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ በሚውሉበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰባኪ ፡ ከኤፌሶን ፡ ፪ ፤ ፲፪ ፡ ላይ ፡ ጥቅሱን ፡ ወስዶ ፡ «ስለ ፡ ጊዜው ፡ አለመታመን ፡» ንግግር ፡ ሲያደርግ ፡ ይህ ፡ አለመታመን ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊነት ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ እንደምን ፡ እንደሚገባ ፡ አስረድቶበታል ። ሌላም ፡ ሊቅ ፡ አዲስ ፡ ፍቅር ፡ በኃይል ፡ እንዴት፡ እንደሚሠርፅ ፡ ከ፩ኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ ፤ ፲፰ ፡ ወስዶ ፡ ሰብኳል ። በ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ አንድ የወንጌል ፡ ሰባኪም ፡ ከማርቆስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፰ ፤ ፴፰—፵፫ ፡ አንድ ፡ ጥቅስ ፡ ወስዶ ፡ ስለ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሰብአዊነት ፡ አንድነት ፡ ሰብኳል ። ሌላውም ፡ ሰባኪ ፡ «ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሐሳብ ፡» በሚል ፡ አርእስት ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ፻፵፫ ፤ ፰ ፡ ጥቅሱን ፡ ወስዶ ፡ ሰብኳል ። በአጋጣሚ ፡ ዕለት ፡ ለሚሆን ፡ የንግግር ፡ ስብከት ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ «አሁን ፡ ለምን ፡ ተአምራት ፡ አይታይም ፡» በሚል ፡ አርእስት ፡ ከማቴዎስ ፡ ፲፮ ፤ ፬ ፡ እንዲሁም ፡ «የራሱም ፡ ፀጉር ፡ እንደገና ፡ ያድግ ፡ ጀመር ፡» በሚል ፡ አርእስት ፡ ከመሳፍንት ፡ ፲፮ ፤ ፳፪ ፡ ሊወሰድ ፡ ይቻላል ።

የንግግር ፡ ስብከት ፡ ለዚያው ፡ ለሰዓቱና ፡ ለአጋጣሚው ፡ ጉዳይ ፡ በዚያው ፡ በቦታው ፡ ሲሆን ፡ ጥቅም ፡ አ



ለው ፤ ሆኖም ፡ በልዩ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ ያሻል ፤ በተቀረስ ፡ በሰባኪው ፡ በኩል ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ንቀት ፡ ያስከትልበታል ። አንድ ፡ ሰባኪ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ትቶ ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ የተመረኰዘ ፡ እንደሆነ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ። ስለዚህ ፡ በጣም ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት ። በአጋጣሚና ፡ በምክንያት ፡ ቀን ፡ የሚደረጉ ፡ ንግግሮች ፡ እንደ ፡ ምክንያቱ ፡ አበዛዝ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አርእስቶችና ፡ ለጉዳዩም ፡ የሚጠቅሙ ፡ ስብከቶች ፡ ሊደረጉባቸው ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፤ የተዘወተሩ ፡ እንደሆን ፡ ያንኑ ፡ ቃል ፡ መደጋገም ፡ ይሆንና ፡ ጣዕሙን ፡ ያጠፋዋል ።

፪ ፤ <u>ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የሚወሰድ ፡ የጥቅስ ፡ ስብከት</u> ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስብከት ፡ ተመርጦ ፡ ከተወሰደው ፡ የጥቅስ ፡ ቃል ፡ ሳይርቅ ፤ ክፍል ፡ በክፍሉ ፤ ቃል ፡ በቃል ፤ መከታተል ፡ አለበት ። የተወሰደው ፡ ጥቅስ ፡ መጀመሪያ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደተነገረ ፡ የሥር ፡ ታሪኩን ፡ አብራርቶ ፡ መግለጽና ፡ ማስረዳት ፡ አለ ፤ ቀጥሎም ፡ ጥቅሱን ፡ ለአሁኑ ፡ ዘመናችን ፡ ጠባይና ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ እንደምንገልጽበት ፡ ማሰብ ፡ አለ ። ጥቅሱን ፡ ለመምረጥና ፡ ለመተንተን ፡ ብልህነትን ፡ ይጠይቃል ።

መዝሙር ፡ ዘዳዊት ፡ ፵፰ ፤ ፲፮ ፡ አንተ ፡ እጅህን ፡ ትዘረጋለህ ፡ ሕያውንም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ በጎ ፡ ፈቃድህ ፡ ታጸግባለህ ፡ የሚለው ፡ ጥቅስ ፡ ሲተነተን ፤

የእግዚአብሔር ፡ ሦስት ፡ ስጦታዎች ፡ እንዳሉበት ፡ ያሳያል ፤

፩ ፤ እራሱ ፡ (አንተ) ፡ በማለቱ ፡



www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ (እጅህን ፡ ትዘረጋለህ ፡)
፫ ፡ በሙላት ፡ (እንደ ፡ በጎ ፡ ፈቃድህ ፡ ታጸግባለህ ፡)

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ፡ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ጸጋ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ሁሉንም ፡ አጸናቸው ፡ በጌታ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ በጸና ፡ በልባቸው ፡ ፈቃድ ፤ የሚለው ፡ ጥቅስ ፡ እንደሚከተለው ፡ ሆኖ ፡ በቀላሉና ፡ ለማስተዋል ፡ በማያስቸግር ፡ ክፍል ፡ ሊተነተን ፡ ይቻላል ።

፩ ፡ በርናባስ ፡ ምን ፡ እንዳየ ፡ (የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡)
፪ ፡ ምን ፡ እንደተሰማው ፡ (ደስ ፡ አለው ፡)
፫ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ (በጸና ፡ በልባቸው ፡ ፈቃድ ፡ በጌታ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አጸናቸው ፡ መከራቸው ፡)

፩ኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ፡ እኛ ፡ እንወደዋለን ፡ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወዶናልና ።

ለክርስቶስ ፡ ያለን ፡ ፍቅር ፤
፩ ፡ በግልጽ ፡ ሊታመኑበት ፡ የሚገባ ፡ (እንወደዋለን ፡)
፪ ፡ ከአንድ ፡ ምክንያት ፡ የሚወጣ ፡ ተግባር ፡ (የምን ወደው ፡ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ወደደን ፡ ነው ።)
፫ ፡ በምስጢር ፡ የተመሠረተ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡
፬ ፡ በሌላ ፡ ኃይል ፡ የተያዘ ፡ አንድ ፡ ኃይል ፡

አንድ ፡ ሰባኪ ፡ ደግሞ ፡ ጌታችን ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ያለቀሰላትን ፡ ልቅሶ ፡ (ሉቃስ ፡ ፲፱ ፡ ፵፩—፵፬ ፡) «በአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ጊዜዎች ፡» ብሎ ፡ እንደሚከተለው ፡ መድቦታል ።



፩ ፡ የጸጋ ፡ ቀን ፡ (በዚች ፡ በቀንሽ ፡)
፪ ፡ የዕውርነት ፡ ቀን ፡ (ዛሬ ፡ ከአይንሽ ፡ ተሰውሯል ፡)
፫ ፡ የፍርድ ፡ ቀን ፡ (ጸላቶችሽ ፡ ቅጥር ፡ ቀጥረው ፡ የሚከቡብሽ ፡ ቀን ፡ ይመጣልና ፡ ወዐዘ ።)

አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰባኪ ፡ ደግሞ ፡ ከዮሐንስ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ «ዳግመኛ ፡ ልትወለዱ ፡ ያስፈልጋችኋል ፡» የሚለውን ፡ ጥቅስ ፡ ወስዶ ፡ በስብከቱ ፡ መግቢያ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራው ፡ ታላቁ ፡ ሥራ ፡ ብሎ ፡ በመሰየም ፡ በሚከተሉት ፡ መደቦች ፡ ከፋፍሎታል ።

፩ ፡ የትምሕርቱ ፡ መሠረት ፡ ዳግመኛ ፡ እንድንወለድ ፡ የሚያስፈልግበት ፡ ምክንያት ፡ የተፈጥሮአችን ፡ መበላሸት ፡ ነው ።

፪ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ዳግመኛ ፡ እንዴት ፡ እንደሚወለድ ፡ ሲያስረዳ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የፍጥረት ፡ «የተፈጥሮ ፡» መለወጥ ፡ እንዴት ፡ እንደሚሆን ፡ ይዘረዝራል ።

፫ ፡ ለምን ፡ ውጤት ፡ ዳግመኛ ፡ መወለድ ፡ እንደሚያስፈልገን ፡ ሲያስረዳ ፡ ለቅድስናና ፡ ለዘለዓለማዊ ፡ ደስታ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ።

፬ ፡ ዳግመኛ ፡ መወለድ ፡ ከሚለው ፡ የሚገኘው ፡ አንዳንድ ፡ መደምደሚያ ፡ ለምሳሌ ፡ ጥምቀት ፡ ዳግመኛ ፡ መወለድ ፡ ከሚለው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አይደለም ። ብቅዓት ፡ ዳግመኛ ፡ በመወለድ ፡ የሚገኝ ፡ የጸጋ ፡ ዕድገት ፡ ስለሆነ ፡ ዳግመኛ ፡ ከመወለድ ፡ ጋር ፡ እኩልነት ፡ የለውም ።



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ «የአምላክ ፡ ቀን ፡» በሚል ፡ ስብከት ፡ ጥቅሱን ፡ «በጌታ ፡ ቀን ፡ በመንፈስ ፡ ነበርኩ ፡» በሚል ፡ ከራእይ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ወስዶ ፡ እንደሚከተለው ፡ ከፋፍሎታል ።

፩ ፡ ለጊዜያችን ፡ ቢያንስ ፡ ከሰባት ፡ አንደኛውን ፡ ክፍል ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ ልናውለው ፡ ግዴታችን ፡ ነው ።

፪ ፡ ጊዜ ፡ እየለየን ፡ ደግሞ ፡ ምድራዊ ፡ ሥራችንን ፡ ልናቆም ፡ ተግባራችን ፡ ነው ።

፫ ፡ ክርስቲያን ፡ «የአምላክን ፡ ቀን ፡» ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ የሚያከብረው ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ስለ ፡ ተነሣበት ፡ ነው ።

፬ ፡ የጌታ ፡ ቀን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክበት ፡ ቀን ፡ እንዲሆን ፡ ተመድቦአል ።

ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅስ ፡ የሚወሰድ ፡ ስብከት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮችና ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ የሚገኝበት ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከቶ ፡ የማያልቅ ፡ የመንፈስና ፡ የእውነት ፡ ትምህርት ፡ የማዕድን ፡ ጉድጓድ ፡ ነው ። ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅስ ፡ የሚደረግ ፡ ስብከት ፡ ፍሬያማ ፡ የሆነ ፡ ረጅም ፡ የመልእክት ፡ ምሥጢር ፡ የያዘ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ስብከታችን ፡ አብዛኛውን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅሶች ፡ መሆን ፡ ይገባል ።



፫ ፡ <u>ትእይንታዊ ፡ ስብከት</u> ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስብከት ፡ አብዛኛውን ፡ በስዕል ፡ ወይም ፡ በትእይንት ፡ መሆን ፡ አለበት ፡

ሀ) በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ ታላላቅ ፡ ቃሎች ፡ መርጦ ፡ መስበክ ፡ እጅግ ፡ ይጠቅማል ። ለምሳሌ ፡ ጽድቅ ፤ ይቅርታ ፤ እውቀት ፤ ርኅራኄ ፤ ፍርድ ፤ ወርቅ ፤ ተስፋ ፤ ጸጋ ፤ እነዚህንም ፡ በመሳሰሉት ፡ ማለት ፡ ነው ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ በሚጽፉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎች ፡ አንዱን ፡ ቃል ፡ መጻፍና ፡ አንዱ ፡ ጸሐፊ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ አንዱን ፡ ቃል ፡ በሚያገባበት ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። ለዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ድጋፍ ፡ ማድረግ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ።

ለ) አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ጥቅስ ፡ ለትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ መምረጥ ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ፻፳፩ ፡ ፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂህ ፡ ነው ፤ የሚለው ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

ሐ) የአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ሙሉ ፡ ምዕራፎች ፡ ወደ ፡ በጣም ፡ ተጠንቅቆ ፡ አቋሙን ፡ ሁሉ ፡ ከመግቢያው ፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መደምደሚያው ፡ ድረስ ፡ በረድፍ ፡ በረድፉ ፡ በአጫጭር ፡ የተጠቃለለ ፡ አርእስት ፡ ሲከፋፍሉት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ። ለምሳሌ ፡ የነቢዩ ፡ የዓሞጽን ፡ መጽሐፍ ፡ በሙሉ ፡ ወስዶ ፡ በሚከተሉት ፡ አርእስቶች ፡ ለመከፋፈል ፡ ይቻላል ።



www.ethiopianorthodox.org

፩ ፡ «ነቢዩና ፡ ጥሪው ፡» ዓሞጽ ፡ ፩ ፥ ፩ ። ፫ ፥ ፲—፲፯ ።
፪ ፡ «የሕዝቦችና ፡ የይሁዳ ፡ ክስ ፡» ዓሞጽ ፡ ፩ ፡ ፪ ፥ ፪-፭ ።
፫ ፡ «የእስራኤል ፡ ክስ ፡ መብትና ፡ ምስጋና ፡ ቢስ ነት ፡» ዓሞጽ ፡ ፪ ፥ ፮—፲፮ ።
፬ ፡ «መብትና ፡ ኃላፊነት ፡» ዓሞጽ ፡ ፫ ፥ ፩ ፡ ፪ ።
፭ ፡ «ትንቢት ፡ የመናገር ፡ ግዴታ ፡» ዓሞጽ ፡ ፫ ፥ ፫—፰ ። ይህ ፡ ክፍል ፡ «ነቢዩና ፡ ጥሪው ፡» ከሚለው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በ፩ኛው ፡ ክፍል ፡ ከተመደበው ፡ ጋር ፡ ሊጠቃለል ፡ ይቻላል ።
፮ ፡ «ኃይለኛ ፡ ክርክር ፡» ዓሞጽ ፡ ፬ ፥ ፬—፲፫ ።
፯ ፡ «ነቢዩ ፡ ሕዝቡን ፡ በመምከር ፡ ሊያስታርቅ ፡ እንደታገለ ፡» ዓሞጽ ፡ ፭ ፥ ፬—፯ ፤ ፲፬ ፡ ፲፭ ።
፰ ፡ «እግዚአብሔር ፡ ሐሰትን ፡ እንደሚጠላ ፡» ዓሞጽ ፡ ፭ ፥ ፲፰ ፡ ፳፯ ።
፱ ፡ «ነቢዩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለማማለድ ፡ እንደ ፡ ጮኸ ፡» ዓሞጽ ፡ ፯ ፥ ፩—፮ ።
፲ ፡ «ጥፋትና ፡ መታደስ ፡» ዓሞጽ ፡ ፱ ።

መ) የቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ለትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አስረጅ ፡ ነው ። አንድ ፡ የሕይወት ፡ ዘመን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ የያዘ ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ ታሪኩ ፡ ሁኔታ ፡ በክፍል ፡ በክፍሉ ፡ በመለየት ፡ ይመደባል ። ለምሳሌ ፡ የአብርሃም ፤ የዮሴፍ ፤ የዳዊት ፤ የጴጥሮስ ፤ የጳውሎስ ፡ ወበዘ ፡ የሕይወት ፡ ታሪ



ሮች ፡ የተለያዩ ፡ ትእይንታዊ ፡ ስብከቶች ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስችሉ ፡ ናቸው ።

ትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ ራሱ ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ መሠረት ፡ የያዘ ፡ ነው ። ይህ ፡ ትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥንታዊ ፡ የሆነ ፡ ስብከት ፡ የተጀመረበትና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፡ ከፍተኛውን ፡ የአትሮኖስን ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተነግሮለታል ። መድኃኒታችን ፡ በመስጊዱ ፡ ውስጥ ፡ የኢሳይያስን ፡ መጽሐፍ ፡ ገልጦ ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳበት ፡ ስብከት ፡ ለክርስቲያን ፡ ሰባኪዎች ፡ የዘወትር ፡ ረዳታቸው ፡ ሆኗል ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ የ[illegible] ፡ ታላላቅ ፡ ሰባኪዎች ፡ የተሰኙት ፡ ይህን ፡ ትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ በማዘውተራቸው ፡ ነው ። ለራሱ ፡ ለሰባኪውም ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይረዳዋል ።

ትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ ለሰንበት ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ ለመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ትምህርት ፡ ማሰናጃ ፡ ከሁሉ ፡ [illegible]ጠ ፡ ጥቅም ፡ አለው ።

በአትሮኖስ ፡ ስብከት ፡ ጊዜ ፡ በአጫጭር ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎች ፡ ቢጀመር ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ «ሩት ፤ የመከሩ ፡ ሰብል ፡ ታሪክ ፡» «ፊሊሞን ፡ ትሑት ፡ ሐዋርያ ፤» «ለ፯ቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የተላከ ፡ መልእክት ፡» «የተራራ ፡ ስብከት ፡» «ምስጋናዎች ።» አንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንቶችና ፡ ሰባኪዎች ፡ የተረጎሙአቸውን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎችን ፡ ማጥናት ፡ ለትእይንታዊ ፡ ስብከት ፡ ዓይነተኛ ፡ ጥቅም ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ከመለዋወጥ ፡ የሚመነጭ ፡ የት
እይንታዊ ፡ ስብከት ፡ አከፋፈል ፡ ደግሞ ፡ አለ ።

ሀ) <u>ገላጭ ፡ ስብከት</u> ፤ ለምሳሌ ፡ መሠረተ ፡ ትምህ
ርት ፤ ተግባር ፤ ክብረ ፡ በዓል ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡
ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄን ፡ ይጠይቃሉ ።

ለ) <u>መጽሔታዊ ፡ ስብከት</u> ፤ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስብ
ከት ፡ የሚደረገው ፡ ሐሳቡ ፡ እንደ ፡ ስዕል ፡ ጐልህ ፡ ሆኖ ፡
በሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ተስማሚ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁል
ጊዜም ፡ መጽሔቶች ፡ (ስዕሎች ፡) ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታን ፡
ይሰጣሉ ። ሆኖም ፤ መጠንቀቅ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ስሜትን ፡
የሚቀላቅሉ ፡ ክብር ፡ የተጓደለባቸው ፡ እንዳይሆኑና ፡ ለዋ
ናው ፡ ዓላማም ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጡ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈልጋል ፤
ይበልጡንም ፡ በእጅ ፡ የተያዘውን ፡ ዓይነተኛውን ፡ ጉዳይ ፡
የሚገልጹ ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ፡ እንጂ ፤ ሐሳብን ፡ ወደ ፡
ሌላ ፡ የሚያዋልሉ ፡ እንዳይሆኑ ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልጋል ፤
ይህም ፡ ማለት ፡ መጽሔቶቹ ፡ (ስዕሎቹ ፡) ምን ፡ ያኽል ፡ የ
ሚያጓጉ ፡ ቢሆኑም ፤ ሰባኪው ፡ የሚሰብክበትን ፡ ክፍል ፡
በበለጠ ፡ የሚያብራሩ ፡ እንዲሆኑ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፤ ስለ ፡
ስዕሎቹ ፡ ስለ ፡ ራሳቸው ፡ መግለጫ ፡ ማድረግ ፡ አይገ
ባም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ የተዘጋጀውን ፡ የስብ
ከት ፡ መግቢያ ፡ የማይስማማ ፡ ታሪክ ፡ ወይም ፡ ተረት ፡ በ
መቀላቀሉ ፡ ሲበላሽ ፡ ይታያል ።

ስብከትን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመጽሔት ፡
መግለጫዎችን ፤ አጫጭር ፡ ታሪኮችን ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳ
ቦችን ፡ የሚያከማቹበት ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ መያዝና ፡



የሚሰብኩበትን ፡ ክፍል ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ተንትኖ ፡ መ
ተንተኑ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ።

ሐ) <u>የክርክር ፡ ስብከት</u> ፤ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስብከት ፡
የሚቃጣው ፡ ወደ ፡ መመራመር ፡ ሲሆን ፡ ብዙ ፡ የመሠ
ረተ ፡ ትምህርትን ፡ (ዶክትሪንና ፡) የሞራልን ፡ ከፍተኛ
ነት ፡ ይጠይቃል ። ሆኖም ፤ አንድ ፡ ስብከት ፡ በሞላው ፡ በ
ክርክር ፡ ተጀምሮ ፡ በክርክር ፡ ሊያልቅ ፡ አይገባውም ።

አንድ ፡ ስብከት ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ክፍሎች ፡ ሊይዝ ፡
ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከተያዙት ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡
አብዛኛውን ፡ ቦታ ፡ መያዝ ፡ ይገባዋል ።

ጉባኤውን ፡ በማርካት ፡ ዘወትር ፡ ለመስማት ፡ እን
ዲጓጉ ፡ ለማድረግ ፡ አንድ ፡ ሰባኪ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሚሰብ
ክበት ፡ በአንድ ፡ አትሮኖስ ፡ የሚያደርገው ፡ ስብከት ፡ ሌ
ሎች ፡ ሰዎች ፡ በየተራ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀኖች ፡ እንደሚሰብ
ኩቸው ፡ ያኽል ፡ የተለያዩ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈልጋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ሦስት ።

# የስብከት ፡ አተረጓጐም ፡

## የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ።

አንድ ፡ ስብከት ፡ ዓምደ ፡ ክፍሎች ፡ በ፬ ፡ ይመደባሉ ። እነሱም ፤

፩ኛ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ።

፪ኛ ፡ መግቢያው ።

፫ኛ ፡ በስንት ፡ እንደሚከፋፈልና ፡ መግለጫዎቹ ።

፬ኛ ፡ መደምደሚያው ፡ ናቸው ።

እነዚህ ፡ በሙሉ ፡ ለስብከቶች ፡ ሁሉ ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋሉ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ችላ ፡ ቢባሉ ፡ ደግሞ ፡ የስብከቱ ፡ ኃይል ፡ ደካማ ፡ ይሆናል ። መስበክ ፡ የሚለማመድ ፡ ለአንድ ፡ ጀማሪ ፡ ሰው ፡ የስብከትን ፡ ሕጎች ፡ መጠበቅ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ። ሕጎቹን ፡ ማክበርም ፡ የተፈጥሮው ፡ ማበረታቻ ፡ ይሆነዋል ። ሥርዓቶችንና ፡ (ቴዎሪ ፡) ሕጎችን ፡ ብቻ ፡ እየጠበቁ ፡ በመስበክ ፡ ጥሩ ፡ ሰባኪ ፡ ለመሆን ፡ አይቻልም ፤ ሆኖም ፡ ከስብከት ፡ ውጪ ፡ ሊሰረዙ ፡ ደግሞ ፡ ጨርሶ ፡ አይገባም ።



www.ethiopianorthodox.org

## የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ።

በአንዳንድ ፡ ቦታዎች ፡ አዘውትሮ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ሁለት ፡ ጥቅሶች ፡ የመስበክ ፡ ልማድ ፡ በዛሬው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነቀፋን ፡ አስከትሎአል ። ምክንያቱም ፡ ሐሳቡ ፡ የተያያዘ ፡ መሆን ፡ የሚገባውን ፡ በመለያየትና ፡ በመቈራረጥ ፡ የአርትፊሲያልነትን ፡ ሁኔታ ፡ በማስከተሉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ልማድን ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የባርነት ፡ ቀምበር ፡ ይቈጥሩታል ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ አንዳንድ ፡ ሰባኪዎች ፡ በሚያደርጉት ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ስብከት ፡ እውነት ፡ አለው ። ደግሞም ፡ በቀ ጥታ ፡ ያለማመንታት ፡ የማይካደው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በአንድ ፡ ምዕራፍ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ጥቅስ ፡ ሲሰበክ ፡ ሁልጊዜ ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ያልተከናወነ ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ሆኖም ፥ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በተወሰዱ ፡ ክፍሎች ፡ መስበክ ፡ የበለጠ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። በተቀረስ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎች ፡ መዘርጋት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ባለው ፡ የሕዝብ ፡ አምል ኮት ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ዘመን ፡ ባልገነነም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመ ርጦ ፡ በማከናወን ፡ የሚደረገው ፡ ስብከት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ፍርድ ፡ አይደርስበትም ። በቅዱሳት ፡ መጻ ሕፍት ፡ ያለው ፡ የትርጕም ፡ ብዛት ፡ እጅግ ፡ ነው ። ሰባኪ ውም ፡ በመረጠው ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ አተኵሮ ፡ በማሰብና ፡ በጸሎት ፡ በመጠመድ ፡ ቢወሰን ፥ ለአንድ ፡ ስብከት ፡ የሚ ያስፈልጉትን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የእውነት ፡ ትርጓሜዎች እንደ ፡ ልብ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ። ይልቁንም ፡ በደንበኛ ፡ የወን



ጌል ፡ መልእክተኛነት ፡ በሚደረገው ፡ ስብከት ፡ ወርቃ ፡ ወርቅ ፡ ሕግ ፡ ከክፍሉ ፡ ያለመዛባትና ፡ ክፍሉ ፡ የያዛቸ ውን ፡ እውነቶች ፡ በሰፊው ፡ በመግለጽ ፡ መወሰን ፡ ነው ። ብዙ ፡ ስብከቶች ፡ የሚበላሹት ፡ በሌሎች ፡ ምክንያቶች ፡ ሊሆን ፡ ሰባኪው ፡ ከሚሰብክበት ፡ ክፍል ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ በባዘነ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ።

የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ለአድማጮቹ ፡ ዋ ናውን ፡ ጉዳይ ፡ ለማስተዋወቅና ፡ በስብከቱ ፡ ጊዜ ፡ ሊነ ገሩ ፡ የሚገባቸውን ፡ በየዓይነቱ ፡ መግለጫዎችን ፡ እንዲ ሁም ፡ በስብከቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ አንድነት ፡ አጣ ምሮ ፡ ለመያዝ ፡ እጅግ ፡ ይረዳል ። አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅ ዱስ ፡ ክፍል ፡ የሚያምረው ፡ ሙሉ ፡ የሰዋስው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገርን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ለዚሁም ፡ የአነጋገር ፡ ጣ ዕም ፡ እንዲኖረው ፡ ማሰብ ፡ ይገባል ። «የዘላለም ፡ ኪዳን ፡ ደም ፡» ዕብ ፡ ፲፫ ፥ ፳ ። «እኔ ፡ የማን ፡ ነኝ ፡ ማንንስ ፡ አገለ ግላለሁ ፡» የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ፳፯ ፥ ፳፫ ። «ከእግዚአብ ሔር ፡ ጋር ፡ መታረቅ ፡» ሮሜ ፡ ፭ ፥ ፲ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፥ ፳ ። «ነፍስ ጋ ፡ የሌለውን ፡ ባለ ፡ ጸግነት ፡» ኤፌ ፡ ፫ ፥ ፰ ። «ቅድስና ፡ ለእግዚአብሔር ፡» ዘፀ ፡ ፳፰ ፥ ፴፮ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ የጥቅስ ፡ ቊራሾችን ፡ ያሳያሉ ።

በጣም ፡ አጫጭር ፡ የሆኑ ፡ ጥቅሶች ፡ ለስብከት ፡ አይመቹም ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰባኪ ፡ «አሁን ፡ ጴጥ ሮስ ፡» በሚሉ ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ ሊሰብክ ፡ ሞከረ ። እንዲህም ፡ ሊሆን ፡ ከጥቅሱ ፡ ውጭ ፡ በግድ ፡ ተነድቶ ፡ መውጣት ፡ እን ደሚገባበት ፡ አይጠረጠርም ። እንዲሁም ፡ «ነገር ፡ ግን ፡»



www.ethiopianorthodox.org

በሚሉ : ቃላት : ብቻ : አንድ : ሰው : ሲሰብክ : ተሰምቶአል ። ለስብከት : የሚመረጡት : ጥቅሶች : ሁሉ : ከቅዱሳት : መጻሕፍት : የመነጩ : መንፈሳዊ : ቁም : ነገሮች : የያዙ : እንዲሆኑ : ግዴታ : ነው ።

የሚመረጠው : ክፍል : ረጅም : ወይም : አጭር : እንዲሆን : የሚያስገድደው : ለስብከቱ : ጉዳይ : እንደሚያስፈልገው : ነው ። አንድ : ወይም : ሁለት : ክፍሎች : የሚወስዱበትም : ጊዜ : ይኖራል ። አንድ : ሰባኪ : አንድ : ጊዜ : ሲሰብክ : «ሸክምን፡ መሸከም :» ስለሚለው፡ ጉዳይ፡ ሦስት : የተለያዩ : ጥቅሶች : በማይስማማ : መንገድ : ወስዶ : ተነጋገረባቸው ። እነዚህም : ክፍሎች : ከዳዊት : መዝሙር : ፶፭ ፥ ፳፪ : (የመጀመሪያውን : ዓረፍተ : ነገር :) ገላትያ : ፮ ፥ ፪ ፥ እና : ፮ ፥ ፭ : ወሰደ ። ነገር : ግን : ይህ : ሰባኪ : በነዚህ : በሦስት : ጥቅሶች ፥ ሦስት : ልዩ : ልዩ : ስብከቶች : ሊያዘጋጅባቸው : በቻለ : ነበር ።

ከአገር : ወደ : አገር : እየተዘዋወሩ : ወይም : በአንድ : አጋጣሚ : ድንገተኛ : ምክንያት : ስብከት : በሚደረግበት : ጊዜ : በጣም : ጉልህ : ሆነው : ከሚታዩት : ክፍሎች : ለስብከቱ : መውሰድ : መልካም : ነው ፤ ሆኖም ፥ አንዳንድ : ጊዜ : ደግሞ : ከባድና : አስቸጋሪ : የሆነውን : ክፍል : መውሰድ : ይፈቀዳል ። ነገር : ግን : ይህንን : ከባድና : አስቸጋሪ : ክፍል : ደግሞ : ሰባኪው : ክብደቱን : በማፍታታት : ግልጽ : እንደሚያደርገው : እርግጠኛ : መሆን : አለበት ።

አንድ : ሰባኪ : ከመጽሐፍ : ቅዱስ : ክፍል : በሚሰብክበት : ጊዜ : በአድማጮቹ : ፊት : አነጋገሩና : አጠቃ[illegible] : (አመለካከቱ :) ሁሉ : ትሕትናን : የተመላ : መሆን : [illegible]ዋል ።



አንድ : የመጽሐፍ : ቅዱስ : ክፍል : ቀጥታ : ትር[illegible] : ለሚፈቅድለት : ጉዳይ : ብቻ : ሊጠቀስ : ይገባ[illegible] : እንጂ ፥ ከዚያ : ውጪ : ወይም : ልዩ : ለሆነው : ሐሳ[illegible] : ጉዳይ : ሊውል : አይገባውም ። እንደዚሁም : ክፍ[illegible] : የማይመስልና : ከክፍሉ : ጋር : ስምምነት : የሌለው : ትምህርት : ከውስጡ : ለማግኘት : መሞከር : ሙከራው : [illegible]ፈረድበታል ። ምንም : ስንኳ : ለመልካም : ሐሳብ : የተ[illegible]ጠነ : ቢሆን ፥ መጀመሪያ : ክፍሉን : ከጸፊው : ጸሐፊ : ትርጉም : ውጪ : ማዋል፡ በስብከት : ሥነ : ጥበብ : መል[illegible] : አይደለም ። አንድ : ጊዜ : አንድ : ሰባኪ : ከሉቃስ : [illegible] ፥ ፳፪ : «ከባሕሩ : ወዲያ : ማዶ : እንሻገር :» የሚለ[illegible]ን : ቃላት : ለጥቅሱ፡ ወስዶአል ። በወንጌሉ፡ አነጋገር : [illegible] : በቀላሉ : ጌታችን : ለደቀ : መዛሙርቱ : ስለ : ጉዞ[illegible]ቸው : አኳኋን : ያዘዘበት : ንግግር : ነው ። ነገር : ግን : [illegible]ኪው : ካለመታገስ : ወደ : መታገስ ፥ ከልዩ : ልዩ : ስስ[illegible]ነት : ወደ : ለጋስነት : እንሻገር : ሲል : ሰበከበት ። [illegible]ህም : የመጽሐፍ : ቅዱስን : ክፍል : ካለቦታው : ማዋል : [illegible] ፤ በተቀረስ : የዚህን : ትምህርት : በሌሎች : ክፍሎች : [illegible]ለጠ : ለማስተማር : ይቻላል ።

የመጽሐፍ : ቅዱስ : ክፍል : ከሚያስተምረው : ት[illegible]ህርት : በተቀር : በሌላ : ትምህርት : ቢተረጎሙት : [illegible]ፍሉ : ክፍል : መሆኑ : ይቀራል ።

አንዳንድ : ጊዜ : የሚሰማው : ስብከት : ከተጠቀ[illegible]ት : ክፍል : ይልቅ : ከሌላ : ክፍል : ቢጠቀስ : ኖሮ :



www.ethiopianorthodox.org

ትክክለኛ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ የተባለበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ቀደም፡
ብሎ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፤ በአጋጣሚ ፡ ለሚደረገው ፡ የን
ግግር ፡ ስብከት ፡ በተቀር ፤ ስብከት ፡ ሲባል ፡ ከመጽሐፍ፡
ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ የተወሰደ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይህም ፡ ሌላ፡
ሐሳብ ፡ ያለውን ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ሳይሆን ፡ ይህንኑ፡
ክፍል ፡ ብቻ ፡ እየተረጐመ ፡ ማብራራትና ፡ ማጐልመስ፡
ይገባል ፡ ማለት ፡ ነው ።

አንድ ፡ ስብከት ፡ ከክፍሉ ፡ ሳይርቅ ፡ የተሰበከ፡
እንደሆነ ፡ ለሰሚው ፡ ችግር ፡ ስለማይፈጥርበት ፤ ሰሚው፡
ራሱ ፡ ለነገሩ ፤ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ፡
ክፍልና ፡ ስብከቱ ፡ ተስማሚ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ አለዚያ፡
ግን ፡ አድማጮቹ ፡ ግራ ፡ ይገባቸውና ፡ ሐሳባቸው ፡ ይበ
ተናል ።

አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብ ፡ ያለው ፡ የመጽሐፍ፡
ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ለአንድ ፡ ለልዩ ፡ ጕዳይ ፡ ሊወሰድ ፡ አይገ
ባም ። ለምሳሌ ፡ «በጸጋ ፡ እደጉ ፡» (፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፤ ፲፰ ፡)
የሚለው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ትሕትና ፡ ሊሰበክበት ፡ መልካም፡
አይሆንም ። ብልህ ፡ ሰባኪ ፡ ክፍሉን ፡ በስብከቱ ፡ መደም
ደሚያ ፡ ላይ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ሊወጋ ፡ ይችላል ።

ጥሩ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ በስብከቱ፡
ውስጥ ፡ የተነገሩትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የያዘ ፡ መሆን፡
ይገባዋል ። ለምክንያት ፡ የተሰበከውን ፡ ጥቃቅን ፡ ዝርዝር፡
ሁሉ ፡ እንዲይዝ ፡ ማለት ፡ ሳይሆን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ዋና፡
ዋና ፡ ፍሬ ፡ ነገሮቹ ፡ በሙሉ ፡ መጠቀስ፡ አለባቸው፡ ማለት፡
ነው ። በስብከት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ፡



ፍል ፡ በኃይል ፡ ማስገባት ፡ ሰባኪው ፡ የዚህ ፡ ስጦታ ፡
ሌለው ፡ መሆኑን ፡ ያስገነዝባል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ አንዱን ፡
ነገር ፡ ሲደጋግም ፡ ይውላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰባ
ኪው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ባይወስድ ፡ ይሻለዋል።
ተቀረስ ፡ የተያያዘ ፡ ስብከት ፡ ሊሰማ ፡ ስለማይቻል፡በመ
ሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እውቀትና ፡ በጸጋ፡ ለማደግም፡ አይቻልም።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በአትሮኖስ ፡ ስብከት ፡ በወጣት ፡ ሰባ
ዎች ፡ የሚደረገው ፡ የተለመደ ፡ ስሕተት ፤ ከክፍላቸው ፡
ጥተው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ክፍልና ፡ ሐሳብ ፡ ሲባዝኑ ፡ መታ
ታቸው ፡ ነው ። ሰባኪው ፡ በመጀመሪያ ፡ የስብከቱ ፡ ወራ
ት ፡ ከዚህ ፡ ከተለመደው ፡ ስሕተት ፡ ለመዳን ፡ ሳይሞክ
ርና ፡ ሳይጠነቀቅበት ፡ ቢቀር ፤ ልማዱ ፡ ሥር ፡ ይተክልና ፡
መንቀልና ፡ ማረሙ ፡ ስለሚያስቸግር ፡ ስብከቱ ፡ ሁሉ ፡
ተመሳሰለ ፡ በመሆን ፡ የተለያየ ፡ መልክ ፡ ሊሰጠው ፡ አይ
ችልም ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስብከት ፡ ደብዛዛ ፡ ልብን ፡ የማ
ስጥና ፡ ደካማ ፡ ይሆናል ።

አንዳንድ ፡ ጉባኤ ፡ ስለ ፡ ሰባኪያቸው ፡ የሚያቀር
ት ፡ አቤቱታ ፡ ምንም ፡ ስንኳ ፡ በየእሑዱ ፡ ዕለት ፡ አዳ
ስ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ቢወሰድ ፤ ምናልባትም ፡
ዲስ ፡ መግቢያ ፡ ቢፈጠር ፤ ስብከቱ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡
ው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡
ብከት ፡ ብርቱ ፡ ምዕመናን ፡ ሊያዘጋጅና ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ያን ፡ ሊያስፋፋ ፡ ከቶ ፡ አይችልም ። ጥሩ ፡ ሰባኪ ፡ የሚ
ቀርባቸው፡ ስብከቶች ፡ እያንዳንዱ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ቀን
፡ ሐሳብና ፡ ትምህርት ፡ የያዘ ፡ መልእክት፡ ሲሆን፡ ነው ።
መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎች ፡ በየዓይነቱ ፡ ትምህርቶች ፡



www.ethiopianorthodox.org

የያዙ ፡ በመሆናቸው ፡ ጥሩ ፡ ሰባኪም ፡ ከክፍሉ፡ ሳይወጣ፡ በዚያው ፡ በክፍሉ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

## መስተዋድድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎች ።

ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ እየተላለፈ ፡ በተገ ኘው ፡ የሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገትና ፡ የፖለቲካ ፡ አካሄድ ፡ መለዋወጥ ፡ ምክንያት ፡ በብሉይ ፡ ዘመን ፡ የማይታወቅ ፡ ሁኔታዎችን ፡ በማበርከቱ ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ከማስነሣቱ ፡ አላቋረጠም ። ቢሆንም ፡ በማናቸውም ፡ ዘመን ፡ የሰውን ፡ ትክክለኛ ፡ ኑሮ ፡ የሚገዙት ፡ መሠረታውያን ፡ ትምህርቶች፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙ ፡ ለዚህ ፡ የሚያስ ፈልገውን ፡ ጥንታዊውን ፡ መሠረታዊ ፡ ትህምርት ፡ ከዘ መናዊው ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ በማዋሃድ ፡ ማስረዳት ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ መስተዋድድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ክፍሎች ፡ የሚጠቀሙት ። የስብሰባው፡ ምክንያት፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቢሆንም ፡ መሪው ፡ ሥርዓት ፡ በመሠረቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ተመሳሳይነት ፡ አለው ። የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ጥቅ ሶች ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ በመጠቀስ ፡ ተዋድደው ፡ ስለሚ ገኙ ፡ እንዲሁም ፡ የጌታችን ፡ የምሳሌ ፡ ትምህርቶች ፡ ይህንን ፡ ይገልጻሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰባኪው ፡ የዚህን ፡ ዓይ ነት ፡ ክፍል ፡ በሚወስድበት ፡ ጊዜ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባ ዋል ። ለስብከቱ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ክፍ ሎች ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ መስተዋድዶቹን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎች ፡ መውሰድ ፡ አያሻም ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረት ፡ ክብርና ፡ ደረጃቸው ፡ እንዲ ቀነስ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ። «ጠባቂ ፡ ሆይ ፡ ሌቱ፡



ን ፡ ያህል ፡ ነው ፡» ኢሳ ፡ ፳፩ ፡ ፲፩ ፡ የሚለው ፡ ጥቅስ ፡ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ጊዜ ፡ ምልክት ፡ ሲሰብክበት ፡ ይሰማል ። ር ፡ ግን ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሐሳብ ፡ ስለ ፡ ዝምታም ፡ ር ፡ ስለ ፡ «ዱማ ፡» አሳዛኝ ፡ ሁኔታ ፡ ብርሃን ፡ እንዲወ ት ፡ የተደረገ ፡ ጩኸት ፡ መሆኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ትም ርት ፡ ያለው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ሲወሰድም ፡ ተኛ ፡ በሆነ ፡ ግልጽ ፡ አነጋገር ፡ «ትምህርት ፡» ሆኑን ፡ ሳይደብቁ ፡ ማስረዳት ፡ ይገባል ።

አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ለስብከት ፡ ሚመረጥበት ፡ ጊዜ ፡ በዘርፉ ፡ ላይ ፡ አለመጫን ፡ ነው ። ልቁ ፡ ጥቅም ፡ የሚገኘው ፡ ከዘርፉ ፡ ጋር ፡ በማዛመድ ፡ ነውን ፡ ክፍል ፡ አስፋፍቶ ፡ በማጉላት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ኍልቊ ፡ ፴፪ ፡ ፳፫ ፡ «ኃጢአታችሁም ፡ እንድታገኛችሁ ፡ ወቁ ፡» የሚለው ፡ ክፍል ፡ ዘርፉ ፡ ሲመረመር ፡ ግልጽ ፡ ና ፡ እንደሚታይ ፡ ሰዎች ፡ የሚገባቸውን ፡ ካለማድረጋ ቸው ፡ ስለሚደርስባቸው ፡ ፍርድ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ስ ፡ ተፈጸመ ፡ አንዳንድ ፡ የሚቈጠር ፡ ኃጢአት ፡ ሳይሆን፡ ፈጸሙ ፡ ስለሚገባቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሳይፈጸሙ ፡ ስለ ሩት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በሰፊው ፡ ያመለክታል ። አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ የተሟላና ፡ እውነተኛ ፡ ትር ጉም ፡ የሚሰጠው ፡ ሊነገርበት ፡ ወይም ፡ ሊሰበክበት ፡ ተፈለገው ፡ ለዓይነተኛ ፡ አካባቢ ፡ ምክንያት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ እንዲሰጠው ፡ ነው ። ሰባኪው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅ ዱስ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ ያገኘለት ፡ ንድ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ የተቀደሰ ፡ አስተያየ ትን ፡ ማስፈር ፡ አለበት።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ አራት ።

## የስብከት ፡ መግቢያ ።

መግቢያው ፡ የአድማጮቹን ፡ ሐሳብ ፡ ለማዘጋጀት ፡ የሚደረግ ፡ ዝግጅት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ሐሳብና ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ ለማቅረብ ፡ ሰፊ ፡ ቦታ ፡ አለ ። የአድማጮቹ ፡ የአእምሮ ፡ ሁኔታና ፡ ንግግሩ ፡ የሚደረግበት ፡ ጉዳይ ፡ ግምት ፡ ሊሰጠው ፡ ያስፈልጋል ። የአድማጮቹን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ሰባኪው ፡ አትኩሮ ፡ እንዲመለከት ፡ ማድረግ ፡ ከፍተኛና ፡ ቀዳሚ ፡ ተግባር ፡ ነው ። አንድ ፡ ንግግር ፡ በሚከፈትበት ፡ ጊዜ ፡ አድማጮቹ ፡ ለመስማት ፡ በታላቅ ፡ ጉጉት ፡ የሚጠባበቁት ፡ አንድ ፡ ፍላጎት ፡ አለ ። ጥሩው ፡ ሰባኪ ፡ የዚህን ፡ ፍላጎት ፡ መዋያ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ እንደምን ፡ እንደሚያሰፍረው ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቃል ።

የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ክፍል ፡ ለመግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ በመግቢያው ፡ የንግግር ፡ ጊዜ ፡ እንደሚተቹ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ንግግሮች ፡ መዘባዘብ ፡ አያስፈልግም ። መግቢያው፡ የተጣራና ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይህ ፡ አገላለጽ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱሱን ፡ ክፍል ፡ እውነተኛ ፡ ትርጉም ፡ የያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ። የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ የስብከትን ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ተመርኵዞ ፡ በስሕተተኛ ፡ ትር



www.ethiopianorthodox.org

ጕም ፡ መመራቱ ፡ ቢሰማህ ፡ ከቶ ፡ አትከተለው ። ትምህ
ርት ፡ ከሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በምትገኝበት ፡ ጊዜ ፡
ስለ ፡ ትርጕም ፡ ጕዳይ ፡ በሚገጥምህ ፡ ክርክር ፡ ሕሊናህን ፡
በማጋጨት ፡ አታባክነው ። የራስህ ፡ ትርጕም ፡ ዋጋ ፡ የሌ
ለው ፤ የማይታመን ፡ እንዳይመስልብህ ፡ ለሌሎቹ ፡ መን
ገድ ፡ አትክፈትላቸው ። የመግቢያው ፡ መግለጫ ፡ በተ
ቻለ ፡ መጠን ፡ ሙሉውን ፡ ትርጕም ፡ ሊይዝ ፡ ይገባል ።
አንድ ፡ ተማሪ ፡ በፈተና ፡ እንዳይወድቅና ፡ ብልጫ ፡ ለማ
ግኘት ፡ በመጣጣር ፡ ለራሱ ፡ የሚያደርገውን ፡ ያህል ፡
አንድ ፡ ሰባኪም ፡ ለጉባኤው ፡ እንደዚሁ ፡ ማድረግ ፡ ይገ
ባዋል ፤ ሆኖም ፡ ከሚገባው ፡ ሙሉ ፡ ትርጕም ፡ በላይ ፡
ደግሞ ፡ መጨመር ፡ አይገባውም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አን
ዳንድ ፡ ሰባኪዎች ፡ የጌታችን ፡ ምሳሌ ፡ ከሚያስረዳው ፡
ይልቅ ፡ የሚጨማምሩበት ፡ አሉ ። አንድ ፡ ሰባኪ ፡ ስለ ፡
«ደጉ ፡ ሳምራዊ ፡» በሰበከበት ፡ ጊዜ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊያ
ውን ፡ ወይም ፡ በዘመኑ ፡ አነጋገር ፡ ሆቴል ፡ የተባለውን ፡
«የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡» ምሳሌ ፡ አድርጎታል ። ሁለቱ ፡ ቤሳ
ዎች ፡ ደግሞ ፡ በሁለቱ ፡ የክርስቲያን ፡ ሥርዓቶች ፡ ማለት ፡
«በጥምቀትና ፡ በቅዱስ ፡ ቍርባን ፡» ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ በነ
ዚህ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል ፡ ብሎአል ።
እንደዚህ ፡ ይመስላችኋልን ? አይደለም ።

በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በቦታ ፡ በቦታቸው ፡ የሚስ
ማሙና ፡ ሥርዓታዊ ፡ አቀራረብ ፡ ያላቸው ፡ ከፍተኛ ፡
ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ የያዙ ፡ ትምህርቶች ፡ ተትረፍርፈውበታል ።
ስለዚህ ፡ ትምህርቶቹን ፡ ማቀላቀልና ፡ ያለቦታቸው ፡ ማግ
ባት ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡



ነገረው ፡ ሰባኪው ፡ በሚሰብክበት ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡
ፍል ፡ ላይ ፡ ባይወሰን ፡ ከሌላ ፡ ክፍል ፡ በማቀላቀል ፡ መስ
፡ ግድ ፡ ሊሆንበት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ስብከቱን ፡
ሚያደጋግም ፡ ወጽመድ ፡ ይሆንበታል ።

የጠራና ፡ (ጥሩ ፡ የሆነ ፡) ትክክለኛ ፡ አንደበት ፡
ስፈላጊ ፡ ነው ። ለተዘበራረቀ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ይቅርታ ፡
ይደረግለትም ። የስብከት ፡ አገላለጽ ፡ የሞቀና ፡ የደስ ፡
ስ ፡ ያለው ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ስልቹና ፡ ረጅም ፡ መሆን ፡
፡ የለበትም ። ግዴታ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ የቴክኒክና ፡
ይዘወተሩ ፡ ከፍተኛ ፡ ቃላቶች ፡ በስብከት ፡ ውስጥ ፡
ስገባት ፡ አያስፈልግም ። አድማጮቹ ፡ ከየዓረፍተ ፡ ነገሩ ፡
ንዳንድ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ትርጕም ፡ የሚያገኙበት ፡
ሆናቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለብህ ።

እንደ ፡ ሥርዓቱ ፡ በስብከት ፡ መካከል ፡ የሚያስቅ ፡
ገር ፡ ሊደረግ ፡ አይገባም ። የወንጌልን ፡ ስብከት ፡ ክብር ፡
፡ የሚያደርግ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ በም
፡ አይረዳም ።

## <u>የመግቢያ ፡ ዓይነተኛ ፡ ነገሮች ።</u>

### ሀ) <u>የአድማጮቹን ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ መማረክ ፤</u>

ህ ፡ ጊዜ ፡ የሰባኪው ፡ የታረመ ፡ ሰውነትና ፡ የአድማጮ
ንም ፡ ፍላጎት ፡ ማስተዋል ፡ ዓይነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። በሰ
ኪውና ፡ በአድማጮቹ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡
ነ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ መገናኛና ፡ ማሰሪያ ፡ እንዲ
ር ፡ ማድረግ ፡ የሰባኪው ፡ ተግባር ፡ ነው ። ከሁሉ ፡ በላ



www.ethiopianorthodox.org

ይም ፡ ሰባኪው ፡ ለአድማጮቹ ፡ ታላቅ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሊያደርግላቸው ፡ እንደሚፈልግ ፡ የሚያሳየው ፡ ፈቃደኝነት ፡ ነው ።

ለ) የአድማጮቹን ፡ ሐሳብ ፡ ማንቃት ፤ የወንጌሉ ፡ መልእክተኛ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ በአንድ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ብቻ ፡ የሚሰብክ ፡ ሲሆን ፥ አድማጮቹ ፡ ይሰለቹታል ፥ ደግሞም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ንግግር ፡ እንዳይደገም ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልገዋል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፥ ጥሩ ፡ መግቢያ ፡ የአድማጮቹን ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍላጎት ፡ እንዲማርክ ፡ ያስፈልጋል ። የስብከት ፡ የመጀመሪያውና ፡ የመጨረሻው ፡ ዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡ በአድማጮች ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ ተናፋቂዎች ፡ ናቸው ። የስብከቱን ፡ መግቢያ ፡ ጉባኤው ፡ ይበልጥ ፡ ለመስማት ፡ እንዲጓጉ ፡ አድርጎ ፡ ማቅረብ ፡ ያስፈልጋል ።

ሐ) <u>ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ እንዲሰሙት ፡ ማድረግ</u> ፤ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ በደህና ፡ የማይቀበሉት ፡ ሲሆን ፡ ሰባኪው ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ መንገዱን ፡ ማስተካከል ፡ አለበት ። ቈይተህ ፡ ብትተወው ፡ ስንኳ ፡ ሁልጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ በተለመደ ፡ ነገር ፡ መጀመር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ በማርስ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ (የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፲፯ ፡) በግሪክ ፡ አገር ፡ ያደረገውን ፡ ስብከት ፡ መመልከት ፡ ይበጃል ፡ አድማጮቹ ፡ ከሚያውቋቸው ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ በስብከት ፡ ውስጥ ፡ ማውሳት ፡ ጥሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ። ደግሞም ፡ አንዳንድ ፡ ምሳሌ ፡ ማግባት ፡ ጠቃሚ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ። በሚሰበክበት ፡ ክፍለ ፡ ሐገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡



ጥቃቅን ፡ ብጥብጥ ፡ ቢነሣ ፡ ስንኳ ፤ ይልቁንም ፡ ክርስትና ፡ [illegible]ላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ በዘዴ ፡ ማሸነፍ ፡ ይገባል ። ይህም ፡ ሊከናወን ፡ የሚችለው ፡ በባሕርይና ፡ በተግባርም ፡ ነው ። የወዳጅነትን ፡ መንገድ ፡ በማዳ[illegible]ር ፡ መቅረብ ፡ ነው ። የንግግር ፡ ዘዴ ፡ ማወቅ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ፤ ፍቅር ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነው ።

## <u>በመግቢያ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረጉ ፡ ባሕሪዮች ፡</u>

ሀ) <u>ግልጽነት</u> ፤ በመግቢያው፡ ጊዜ፡ የሚነገርለትን፡ ጉዳይ ፤ ሰዎቹ ፡ በቀላሉ ፡ ሊያስተውሉት ፡ ካልቻሉ ፥ ስለ ፡ ነገረው ፡ ጥንቃቄ ፡ አያደርጉም ። ግልጽ ፡ መሆን ፡ ጠንካራና ፡ መልካም ፡ ሐሳብን ፡ አያስወግድም ። በመግቢያ ፡ ጊዜ ፡ ረጅም ፡ ክርክር ፡ ማቅረብ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ። የማይገባ ፡ ስሜትና ፡ ወቀሣ ፡ ማብዛትም ፡ ከክፍሉ ፡ ውጭ ፡ ነው ። ምክርን ፡ ያዘለ ፡ ወቀሣንም ፥ የቀረው ፡ ሐሳብ ፡ ሁሉ ፡ ተነግሮ ፡ እስኪሰበሰብ ፡ ድረስ ፡ ማቆየት ፡ ይገባል ።

ለ) <u>አንድነት</u> ፤ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለአንድ ፡ ዓላማ ፡ መገዛት ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ ጉዳዩን ፡ በመግቢያ ፡ መግለጽ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሰባኪው ፡ ዓይነተኛና ፡ የመጀመሪያ ፡ ጥያቄ ፡ «ጉዳዩ ፡ ምንድር ፡ ነው ? እንዴትስ ፡ ነው ፡ የማቀርበው ?» የሚል ፡ ነው ። እንደ ፡ ልማድ ፡ መግቢያው ፡ ረጅም ፡ መሆን ፡ የለበትም ። ወይም ፡ መግለጫው ፡ ማለት ፡ ከዋናው ፡ ስብከት ፡ የበለጠ ፡ ንግግር ፡ ያለበት ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። ያለዚያስ ፡ የቀረው ፡ ስብከት ፡ ለዛ ፡ ያጣና ፡ ደብዛዛ ፡ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

ሐ) <u>ትሕትና</u> ፤ የራስን ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛ
ነት ፡ ሥልጣን ፡ በብዙ ፡ ማስረጃ ፡ መግለጽ ፡ አይገባም ።
ወይም ፡ ሃይማኖተኛ ፡ በመምሰል ፡ ራስን ፡ ለትምክህት ፡
ማቅረብ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ። ሁልጊዜ ፡ ጉባኤውን ፡ማክ
በር ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ በሰባኪዎቹ ፡ ላይ ፡ አተኵሮ ፡ መስ
በክ ፡ አይገባም ። «እኔ ፡» የሚለው ፡ የስም ፡ ምትክ ፡ ብዙ ፡
ጊዜ ፡ ሊደጋገም ፡ አይገባም ። ላላመኑ ፡ ካልሆነ ፡ በተቀር ፡
«እናንተ ፡» እያሉ ፡ ከመስበክ ፡ ይልቅ ፡ «እኛ ፡» ማለት ፡
በጣም ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ራስህን ፡ አስገልለህ ፡ ሌሎችን ፡
ብቻ ፡ ለማስተማር ፡ ስጦታ ፡ ያለህ ፡ አትምሰል ። የበላይ
ነትን ፡ አትነካካ ፤ ይልቁንም ፡ የትሕትናን ፡ ሁኔታ ፡ ብታ
ሳይ ፡ የትዕቢትን ፡ መንፈስ ፡ ከብዙዎች ፡ ታስወግዳለህ ።

መ) እንዲያስቡ ፡ ማድረግ ፤ በስብከት ፡ መጀመሪያ ፡
የሰዎቹ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲሰበሰብና ፡ እንዲያስቡ ፡ ማድረግ ፡
በጣም ፡ ይጠቅማል ። መግቢያው ፡ በምሳሌ ፡ ዓይነት ፡ ተዘ
ርዝሮ ፡ ሲገለጥ ፡ ለማስተዋል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታን ፡ ያስገ
ኛል ። ጥሩ ፡ አገላለጽ ፡ እውነትን ፡ በስዕል ፡ እንደማቅረብ ፡
ያህል ፡ ይቈጠራል ። ያለፉትን ፡ የጊዜ ፡ ሁኔታዎች ፡ በሚ
ገባ ፡ ማቅረብም ፡ ለጥቅም ፡ ይውላል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በ
ዚያኑ ፡ ጊዜያት ፡ ስለሚፈጸመው ፡ አጋጣሚ ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡
ንግግር ፡ በማድረግ ፡ መግቢያውን ፡ ቢከፍቱት ፡ መልካም ፡
ነው ። እንዲሁም ፡ ሐሳብን ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ጥያቄ ፡ በመግቢ
ያው ፡ ጊዜ ፡ ማቅረብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ሰባ
ኪው ፡ ከስብከቱ ፡ መሐል ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡
እንዳለበት ፡ መዘንጋት ፡ የለበትም ።



<u>ለመግቢያ ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምሳሌዎች ።</u>

፩ ፡ ገላጭ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደታተተው ።

፪ ፡ መስተዋድድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ክፍል ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ ማዋሐድ ።

፫ ፡ ከሌሎች ፡ ቅዱሳን ፡ ጽሑፎች ፡ ጋር ፡ ማመዛዘን ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ የተወሰደውን ፡ ክፍል ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያጐላል ፡ (ያደምቃል ።)

፬ ፡ በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ መግለጽ ፡ ይህ ፡ አስፋፍቶ ፡ ለመነጋገርም ፡ መንገድ ፡ ይከፍታል ።

፭ ፡ የተግባር ፡ ታሪክ ፡ ይኸውም ፡ የመጽሐፍ፡ ቅዱሱ፡ ክፍል ፡ መጀመሪያ ፡ የተሰበከበትን ፡ ታሪክና ፡ ምክንያት ፡ መግለጽ ።

፮ ፡ በጉዳዩ ፡ ችልታ ፡ እንዳይገባ ፡ አደራ ፡ ማለት ፡ ለምሳሌ ፡ የትምህርቱን ፡ ዓላማና ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በቀጥታ ፡ ማረጋገጥ ። ከዝቅተኞች ፡ ንግግሮች ፡ ጋር ፡ ማመዛዘን ። ከከፍተኛ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋር ፡ ማመዛዘን ።

፯ ፡ አስቀድሞ ፡ ከተሰበከው ፡ ጋር ፡ ማገናኘት ፡ ይህ ፡ የሚጠቅመው ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ በሚሰበክበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፰ ፡ ከተያዘው ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ የሚስማማውን ፡ ሌላ ፡ ጥቅስ ፡ መርጦ ፡ በጥብቅ ፡ ማስረዳት ። ነገር ፡ ግን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ በዚሁ፡
አለመዝለቅ ፡ ነው ።

፱ ፡ የተመረጠው ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ሰባኪው ፡ ሐሳብ ፡
እንደምን ፡ እንደመጣለት ፡ መተረክ ፡ አንዳንድ ፡
ጊዜ ፡ ይጠቅማል ።

፲ ፡ ስለሚነጋገሩበት ፡ ዓላማ ፡ ባጭሩ ፡ ዝርዝር ፡ መስ
ጠትና ፡ ሰባኪውም ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለመስበክ ፡
ያሰበበትን ፡ ዓይነተኛ ፡ ምክንያት ፡ ማስረዳት ።

ይህ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ተሰጠ ፡ እንጂ ፡ በብዙ ፡
ዓይነት ፡ መንገድ ፡ መግቢያውን ፡ ለመክፈት ፡ ይቻላል ፡

## መግቢያውን ፡ ስለ ፡ ማጠቃለል ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የስብከት ፡ ዋናው ፡ አስቸጋሪ ፡ ክፍል ፡
መግቢያው ፡ ነው ። ቃሉን ፡ በማውጣጣት ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ
ና ፡ ብልህነት ፡ ያስፈልጋል ። ደካማ ፡ ወይም ፡ የደስ ፡ ደስ ፡
የሌለው ፡ መግቢያ ፡ ስብከቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ከሚጎትቱት ፡
ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ ሊጠበቅ ፡
የሚገባው ፤ ሰባኪው ፡ በሚሰብክበት ፡ ዓላማና ፡ በክፍሉ
አቅዋም ፡ ሐሳቡን ፡ የጠራ ፡ ማድረግና ፡ ቀጥሎም ፡ መግቢ
ያውን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ዓላማዎ
ች ፡ መግቢያ ፡ አያስፈልጋቸው ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ አንዳ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ይደርስ ፡ ይሆናል ።

መግቢያው ፡ ለሰዓቱ ፡ የሚደረገውን ፡ ስብከት ፡ በ
ሙሉ ፡ በአጭር ፡ አነጋገር ፡ አነጣጥሮ ፡ ያጠቃለለ ፡ መሆን ፡
አለበት ። ስለዚህም ፡ የስብከቱን ፡ ማስታወሻ ፡ አስቀድሞ ፡



ጋጀት ፡ ያስፈልጋል ። ስለ ፡ ስብከት ፡ ክፍሎች ፡ በሚከ
ው ፡ ምዕራፍ ፡ እንነጋገርበታለን ። በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡
ን ፡ ክፍሎቹ ፡ ማለት ፡ የስብከቱ ፡ ዋና ፡ ሐሳቦች ፡ አስቀ
ም ፡ መወሰን ፡ እንደሚያስፈልግና ፡ ሰባኪውም ፡ በዚህ ፡
ሶቶ ፡ የሚጓዝበትን፡ መሠረታዊ ፡ መንገድ ፡ ሲያውቅ ፡
ብከቱን ፡ መግቢያ ፡ ለመጀመር ፡ ችሎታ ፡ የሚያገኝ ፡
ኑን ፡ ብቻ ፡ ማስረዳት ፡ ይበቃል ።

አስቀድሞ ፡ የስብከቱን ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ (ወይም ፡
ስ ፡ ክፍሎች ፡ ቢኖሩ ፡) ማዘጋጀትና ፡ ቀጥሎ ፡ መግቢያ
ን ፡ ማሰናዳት ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ሁልጊዜ ፡ አስ
ጊ ፡ አይሁን ፡ እንጂ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የስብከቱን ፡
ሎች ፡ በመግቢያው ፡ ጊዜ ፡ ማውሳት ፡ ይጠቅማል ።
ጨረሻም ፡ ሥራው ፡ በመልካም ፡ ቅንዓትና ፡ ስሜት ፡
ረግ ፡ ይገባል ። አድማጮቹ ፡ የሰባኪው ፡ ልብና ፡ መን
ስ ፡ በሙሉ ፡ በስብከቱ ፡ ላይ ፡ እንዳረፈና ፡ ስብከቱም ፡
ርሱ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው፡ ሆኖ፡ እንደሚሰማው፡
ት ፡ አለባቸው ። አንድ ፡ መግቢያ ፡ ለዋናው ፡ ስብከት ፡
ንደ ፡ ትንቢት ፡ ሆኖ ፡ በቀዳሚነት ፡ ተስፋን ፡ የሚሰጥ ፡
ብራት ፡ ነው ።

## የስብከት ፡ አርእስት ።

የንግግሩን ፡ አርእስተ ፡ ነገር ፡ በመግቢያ ፡ ጊዜ ፡
ንገር ፡ ያሻል ። አንድ ፡ አርእስት ፡ ማዘጋጀት ፡ ታላቅ ፡
ቅም ፡ ያለው ፡ ነው ። እንደሚከተለውም ፡ ለማመልከት ፡
ቻላል ።



www.ethiopianorthodox.org

፭ ፣ <u>በንግግሩ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገውን ፡ አመዳደብ ፡ የተስተካከለ ፡ መሆኑን ፡ ያጋግጣረል</u> ፤ ሰባኪው ፡ ስብከቱን ፡ በሚያዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ «ከምሰብክበት ፡ ጉዳይ ፡ ተጠግቻለሁ ፡ ወይም ፡ አልራቅኩም ፡» እያለ ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ ራሱን ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

፮ ፣ አንድነትን ፡ ያደራጃል ፤ በአንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ለሚደረግ ፡ የአርእስት ፡ ምርጫ ፡ ጥራትንና ፡ የንግግርን ፡ አወሳሰን ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳል ። አርእስቱን ፡ ማለት ፡ የስብከቱን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ ወዲያው ፡ ማስታወቅ ፡ ነው ። ሙሉ ፡ ስብከቱም ፡ የአርእስቱ ፡ ወይም ፡ የመሠረተ ፡ ሐሳቡ ፡ መግለጫ ፡ እንዲሆን ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

፯ ፣ <u>ነገሩን ፡ ያጠብቃል</u> ፤ የተወሰኑ ፡ አርእስተ ፡ ሐሳቦች ፡ የበለጡ ፡ ናቸው ። በከፍተኞች ፡ ትምህርቶች ፡ መስበክ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንድ ፡ ስብከት ፡ ውስጥ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ አትሞክር ። አርእስተ ፡ ሐሳቡ ፡ በጥንቃቄና ፡ በጠራ ፡ አነጋገር ፡ በተቻለም ፡ መጠን ፡ ባጭሩ ፡ ሊገለጽ ፡ ይገባል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተባለው ፤ ሰባኪ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የስብከት ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ መያዝ ፡ ይገባዋል ። በዚህ ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተርም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ክፍሎችና ፡ ስለዚሁም ፡ የሚያስታውሳቸውን ፡ ከመያዙ ፡ ሌላ ፣ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የሰበካቸውንም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ዝርዝር ፡ መያዝ ፡ ይገባዋል ። ማስታወሻውን ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ ያየው ፡ እንደሆነ ፡ እጥልቅ ፡ ፈር ፡ ውስጥ ፡ ከመግባት ፡ ይድናል ። ስለ ፡ እውነትም ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ለዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ በሚያስፈልገው ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ለመናገር ፡ ይችላል ።



አንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሰባኪዎች ፡ ስለ ፡ ስብከት ፡ አርእስተ ፡ ሐሳብ ፡ የተነጋገሩባቸውን ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ እንጠቅሳለን ።

«የክርስቲያን ፡ ወዳጅነት ፡» ሚልክ ፡ ፫ ፣ ፲፮ ፡ ጌታን ፡ የሚፈሩት ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ።

«የኀዘን ፡ ኃይል ፡» ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፣ ፱ ፡ ፲ ።

«የሰው ፡ ትልቅነትና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትልቅነት ፡» ኢሳ ፡ ፶፯ ፣ ፲፭ ፡ ይህንን ፡ ልዑል ፡ ይላልና ፡ ታላቁም ፡ ከዘለዓለም ፡ ጀምሮ ፡ የነበረ ፡ ስሙ ፡ የተቀደሰ ፡ በከፍታና ፡ በመቅደስ ፡ እቀመጣለሁ ፡ ከተቀጠቀጠም ፡ ከተዋረደ ፡ መንፈስ ፡ ጋር ።

«የሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡» ማርቆስ ፡ ፫ ፣ ፳፩ ፡ ወገኖቹም ፡ ሰምተው ፡ ሊይዙት ፡ ወጡ ። ምናልባት ፡ ልቡ ፡ ዘነጋ ፡ ብለው ፡ ነበሩና ።

«የሕይወት ፡ መስማማት ፡ ወይም ፡ መመዛዘን ፡» ራእይ ፡ ፳፩ ፣ ፲፮ ፡ ከተማይቱም ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ናት ፡ ርዝመቷም ፡ በስፋቷ ፡ ልክ ፡ ነው ።

«የተገለጸ ፡ ፍላጎት ፡ ያልተነገረ ፡ ጥያቄ ፡» ዮሐ ፡ ፪ ፣ ፫ ፡ የኢየሱስም ፡ እናት ፡ አለችው ፣ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የላቸውም ፡ ዮሐ ፡ ፲፩ ፣ ፫ ፡ እኅቶቹም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ላኩ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፣ የምትወደው ፡ ታሞአል ።



www.ethiopianorthodox.org

«የክርስቶስ ፡ ስጦታ ፡ ለእኛ ፤ የእኛ ፡ ስጦታ ፡ ለእ
ርሱ ፡» ቲቶ ፡ ፪ ፤ ፲፬ ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የለወጠ ፡ ከኃጢ
አት ፡ ሁሉ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ለራሱም ፡ የተመረጠ ፡ ወገን ፡
ያነፃ ፡ ዘንድ ፡ ለመልካም ፡ ነገር ፡ የሚቀና ።

«ያልተፈጸሙ ፡ ሐሳቦች ፡» ፩ ፡ ነገሥት ፡ ፳ ፤ ፲፯-፲፰፡

«የተቀበሉ ፡ ጣዖቶች ፡» ዘፍ ፡ ፴፭ ፤ ፬ ፡ እንግዶቹ
ንም ፡ አማልክት ፡ (ጣዖቶች ፡) ሁሉ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሰጡት ፡
በእጃቸው ፡ የነበሩትን ፡ በጆሮዋቸውም ፡ የነበሩትን ፡ ጕት
ቾች ። ያዕቆብም ፡ በሴኬም ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ዛፍ ፡ በ
ታች ፡ ቀበራቸው ።

«የሕይወት ፡ ሀብቶች ፡» በመዝ ፡ ዘዳዊት ፡ ፸፫ ፡
፳ ፡ ዕዋዬም ፡ የተረፈ ፡ ነው ።

«የርኅራኄ ፡ አለመሰሰት ፡ » ሉቃ ፡ ፮ ፤ ፴፭ ፡ መጽ
ውቱ ፡ አበድሩም ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ ሳታደርጉ ።

«የወንጌል ፡ መልእክተኛው ፡ መሣሪያ ፡» ፪ ፡ ቆሮ ፡
፬ ፤ ፪ ፡ እውነቱን ፡ በመግለጽ ፡ ራሳችንን ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ሕ
ሊና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንገልጻለን ።

«ነፃነትና ፡ ግዴታ ፡» ሉቃ ፡ ፪ ፤ ፵፱ ፡ በአባቴ ፡
ቤት ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባኝ ፡ አላወቃችሁምን ?

«ለጌታ ፡ የሚሆን ፡ የፍቅር ፡ ስጦታ ፡» ዮሐ ፡ ፲፪ ፡
፫ ፡ ማርያምም ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ የጥሩ ፡ ናርዶስ ፡
ሽቱ ፡ ንጥር ፡ ወስዳ ፡ የኢየሱስን ፡ እግር ፡ ቀባች ፤ በጠጕር
ዋም ፡ እግሩን ፡ አበሰች ፤ ቤቱም ፡ ከናርዶስ ፡ ሽቱ ፡ ሞላ ።



ምዕራፍ ፡ አምስት ።

# ክፍለ ፡ መደቦች ።

ስብከትን ፡ በመደብ ፡ በመደቡ ፡ መከፋፈል ፡ በ
[illegible] ፡ አሮጌ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ነው ። አከፋፈሉ ፡ ግን ፡ ብዙ
[illegible] ፡ በተሳሳተ ፡ መንገድ ፡ ሲደረግ ፡ ኑሯል ። ሆኖም ፤ በት
[illegible] ፡ የተዘጋጀ ፡ እንደሆነ ፤ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ እጅግ ፡
[illegible] ፡ ያለ ፡ ነው ። የአንዱን ፡ ስብከት ፡ በመደብ ፡ በመደቡ ፡
[illegible]ፋፈል ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ በሚከተለው ፡ ለማስረ
[illegible] ፡ ይቻላል ። ይኸውም ፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡ ተብሎአል ።

፩ ፤ አንድ ፡ ስብከት ፡ በየመደቡ ፡ የተከፋፈለ ፡ እን
[illegible]ን ፡ የንግግሩን ፡ ጥራት ፡ ያበረክታል ፤ የክፍለ ፡ መደብ ፡
[illegible] ፡ ጥቅም ፡ ለስብከቱ ፡ የሚሆኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ በመመ
[illegible]ርና ፡ በማበጠር ፡ ነው ። አንድ ፡ ስብከት ፡ በሁለት ፡ ወ
[illegible] ፡ በሦስት ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ ተጣርቶ ፡ የተጠቃለለ ፡
[illegible]ሆነ ፤ በቀላሉ ፡ ለማስተዋልና ፡ ለማስታወስም ፡ ይቻ
[illegible] ፡ ስለዚህ ፡ የጥሩ ፡ ሰባኪ ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ የሚሰ
[illegible]ትን ፡ ጉዳይ ፤ መሐከለኛ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡
[illegible]ሉ ፡ ሊያስተውለውና ፡ ሊያስታውሰው ፡ እንደሚችል ፡
[illegible]ርጎ ፡ በመመደብ ፡ ሲያቀርብ ፡ ነው ።

፪ ፤ ንግግሩን ፡ ለማስተዋል ፡ ይረዳል ፤ ሰባኪውን ፡
[illegible]ን ፡ የስብከቱን ፡ ጉዳዮች ፡ ወይም ፡ መሣሪያዎች ፡ ለመ



www.ethiopianorthodox.org

ሰብሰብና ፡ ለማደላደል ፡ ይረዳዋል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡
በንግግሩ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ እንዳያዘነብል ፡
ይከለክለዋል ። አድማጩንም ፡ የንግግሩን ፡ ተስተዋይነት ፡
አተኵሮ ፡ እንዲመለከተውና ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ እንዲሰ
ጠው ፡ ይረዳዋል ።

፫ ፡ የንግግሩን ፡ አንድነት ፡ ወይም ፡ መሰብሰብ ፡ ያሳያል ፤ ነገሮችን ፡ በክፍል ፡ በክፍላቸው ፡ ለመመደብ ፡
መደ ከም ፡ የሚያሻው ፡ በውጤቱ ፡ ላይ ፡ የማያስፈልገውን ፡
ትቶ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ሰብስቦ ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡
አድማጩ ፡ የስብከቱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ከሌላው ፡ ክፍል ፡
ጋር ፡ ሲገጣጠም ፡ ማየቱ ፡ ዋና ፡ ጕዳዩ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡
ክፍለ ፡ መደብም ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱሱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ሊ
ደረግ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡ ምንጭ ፡ ሊሆን ፡ ከቶ ፡
አይገባም ።

፬ ፡ በንግግሩ ፡ ጊዜ፡ እርምጃን ፡ ይሰጣል ፤ ሰባኪው
በሚዘጋጅበትና ፡ አድማጮቹ ፡ ስብከቱን ፡ በአንክሮ ፡
ሚከታተሉበት ፡ ጊዜ ፡ እርምጃን ፡ ይሰጣል ። እያንዳንዱ ፡
ልዩ ፡ ክፍለ ፡ መደብ ፡ ቀዳሚውን ፡ መከተል ፡ አለበት ፡
የስብከቱን ፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ እያሉ ፡ መቁ
ጠር ፡ አያስፈልግም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕጋዊው ፡ ተከታታይ
ታቸው ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

፭ ፡ የንግግሩን ፡ ትክክለኛነት ፡ ያስረዳል ፤ ስብከቱ
የተጣራ፡ ነዋሪ ፡ እትም ፡ እንዲተው ፡ ሲፈለግ ፤ የጠነከረ
ንግግር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በአትሮኖስ ፡ ላይ ፡ ሲሰበክ
እጥር ፡ ያለ ፡ እንዲሆን ፡ በየጊዜው ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ



ነው ። ስለዚህም ፡ የንግግሩ ፡ አቀራረብ ፡ አጫጭር ፡ ሆኖ ፡
ጥነት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ በብዙ ፡ ይረዳል ።

በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የስብከቱን ፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡
ገቢያው ፡ ቀጥሎ ፡ ማስታወቅ ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ነው ፡
ራቸውም ፡ በስብከቱ፡ መጠን ፡ ሊሆኑ ፡ ይገባል ። ለም
፡ ለምክር ፡ ተብሎ ፡ በሚደረግ ፡ ስብከት ፡ ከሚደረገው ፡
ፈል ፡ ይልቅ ፡ በክርክር ፡ ስብከት ፡ በሚደረገው ፡
ፈል ፡ የበለጠ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያስፈልገዋል ። ክፍሎቹ ፡
ንም ፡ በወጣቶችና ፡ ባልተማሩ ፡ አድማጮች ፡ ስብ
፡ ጊዜ ፡ በተቻለ ፡ መጠን፡ ጥቂቶች፡ ቢሆኑ፡ ሰባኪውን ፡
ባዘን ፡ ያድነዋል ። ቶሎ ፡ ለማስተዋልና ፡ በፍጥነት ፡
ስታወሳቸው ፡ የሚቻሉ ፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡ ከሁሉ ፡ የበ
፡ ናቸውም ፡ ተብሏል ።

ለምሳሌ ፡ ሉቃስ ፡ ፭ ፡ ፬ ፡ ስምዖንን ፡ ወደ ፡ ጥልቁ ፡
፡ በል ፡ መረቦቻችሁንም ፡ ለማጥመድ ፡ ጣሉ ፡ አ
፡ (ታሪኩን ፡ በሙሉ ፡ አንብብ ፡ ፩ ፡) ፈቀቅ ፡ በል ፤
ጣሉ ፤ ፫ ) ሁሉን ፡ ትተው ፡ እነዚህ ፡ ቀላሎች ፡ ነገር ፡
፡ ሊስተዋሉ ፡ የሚችሉ ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው ።

ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ፡ ብርሃን ፡ ሳለላችሁ ፡ በብርሃን ፡ እ
፡ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ። እዚህ ፡ ላይ ፤ ፩ )
ችን ፤ ፪ ) ተግባራችን ፤ ፫ ) መድረሻችን ፡ ወይም ፡ ፍ
ያችን ፤ እነዚህ ፡ ጥሩ ፡ መደቦች ፡ ናቸው ።

አስቴር ፡ ፭ ፡ ፲፫ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ለእኔ ፡ ምንም ፡
ጠቅመኝም ፡ በንጉሡ ፡ ደጅ ፡ አይሁዳዊው ፡ መርዶክ
፡ ተቀምጦ ፡ ባየሁት ፡ ጊዜ ።



www.ethiopianorthodox.org

ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ «ውስጣዊ ፡ ዕረፍት ፡ ወይም ፡ ሰ
ላም ፡ ማጣት ።»

፩ ፡ ግዳማዊው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ውስጣዊውን ፡ ፍላ
ጎት ፡ እንደማይሞላ ፤

፪ ፡ ውስጣዊው ፡ ክፋት ፡ ማናቸውንም ፡ ግዳማዊውን
መልካም ፡ ነገር ፡ ሊያበላሽ ፡ እንደሚችል ።

፫ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ በረከት ፡ የተቀደሰ ፡ ባሕርይ
ነው ። ምንም ፡ ስንኳ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ቢሆን ፡ ከመጽሐፍ
ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያልተገኘ ፡ የክፍል ፡ መደብ ፡ ከቶ
አለማድረግ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፤ ነገር ፡ ግን
አስፈላጊነቱ ፡ በማይዘለል ፡ ሥርዓት ፡ የሚደርሰው ፡ ያለ
ጠንቀቅ ፡ መጨረሻ ፡ የሚመራው ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ወ
ተደጋገመና ፡ አዲስነት ፡ ወደሌለው ፡ ደብዛዛና ፡ ስልቹ ፡
ደ ፡ ሆነ ፡ ስብከት ፡ ስለሆነ ፡ በስብከት ፡ ጥበብ ፡ ከሚገኙት
ስህተቶች ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የለም ። በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ስ
ከት ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ወንጌል ፡ ተነጋግሬበት
እዘልቃለሁ ፡ ብለህ ፡ አትሞክር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከወንጌሉ
ውስጥ ፡ በተወሰደው ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ራስህን ፡ መወሰን
ነው ።

መደቦቹ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱሱ
ክፍል ፡ በሚያስተምረው ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፤ ክፍሎቹም
ከዚያው ፡ ያልወጡና ፡ የተመሳሰሉም ፡ መሆን ፡ ይገባ
ዋል ። ለምሳሌ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ መደብ ፡ ሐተታን ፡ ቀጥሎ
ያለው ፡ ጥያቄ ፤ ወይንም ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ መደብ ፡ ዓቢይ
አንቀጽን ፤ ሌላው ፡ ሙሉ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገርን ፡ የያዘ ፡ ለ



ን ፡ ትክክለኛ ፡ አመዳደብ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።
ኪው ፡ ክፍለ ፡ መደቦቹን ፡ በሚያዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ የአ
ሎቹን ፡ ሐሳብ ፡ የሚደግፍበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡
በት ። በዓቢይ ፡ አንቀጽ ፡ ወይም ፡ በዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡
ጋጁ ፡ መደቦች ፡ ሁልጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ለማስታወስ ፡
ዎች ፡ ናቸው ። ሰባኪው ፡ የክፍለ ፡ መደቦቹን ፡ ቃላት ፡
ያውጣጣበት ፡ ጊዜ ፡ ለእሱ ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ እስኪታየ
ና ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ለመጨመር ፡ እንደማይችል ፡ እስኪ
ው ፡ ድረስ ፡ ሳይሰለች ፡ ጊዜውን ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡
ዋል ፡ አለበት ። የተጣሩ ፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡ ስብከትን ፡
ዘጋጀት ፡ ታላቅ ፡ ረዳቶች ፡ ናቸው ።

ክፍለ ፡ መደቦቹን ፡ በተራ፡ ቊጥር ፡ ለማስታወቅ ፡
ቻላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንኡሳን ፡ ክፍለ ፡ መደቦቹን ፡ ለአድ
ች ፡ ግራ ፡ እንዳይገባቸው ፡ በተራ ፡ ቊጥር፡ ማስታወ
፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ሰባኪው ፡ ለራሱ ፡ እንዲመቸ
፡ ሲል ፡ ብቻ ፡ በማስታወሻው ፡ ቢይዛቸው ፡ ደግሞ ፡
ከለከልም ። ክፍለ ፡ መደቦቹ ፡ እንዳይዘነጉ ፡ በንግግር ፡
ከል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ማስታወሳቸው ፡ ተገቢ ፡ ነው ።

የስብከት ፡ ኃይል ፡ በሰፊው ፡ የሚገኘው ፡ በጥሩ ፡
ፍለ ፡ መደቦች ፡ ነው ፤ ማለት ፡ የሐሳብን ፡ ጥሩ ፡ ፕላን ፡
ዘጋጀት ፡ ነው ። «ከመናገር ፡ በፊት ፡ ማሰብ ፡»እንደ
ው ፡ አስቀድሞ ፡ በጥሩ ፡ የሚያስብ ፡ ንግግሩም ፡ ጥሩ፡
ንለታል ።

የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ የክፍሉ ፡ ዘርፍ ፤ መግ
፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዓይነተኛ ፡ የስብ
፡ አቅዋሞች ፡ ስለሆኑ ፡ ሰባኪው ፡ በየቦታቸው ፡ በማስ



www.ethiopianorthodox.org

ታወሻው ፡ መያዝ ፡ አለበት ። የክፍሉ ፡ ዘርፍ ፡ ዋናውን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍል ፡ የሚያጐላ ፡ ጠቃሚ ፡ ሐሳብ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ። ምናልባት ፤ አንድ ፡ ክፍለ ፡ መደብ ፡ በሐሳብህ ፡ የማታስተውለው ፡ ቢመስልህ ፤ አሁንም ፡ አሁንም ፡ አስብበት ።

ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ሲናገር ፡ «ብዕር ፡ በእጅ ፥ ዓይን ፡ በጽሑፍ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ በሚገናኙበት ፡ ጊዜ ፡ ለሐሳብ ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቁ ፡ ዘመዶች ፡ ይሆኑታል ፤ ይህ ፡ አንዳችም ፡ ፍሬ ፡ ባይሰጥ ፡ ወደ ፡ ንባቡ ፡ ተመልሰህ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አስብበት ፡» ብሏል ። በክፍለ ፡ መደቦች ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረትክ ፡ መሆንህን ፡ ለራስህ ፡ አረጋግጥ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሐሳብ ፥ ልጓም ፡ እንደ ሌለው ፡ እንስሳ ፡ ባገኘው ፡ መንገድ ፡ ሽቅብና ፡ ቁልቁል ፡ ይዘምታል ። ስለዚህ ፡ በንግግር ፡ ጊዜ ፡ ከአንዱ ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሐሳብ ፡ መዝለል ፡ አይገባም ። በጠቅላላው ፡ የአንዱ ፡ ክፍለ ፡ መደብ ፡ ከሌላው ፡ ክፍለ ፡ መደብ ፡ ይልቅ ፡ መጠኑን ፡ በመጠበቅ ፡ መስፋፋት ፡ አለበት ፤ ማለት ፡ በጣም ፡ ክብደት ፡ ላለው ፡ ወይም ፡ ለበለጠው ፡ ክፍል ፡ ሰፊ ፡ ጊዜ ፡ ስጠው ። የመጨረሻው ፡ ክፍለ ፡ መደብህ ፡ ባዶውን ፡ እንዳይቀር ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ መደብህ ፡ ላይ ፡ አስፋፍተህ ፡ አትነጋገርበት ፤ ይህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባልሰበኩ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ዘወትር ፡ የሚገኝ ፡ ስህተት ፡ ነው ።

ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ የተገኙ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጥቂቶች ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎችንና ፡ ክፍለ ፡ መደቦችን ፡ እንጠቅሳለን ።



መዝ ፡ ዘዳዊት ፡ ፶ ፥ ፳፩ ፡ ይኽንን ፡ አደረግህ ፤ እኔም ፡ ዝም ፡ አልሁህ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ እንደሆንሁ ፡ መሰለህን ? እወቅስሃለሁ ፤ ኃጢአትህንም ፡ በፊትህ ፡ አቆማለሁ ።

ዓላማው ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ካለቦታው ፡ ሲያስቀምጥ ።

፩ ፤ የሰው ፡ ኃጢአት ፡ (ትምህርትንና ፡ ግሣጼን ፡ መጥላቱ ፡ ከኃጢአተኞችም ፡ ጋር ፡ በመገናኘቱ ፡ ወቦዘ ፡ ከቍጥር ፡ ፲፮—፳ ፡ ተመልከት ።)

፪ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዝምታ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ነፃነት ፡ አለው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዝምታ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ መርሳት ፡ ማለት ፡ አለመሆኑን ፡ (መዝ ፡ ፲ ፥ ፬—፲፩ ፡ ተመልከት ።)

፫ ፤ ሰው ፡ ያለ ፡ መንገዱና ፡ ያለ ፡ አግባቡ ፡ ሲሠራ ፡ (እግዚአብሔርን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ በማድረጉ ፡ ይህ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ስህተት ፡ መሆኑን ።)

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ራሱ ፡ እንደሚበቀል ፡ (የሰውን ፡ ፈቃድ ፡ እንደሚገዛ ፡) የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፲፱ ፤ ፲፱ ፡ ከአስማተኞቹም ፡ ብዙዎቹ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ሰብስበው ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አቃጠሉት ፡ ዋጋውም ፡ ቢታሰብ ፡ ሃምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ።

፭ ፤ ይህ ፡ በባርነት ፥ ሲገዙለት ፡ የኖሩበትን ፡ ኃጢአት ፡ በመጥላት ፡ አዝነውና ፡ ተበሳጭተው ፡ እን



www.ethiopianorthodox.org

ደነበረ ፡ የሚያሳይ ፡ አንድ ፡ ጉልህ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

፪ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ጨርሰው ፡ መለየታቸውንና ፡ ዳግ መኛም ፡ እንደማይመለሱበት ፡ የወሰኑበት ፡ የን ስሐ ፡ መግባት ፡ ምልክታቸው ፡ መሆኑን ፡ ያስረ ዳል ።

፫ ፡ ወደ ፡ ኃጢአታቸው ፡ እንደማይመለሱ ፡ የሚያረ ጋግጥ ፡ ኃይለኛውን ፡ ፈተና ፡ ማስወገዳቸውን ፡ ያስረዳል ።

፬ ፡ የዓለምን ፡ ፍቅር ፡ ድል ፡ ማድረጋቸውን ፡ የሚያ ስረዳ ፡ ማረጋገጫ ፡ ነው ።

፭ ፡ በሌሎች ፡ ላይ ፡ ክፋትን ፡ ከመሥራት ፡ የሚያግድ ፡ ትምህርት ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ የሰነፎች ፡ ባልንጀራ ፡ ግን ፡ ይ ጠፋል ።

፩ ፡ ሰነፎች ፡ እነማን ፡ ናቸው ?

ሀ) ጊዜያቸውንና ፡ ሐሳባቸውን ፡ በከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚያሳልፉ ።

ለ) ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያላቸውን ፡ እውነተ ኛና ፡ እርግጠኞችን ፡ ነገሮች ፡ የሚንቁ ።

ሐ) ለታላቅና ፡ ምንም ፡ ሊያግደው ፡ ለማይችል ፡ ደራሽ ፡ ነገር ፡ የማይዘጋጁ ።



፪ ፡ የሰነፎች ፡ ባልንጀራ ፡ በመሆን ፡ የሚከተለው ፡ ውጤት ፡ ምንድር ፡ ነው ?

ሀ) በመጥፎ ፡ አመላቸው ፡ እንቀባለን ፤ ወይም ፡ መጥፎ ፡ አመላቸው ፡ ይጋባብናል ።

ለ) ያሉበትን ፡ ሥቃይ ፡ እንካፈላለን ።

ሐ) በማይቀረው ፡ በእነርሱ ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ እን ጨመራለን ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ይፈረድብናል ።

፩ኛ ፡ ነገሥት ፡ ፲፱ ፥ ፲፪ ፡ ከእሳቱም ፡ በኋላ ፡ መል ጎም ፡ የለሰለሰ ፡ ነፋስ ፡ ድምፅ ።

፩ ፡ ይህ ፡ ራእይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐሳቡን ፡ ለመፈ ጸም ፡ በሚፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ከኃይል ፡ ይልቅ ፡ የዋ ህነትን ፡ ከማስደንገጥ ፡ ይልቅ ፡ ፍቅርን ፡ ማሳየት ፡ እንደሚመርጥ ፡ የሚያሳይ ፡ ታላቅ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

፪ ፡ ይህ ፡ ራእይ ፡ በሕግና ፡ (በኦሪት) ፡ በወንጌል ፡ (በተ ስፋ ፡) መካከል ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

፫ ፡ ይህ ፡ ራእይ ፡ ካለማመን ፡ ወደ ፡ ማመን ፡ እንደ ፡ ተለወጠ ፡ የሚያሳይ ፡ ታላቅ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ራእይ ፡ ፪ ፥ ፲፯ ፡ ድል ፡ ለነሣው ፡ ከተሰወረ ፡ መና ፡ እሰጠዋለሁ ፤ ነጭ ፡ ድንጋይንም ፡ እሰጠዋለሁ ፡ በድንጋ ዩም ፡ ላይ ፡ ከተቀበለው ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚያው ቀው ፡ የሌለ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ተጽፎአል ።

፩ ፡ የክርስቲያን ፡ ኑሮ ፡ ያው ፡ ክርስቲያን ፡ አሸናፊ ፡ እንደሚሆን ፡ የሚጠበቅበት ፡ ትግል ፡ እንደሆነ ፡ ያሳያል ።

፪ ፡ የአሸናፊው ፡ ቀዳሚ ፡ ዋጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ራሱ ፡ የሚሰጠው ፡ የነፍስ ፡ ምግብ ፡ ነው ።

፫ ፡ የታማኝ ፡ ክርስቲያን ፡ የመጨረሻ ፡ ዋጋ ፡ የሚገ ኘው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ከክርስቶስ ፡ የማይላቀቅ ፡ ፍ ቅር ፡ እንዳለው ፡ ሲያሳዩ ፡ ነው ።

ማቴዎስ ፡ ፲፬ ፡ ፲፬ ፡ መጥቶም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አ
የና ፡ አዘነላቸው ፡ ድውያኖቹንም ፡ ፈወሰ ።

፩ ፡ የክርስቶስ ፡ ርኅራኄ ፡ ከራሱ ፡ ነፃ ፡ ፈቃድ ፡ የሚ ፈልቅና ፡ ሁሉንም ፡ የሚያቅፍ ፡ ነው ።

፪ ፡ የክርስቶስ ፡ ርኅራኄ ፡ ፈጣንና ፡ መልካም ፡ ው ጤት ፡ ያለው ፡ እርዳታ ፡ ያበረክታል ።

፪ኛ ፡ ሳሙኤል ፡ ፲፰ ፡ ፴፫ ፡ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ አ
ዘነ ፡ በደጅ ፡ ላይም ፡ ወዳለችው ፡ ቤት ፡ ንጉሥ ፡ ወጣ ፡ አለ
ቀሰም ። እየሄደም ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ አብ
ሴሎም ፤ አብሴሎም ፡ ሆይ ፡ ልጄ ፡ ባንተ ፡ ፈንታ ፡ሙቼ ፡
በሆነ ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፡ ነበር ፤ አብሴሎም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡
ልጄ ፡ ሆይ ። ዓላማው ፤ «እውነተኛ ፡ አባትነት ።»

፩ ፡ እውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ኃጢአት ፡ በመሥራትም ፡ ቢ ሆን ፡ በማመፅ ፡ ከቶ ፡ አይለወጥም ።

፪ ፡ እውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ስለ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ቢዛነት ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ መስዋዕትነት ፡ ያደርሳል ።



፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፰ ፡ ለእውነተኛ ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡
[illegible] ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አንችልምና ። ዓላማው ፡ «የሰው ፡
[illegible]ግባሮች ፡ ዳርቻ ።»

፩ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊወዳደር ፡ ወይም ፡ ሊቃ ወም ፡ እንደማይችል ። ለምሳሌ ፡ የፍጥረት ፡ ሕ ጎች ፡ የጥበባት ፡ (የሳይንስ ፡) ሕጎች ፡ የጤንነት ፡ ሕጎች ፡ እንዲሁም ፡ የሞራል ፡ ሕጎች ፡ እነዚህን ፡ ላንታዘዛቸው ፡ እንችላለን ፤ ልንለውጣቸው ፡ ግን ፡ አንችልም ።

፪ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የመርዳት ፡ ታላቅ ፡ አስመስ ጋኝ ፡ ችሎታ ። የፈጠነ ፡ ውድቀት ፡ ሜሮዝን ፡ አስቡ ፡ (መሳፍንት ፡ ፭ ፡ ፳፫ ፡) ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ያለን ፡ የሥራ ፡ ጓደኝነት ፡ መብት ፡ መዝ ፡ ዘዳዊት ፡ ፰ ፡ ፭ ፡ ፯ ፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አሳነስ ኸው ፤ በክብርና ፡ በጌጽም ፡ ከለልኸው ፤ በእጆ ችህ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሾምኸው ፤ በእግሮቹ ፡ በታች ፡ ሁሉን ፡ አስገዛህለት ።

ዓላማው ፡ «የሰው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክብር ፡» የእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ መግባባት ።

፩ ፡ የሰውነት ፡ አንድነት ፡ (በዝቅተኛው ፡ ፍጥረት ፡ ዘር ፡ ካለ ፡ አንድነት ፡ አለ ፤ ማለት ፡ አንድነት ፡ ሳይኖር ፡ ዘር ፡ አለ ። በሰው ፡ ዘንድ ፡ ዘር ፡ ከአን ድነት ፡ ጋር ፡ አለ ። በመላእክቶች ፡ ዘንድ ፡ አንድ



www.ethiopianorthodox.org

ነት ፡ ካለ ፡ ዘር ፡ አለ ፤ ማለት ፡ ዘር ፡ ሳይኖር ፡ አንድነት ፡ አለ ።

፪ ፡ የተማሩ ፡ መሆን ፡ (ከእንስሳ ፡ ሁኔታ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ወዲሁም ፡ መጨረሻው ፡ የሌለው ፡ የልማት ፡ እርምጃ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ ነው ።)

፫ ፡ የፍጥረት ፡ ገዥነት ፡ (ገዥ ፡ መሆን ፡)

፬ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ (ሞራል ፡) ሕሊናን ፡ ጨምሮ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ለማድረግ ፡ ያለው ፡ ችሎታ ።)



ምዕራፍ ፡ ስድስት ።

## መደምደሚያ ።

ስብከት ፡ ዘወትር ፡ የሚደረገው ፡ ለአንድ ፡ ዓላማ ፡ ነው ። ስብከቱም ፡ እውጤቱ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረሱ ፡ በሩቅ ፡ ይመለከታል ። ስለዚህ ፡ የመደምደሚያው ፡ ዋና ፡ ባሕርያዊ ፡ ሐሳብ ፡ የዓላማውን ፡ ውጤት ፡ መግለጽ ፡ ነው ።

መጀመሪያ ፡ በመደምደሚያው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ አንዳንድ ፡ የስሕተት ፡ ምክንያቶችን ፡ እንመልከት ።

፩ ፡ ዋነኛው ፡ ምክንያት ፡ በሰባኪው ፡ በኩል ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅድስና ፡ ሲጐድል ፡ ነው ። ስብከቱ ፡ በስብከት ፡ ጥበብ ፡ በኩል ፡ ትክክለኛና ፡ የተመቻቹ ፡ ክፍለ ፡ መደቦች ፡ እያሉት ፡ መግቢያውም ፡ በጥብቅ ፡ የታሰበበት ፡ ሰባኪውም ፡ ድምፀ ፡ መልካም ፡ ሊሆን ፡ ሲችል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ አንድነት ፡ በጣም ፡ የተሟላና ፡ ጥብቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ሌሎችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያስጠጋ ፡ አይችልም ፤ ሌሎችን ፡ በሚገሥጽበት ፡ ጊዜ ፡ የግሉ ፡ ሕይወታዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ አብዛኛውን ፡ ጉዳይ ፡ ይገልጽበታል ። በዚህ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ጉድለት ፡ የንግግሩን ፡ ኃይል ፡ ያደክምበታል ።

፪ ፡ የስብከቱን ፡ አንዱን ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ አጋኖ ፡ መስበክ ፡ ሌሎቹን ፡ ያበላሻቸዋል ፤ ለምሳሌ ፡ የአንድ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሰባኪ ፡ ስብከቶች ፡ የደረቅ ፡ ትምህርትና ፡ የክርክር ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ የመስተያየት ፡ ሁኔታቸው ፡ በጣም፡ የተወሰነ ፡ ይሆናል ። ለአንድ ፡ ካህን ፡ ጉብኝት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ታማኝነት ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ በቲዎሪ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ከመስበክ ፡ ያድናል ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሰባኪው ፡ በብስጭት ፡ ወይም ፡ በቊጣ ፡ መንፈስ ፡ ብቻ ፡ የሚሰብክ ፡ ሲሆን ፡ የእርሱ ፡ ስሞታ፡ ደካማና ፡ ፍሬ፡ ቢስ ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፡ በብርቱና ፡ ጤናማ ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ባለመመሥረቱ ፡ ነው ።

፫ ፡ ፋናቲክ ፡ እንዳይባል ፡ የየዋህነት ፡ ፍርሃት ፤ ንቁና ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፋናቲክ ፡ የመባል ፡ ዕድል ፡ ይገጥመዋል ። ለምሳሌ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲሁም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ዕድል፡ ገጥሞአቸዋል ። ይህ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ፍርሃት ፡ ነው ። ነፍሳትን ፡ ለማዳን ፡ በቊርጥ ፡ ላደረ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ በፍጹም ፡ አያሸብረውም ። የጋለ ፡ መንፈስ ፡ አለው ፡ ብትባል ፡ አትፍራ ። እውነተኛ ፡ ሰባኪ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ አቋቋምና ፡ ሁኔታ ፡ መውሰድ ፡ ወይም ፡ መከተል ፡ አለበት ።

«ዕብዶች ፡ ብንሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ባለ ፡ አእምሮች ፡ ብንሆን ፡ ለእናንተ ፡ ነው ። ይህንን ፡ ስለ ፡ ቈረጥን ፡ የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ግድ ፡ ይለናልና ።» ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

፬ ፡ በሰባኪው ፡ በኩል ፡ የሚጐድለው ፡ ብርቱ ፡ መታመን ፡ ይህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚደርሰው ፡ ደካማና ፡ ስሕተተኛ ፡ በሆነ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ነው ። ሰባኪው ፡ የሚሰብክበት ፡ ወንጌል ፡ የአድማጮቹን ፡ ፍላጎት ፡ እንደሚያረካና ፡ ከሌላ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ የሚፈልጉት ፡ እሸው ፡ መሆኑን ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ካላመነ ፡ ለመስበክ ፡ ምንም ፡ ኃይል ፡ አያገኝም ። ስለዚህ ፡ ብርቱ ፡ ስብከት ፡ የሚገኘው ፡ የክርስቶስ ፡ የመድኃኒትነቱ ፡ ኃይል ፡ በሰባኪው ፡ በኩል ፡ የሙሉ ፡ እምነትና ፡ ተቀባይነት ፡ ልማድም ፡ ሲኖር ፡ ነው ። «ያመንሁትን ፡ አውቃለሁና ፡ የሰጠሁትንም ፡ አደራ ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሊጠብቅ ፡ እንዲችል ፡ ተረድቻለሁ ።» ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።

እንግዲህ ፡ አሁን ፡ መደምደሚያው ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ሊኖርበት ፡ እንደሚገባው ፡ እንይ ።

፭ ፡ መክሰስ ፡ (መድገም ፡) ይህ ፡ በጣም ፡ የሚያስፈልገው ፡ በክርክር ፡ ስብከት ፡ ነው ። ማለት ፡ ማስረጃን ፡ ማቅረብ ፡ ስለሚሆን ፡ ስብከት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አድማጮቹ ፡ እስኪሰለቹ ፡ ድረስ ፡ ያለፈውን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ መድገም ፡ ማለት ፡ አይደለምና ፡ በጣም ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልጋል ። አነጋገሩና ፡ ቃላቶቹም ፡ የተለዋወጡ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰባኪ ፡ ለወጣት ፡ ተማሪዎች ፡ «በመግቢያው ፡ ጊዜ ፡ ለአድማጮቻችሁ ፡ ወዴት ፡ እንደምትጓዙ ፡ አሳዩአቸው ። በመደምደሚያው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የት ፡ እንደ ፡ ነበራችሁ፡ አስታውሱአቸው ፡» እንደዚሁም፡ «የጦሩን ፡ ሜዳ ፡ መፈተሽ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ድል ፡ መመታቱ ፡ ሲታወቅ ፡ እጦር ፡ ሜዳ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሙሉ ፡ ጦርነት ፡ መግጠም ፡ ደግሞ ፡ አስፈላጊ ፡ አይ



www.ethiopianorthodox.org

ደለም ፡» ስለዚህ ፡ ክለሳ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ የተነገረውን ፡
ለመድገም ፡ ሲፈለግ ፡ በጣም ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልጋል ።

፪ ፡ ማመልከትና ፡ ማሰማት ፡ የወንጌል ፡ ስብከት ፡
እንደራስ ፡ ጉዳይ ፡ ማየት ፡ ነው ። በአገላለጹም ፡ ሁለት ፡
መልክ ፡ ያለው ፡ እንዳይሆንብህ ፡ በጣም ፡ መጠንቀቅ ፡
አለብህ ። አድማጮችህን ፡ ለመጥቀስ ፡ በፈለግህ ፡ ጊዜ ፡
መጀመሪያ ፡ አማኞችን ፡ ቀጥሎ ፡ ያላመኑትን ፡ መጥራት ፡
ማለት ፡ መጥቀስ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ አትዘንጋ ። ሁለት ፡
መልክ ፡ ያለው ፡ የዘዴ ፡ አነጋገር ፡ አድማጮቹን ፡ ከሚያቀ
ርብ ፡ ወይም ፡ ከሚስብ ፡ ይልቅ ፡ አሳዳጅ ፡ ወይም ፡ አባ
ራሪ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶአል ። ከቀዳሚው፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡
አስተዋጽኦውን ፡ ማዘጋጀት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ሰባኪው ፡
በስብከቱ ፡ ዋናው ፡ አካል ፡ ሲነጋገርበት ፡ ከነበረው ፡ እው
ነተኛ ፡ መልክ ፡ ሳይለወጥ ፡ እንዲወሰን ፡ ያስፈልጋል ።
ማለት ፡ በስብከቱ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓይነተኛውን፡
ብቻ ፡ መጥቀስ ፡ እንጂ ፡ ጠቅላላውን ፡ መድገም ፡ አያስፈ
ልግም ። ስሞታው ፡ ወይም ፡ ወቀሳው ፡ በተለየ ፡ ከውስ
ጣዊ ፡ ሕሊናና ፡ ከበጎ ፡ ፈቃድ ፡ የመነጨ ፡ ሊሆን ፡ ይገ
ባል ፤ ይኸውም ፡ ግልጽና ፡ ልብን ፡ የሚወጋ ፡ (የሚነካ) ፡
መሆን ፡ አለበት ። አንድ ፡ ዓሣ ፡ ነባሪ ፡ አጽማጅ ፡ የመን
ደሩን ፡ ቄስ ፡ ስብከት ፡ ሰምቶ ፡ «በቂ ፡ የሆነ ፡ ጥሩ ፡ ስብ
ከት ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መንጠቆ ፡ ወይም ፡ የዓሣ ፡ ነባሪ ፡
መውጊያ ፡ ጦር ፡ የለውም ፡» አለ ፡ ይባላል ። የዛለና ፡ ቀዝ
ቃዛ ፡ አንደበት ፡ ሁልጊዜ ፡ በአትሮኖሱ ፡ ላይ ፡ የድካምን ፡
ምንጭ ፡ ሲያፈስበት ፡ ስለሚታይ ፡ ንቃትና ፡ የሞቀ ፡ አን



ደበት ፡ ደግሞ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምንጭ ፡ እንደሆነ
ተገምቶአል ።

፫ ፡ ልብን ፡ የሚነካና ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ መደም
ሚያ ፡ ይህ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ሊዘጋጅ ፡ ይ
ላል ። ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በሚያዘወትሩ ፡ ሰዎች
ይበልጥ ፡ ይሠራል ፡ ወይም ፡ በስብከት ፡ መጨረሻ ፡ ከ
ጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ከዋናው ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ የሚ
ሳሰል ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ የተመረጠ ፡ ጥቅስ ፡ ለመደምደሚያ
ቢወሰድ ፡ ልብ ፡ ተከፍቶ ፡ የሚቀበለው ፡ ነው ። የሆነ
ሆኖ ፡ ለቀኑ ፡ ስብከት ፡ የተወሰደው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ
ክፍል ፡ በአድማጮቹ ፡ ዘንድ ፡ የመጨረሻ ፡ ማኅተም
ሆኖ ፡ መቀረጽ ፡ አለበት ።

በመደምደሚያው ፡ ጊዜ ፡ ሰባኪው ፡ ራሱን ፡ ለሕ
ዝብ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፡ እንዲሁም ፡ ስብከቱን ፡ የጨረሰ
ሳያስመስል ፡ የመጨረሻውን ፡ ከስብከቱ ፡ ሐሳብ ፡ ጋር
በማገናኘት ፡ የአድማጮቹን ፡ የጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ በመጥቀስ
ማስገንዘብ ፡ አለበት ።

መደምደሚያው ፡ በአጭር ፡ አነጋገር ፡ ዋናውን
ስብከት ፡ በሙሉ ፡ የሚያሳስብ ፡ እንጂ ፡ ከስብከቱ ፡ አ
ዱን ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ሊጠቀስበት ፡ አይገባም ። በስብከቱ
ውስጥ ፡ ከተነገሩት ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ከሆኑት ፡ ንግግሮች
ላይ ፡ መመሥረት ፡ አለበት ። ረጅም ፡ መሆን ፡ የለበትም
ስብከትህን ፡ የምትዘጋ ፡ መሆንህን ፡ ከቶ ፡ አታስታውቅ
እለዚያም ፡ ተስፋ ፡ የሰጠህበትን ፡ ቃልህን ፡ መጠበቅ
አለብህ ። «በመጨረሻ ፡ ደግሞ ፡» እያለ ፡ የሚደጋግም



www.ethiopianorthodox.org

ሰባኪ ፡ በአድማጮቹ ፡ ዘንድ ፡ አይወደድም ። አንድ ፡ ትል
ቅ ፡ ሰባኪ ፡ ሲናገር ፡ «ብቻህን ፡ ደህና ፡ ሁነህ ፡ ለመኖር ፡
ተማር ፤ ጥይት ፣ ካለቀብህ ፣ በኋላም ፡ ተኩስህን ፡ አቁም ፤
ምክንያቱም ፡ ጉባኤው ፡ ባሩድ ፡ የሌለበትን ፡ ጥይት ፡
ቶሎ ፡ ስለሚያውቁት ፡ አይፈሩትም ፡» ይል ፡ ነበር ።
በዓለም ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ የታወቀ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ ደግሞ ፡
«አድማጮችህ ፡ ልባቸውን ፡ ከፍተው ፡ በታላቅ ፡ ጉጉት ፡
በሚሰሙህ ፡ ጊዜ ፡ ስብከትህን ፡ ዝጋ ፤ ምክንያቱም ፡ በሌላ፡
ቀን ፡ በታላቅ ፡ ናፍቆትና ፡ መታደስ ፡ ተመልሰው ፡ ይመ
ጡልሃልና ፡» ይላል ።

የስብከትን ፡ ዋና ፡ ሐሳብ ፡ ከተመለከትን ፡ ዘንድ ፡
የስብከቱን ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ መቀስቀስ ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፣ ነገር ፡ ግን ፡ እሰሚው ፡ ፍላጎት ፡ መድረስ ፡
እንዲሁም ፡ የሰማውን ፡ በሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ማግባባት ፡
ነው ። በአትሮኖስና ፡ በቲያትር ፡ መደብ ፡ (ስቴጅ ፡) መካ
ከል ፡ ያለው ፡ ትልቁ ፡ ልዩነትም ፡ ይህ ፡ ነው ። ብዙ ፡
ጊዜ ፡ አድማጩ ፡ መንፈሱ ፡ ሳይቀሰቀስለት ፣ ሳይረታ ፤
ከቀድሞ ፡ ሥራው ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ሳይፈ
ልግ ፣ እንዲሁ ፡ ሰምቶ ፡ ብቻ ፡ የሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።
ይህ ፡ የራሱ ፡ ፋንታ ፡ ነው ። በሰባኪው ፡ በኩል ፡ ግን ፡
ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስሕተት ፡ ሊገኝበት ፡ ከቶ ፡ አይገባም ።

መደምደሚያው ፡ በየጊዜው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፣
መንገድ ፡ ሊሆን ፡ ያስፈልጋል ። አቅዋሙም ፡ በስብከቱ ፡
ባሕርያዊ ፡ አቀራረብ ፡ ሊወስን ፡ ይገባል ። በአንድ ፡ ዓይ
ነት ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ በልማድ ፡ የሚሆነውን ፡ መተው ፤
ለምሳሌ ፣ በስሞታ ፣ ወይም ፡ በግሣጼ ፡ ከመፈጸም ፡ ይልቅ ፡



አንድ ፡ ጥያቄ ፡ ጣል ፡ አድርጎ ፡ ማቆም ፣ ስለ ፡ መልሱም ፡
የአድማጮቹ ፡ ሕሊና ፡ እንዲመራመርበትና ፡ ከዋናው ፡
ስብከት ፡ ጋር ፡ እንዲአመዛዝነው ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ረጅም ፡ ስብከት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡
እንዳይሰለችና ፡ እንዳይፈዝ ፡ ለማድረግ ፡ በመካከል ፡ ለጥ
ቂት ፡ ሴኮንዶች ፡ ዝም ፡ ማለት ፣ ወዲያውም ፡ በጥቂት ፡
ቃላት ፡ ብቻ ፡ አጭር ፡ ጸሎት ፡ ቢደረግ ፡ የአድማጮቹን ፡
ንቃት ፡ በመማረክ ፡ ሊያስጠነቅቃቸው ፡ ይችላል ። መደ
ምደሚያው ፡ ሁልጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ መዘጋጀት ፡ ሲገባው ፣
ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ድንገተኛ ፡
ንግግር ፡ ሲደረግ ፡ የሚሰማው ። ይህ ፡ ሲሆንም ፡ ሰባኪው፡
አስቀድሞ ፡ ባላሰበበት ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሲባዝን ፡
ይገኛል ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲደረግ ፡ ይታያል ።
በመደምደሚያው ፡ የሚደረገውን ፡ ስሞታ ፡ የሚለውጥበት ፡
አብዛኛው ፡ ጊዜ ፡ በአካባቢው ፡ አዘውትሮ ፡ የሚያየውን ፡
ሁኔታ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ነገር ፡ ይግባኝ ፡ የሚለው ፡
ወይም ፡ ቅርታውንና ፡ ስሞታውን ፡ የሚያቀርበው ፡ በነ
ገሩ ፡ ዘልቆ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡
በማድረግ ፡ ነው ። ተስፈኞችም ፡ ዘላቂዎች ፡ ናቸው ።
አንድ ፡ ሰባኪ ፡ በራሱ ፡ ነገር ፡ እምነት ፡ እንዳለው ፡ ካልታ
የበት ፡ በቀር ፣ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እምነት ፡ ለማስገባት ፡
አይችልም ። አንድ ፡ ተስፋ ፡ የቈረጠ ፡ የወንጌል ፡ መልእ
ክተኛ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ትልቅ ፡ ሰባኪ ፡ ዘንድ ፡ መጥቶ ፣ ስብ
ከቱ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ የ ማያገኝበትን ፡ ምክንያት ፡
ምን ፡ እንደሆነ ፡ እንዲገልጽለት ፡ ጠየቀው ፤ ትልቁ ፣ ሰባ



www.ethiopianorthodox.org

ኪም ፡ መልሶ ፡ «በምትሰብክበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፤ ልባቸው ፡ የሚታደስ ፡ ወይም ፡ ከድሮ ፡ ሁኔታቸው ፡ የሚለወጡ ፡ ሰዎች ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ ታደርጋለህን ?» ሲል ፡ ጠየቀው ። የወንጌል ፡ መልእክተኛውም ፡ «አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ፡ ዘወትር ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ ለማድረግ ፡ አልችልም ፡» ብሎ ፡ መለሰለት ፤ ትልቁ ፡ ሰባኪም ፡ «ጉድለትህ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ነዋ ፡» አለው ። ትልልቆች ፡ ሰባኪዎች ፡ በስብከት ፡ የተናገሩትን ፡ በሥራ ፡ ስለሚያሳዩ ፡ ከቶ ፡ ተስፋ ፡ አይቈርጡም ።

አንድ ፡ ይግባኝ ፡ የሚቀርበው ፡ ያለፈው ፡ ጥቃት ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ጉድለት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ገልጾ ፡ ይህን ፡ ስሜት ፡ ወደ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ዳኛ ፡ ልብ ፡ እንዲገባና ፡ ዳኛውም ፡ ልክ ፡ እንደራሱ ፡ ጥቃት ፡ ሲሰማው ፡ ያለፈውን ፡ ፍርድ ፡ ግልብጥብጥ ፡ አድርጎ ፡ ይለውጠዋል ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ሲሆን ፤ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በሰባኪውና ፡ በአድማጮቹ ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ ስሜት ፡ የሚቀሰቅሰው ፡ ተስፈኛ ፡ በሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ወይም ፡ ስሞታ ፡ ነው ። ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ወይም ፡ ስሞታ ፡ ሰባኪው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደሚደገፍ ፡ የሚተማመን ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ። የሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ በሙሉ ፡ እምነት ፡ የተከናወነ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንዴት ፡ እንዳከበረው ፡ እናውቃለን ። ሰባኪው ፡ ራሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነትና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ እምነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ በመደምደሚያው ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ ስሞታ ፡ ላይ ፡ ይታያል ።



የሐዋርያት ፡ ታላቁ ፡ ምልክት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆኑትን ፡ ነፍሳት ፡ በስብከት ፡ ኃይል ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ደኅንነት ፡ መማረክ ፡ ነው ። ሐዋርያት ፡ በጌታቸው ፡ ላይ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚችል ፡ እስከ ፡ የሌለው ፡ እምነት ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ ለማስረዳት ፡ ቅዱሱ ፡ ሐዋርያ ፡ በጻፈው ፡ የሥራቸው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ሊጠቅሰው ፡ የተገደደበትን ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ እንመልከት ፤ ሐዋርያትም ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ትንሣኤ ፡ በታላቅ ፡ ኃይል ፡ ይመሰክሩ ፡ ነበር ፤ ሁሉም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ነበረባቸው ። (የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፬ ፡ ፴፫ ።)

---



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ሰባት ።

# ስብከትን ፡ በጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ።

ስብከቶችን ፡ በሙሉ ፡ በጽሑፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ ይገባ ፡ እንደሆን ፤ ሰባኪ ፡ ሁሉ ፡ እራሱን ፡ የሚጠይቅበት ፡ ጉዳይ፡ ነው ። ስብከቶች ፡ ሁሉ ፡ በሞላ ፡ በጽሑፍ ፡ ሊዘጋጁ ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ በፍጹም ፡ ሊጻፉ ፡ አይገባቸውም ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ የባሰ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አብዛኛው ፡ ሰባኪ ፡ የስብከትን ፡ ገሚስ ፡ በጽሑፍ ፡ መያዝ፡ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ ያድናል ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ ይኖረዋል ። ይህ ፡ ሲባል ፡ ግን ፤ ስብከቱን ፡ ለጉባኤው ፡ በንባብ ፡ ያሰማል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ቢሆንም ፤ በአንድ ፡ አትሮኖስ ፡ እንደ ፡ ደንበኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚሰብክ ፡ ሰባኪ ፤ ስብከቱን ፡ በሙሉ ፡ በጽሑፍ ፡ መያዝ ፡ አስፈላጊው ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ በጥንቃቄ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ። ለዚህም ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እንዲኖረው ፡ እራሱ ፡ መገመት ፡ ይገባዋል ፤ ማለት ፡ ከሳምንቱ ፡ መግቢያ ፡ ቀን ፡ ቢጀምር ፡ ጥሩ ፡ ነው ። በ፲፩ኛው ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ በችኮላ ፡ ስብከቱን ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ሰባኪ ፤ ስብከቱን ፡ በሚያበረክትበት ፡ ጊዜ ፤ በጥንቃቄና ፡ በጸሎተኛነት ፡ እያሰበ ፡ እንደሚያዘጋጅ ፡ ሰባኪ ፤ በሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ እኩል ፡ ሊታመንበት ፡ ወይም ፡ ነፃነትና ፡ ደስታ ፡ ሊያገኝበት ፡ አይችልም ። ሰባኪዎች ፡ ሁሉ ፡ በሕመም ፡ ወይም ፡ በትርፍ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ ፡ ልዩ ፡ አጋጣሚ ፡ ጕዳይ ፡ ምክንያት ፡ ስብከታቸውን፡
ለማዘጋጀት ፡ የሚያገኙት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አጭር ፡ ሲሆን
ባቸው ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ የራሱ ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ የራሱ ፡
ጥፋት ፡ ባለመሆኑ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የሚመጣለትን ፡
እርዳታ ፡ ለመጠበቅ ፡ መብት ፡ አለው ፤ ይህንኑም ፡ በእር
ግጥ ፡ ያገኘዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከራሱ ፡ ስንፍና ፡ ወይም ፡
ይደርስልኛል ፡ በማለት ፡ በቀጠሮ ፡ በማቈየት ፡ ጕድለት ፡
የሚያደርግ ፡ ሰባኪ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በረከት ፡ ተስፋ ፡
ሊያደርግ ፡ አይችልም ።

ሰባኪው ፡ በሚሰብክበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ አድ
ርጎ ፡ የመጻፍ ፡ ልማድ ፡ እንዲኖረው ፡ መጣጣር ፡ አለበት ።
«በሚሰብክበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሚቻለው ፡ መጠን ፡ ጥሩ ፡
አድርጎ ፡ የማይጽፍ ፤ ጨርሶ ፡ ያለመጻፍን ፡ ልማድ ፡ ይወ
ስዳል ። » ተብሏል ። ያለ ፡ ማስታወሻ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ አን
ዳች ፡ ጽሑፍ ፡ የመስበክ ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ቢሆ
ንም ፤ ስብከቱን ፡ በጽሑፍ ፡ ማስታወሻ ፡ ቢይዝ ፡ የሚሻ
ለው ፡ መሆኑን ፡ ከመምከር ፡ አንቦዝንም ።« የጥሩ ፡ ንግ
ግር ፡ ምስጢር ፡ በብዕር ፡ መነጋገር ፡ ነው ።» ይባላል ።
እንደ ፡ ሕጉ ፡ በጽሑፍ ፡ ቢያዝ ፡ አይጠቅምም ፡ የተባለው ፤
ከአትሮኖስም ፡ ቢነገር ፡ አይጠቅምም ። በብዙ ፡ ጥንቃቄና ፡
ማሰብ ፡ በጽሑፍ ፡ የተያዘው ፡ ስብከት ፡ ጥሩ ፡ አቀራረ
ብና ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ እንደሚያስገኝ ፡ የታወቀ ፡
ነው ። ስለዚህም ፡ ሰባኪው ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠውን ፡ ዓላማ ፡
ለማቅረብ ፡ ሲፈልግ ፡ በሚቻለው ፡ መጠን ፡ ሁሉ ፡ በበ
ለጠ ፡ መንገድ ፡ መጣጣር ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ሊሆን ፡
ይገባል ። በአቀራረብ ፡ ጠንቃቃ ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ በን



ግሩ ፡ አንዱን ፡ ሳያጠናቅቅ ፡ አለፍ ፡ አለፍ ፡ የሚል ፡
ባኪ ፡ በአድማጩ ፡ ጉባኤ ፡ ፊት ፡ እዚያው ፡ ክብሩ ፡ ይ
ንስበታል ፤ ይህም ፡ ሲሆን ፡ እነርሱን ፡ የሚማርክበት ፡
ኃይል ፡ ይዝላል ፤ ከፍተኛውንም ፡ መልእክተኛነቱን ፡
ንቀት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ተግባ
ሩን ፡ ለመፈጸም ፡ የታጠቀ ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛ ፡ ግን ፡
ሚያገለግላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡
ሉ ፡ ክብሩንና ፡ ዋጋውን ፡ ወይም ፡ ግምቱን ፡ ከቶ ፡
ያስቀንስም ። ተግባሩን ፡ ለመፈጸም ፡ የታጠቀ ፡ መሆ
ኑን ፡ በቀደምትነት ፡ የሚያስረዳለት ፡ ደግሞ ፡ በአትሮኖሱ ፡
ላይ ፡ ለሚያደርገው ፡ ስብከት ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ሕሊናዊ ፡
ዝግጅት ፡ በማደራጀቱ ፡ ነው ። ስብከቱን ፡ ለማዘጋጀት ፡
ሰለጠ ፡ ሥራውን ፡ የማያበረክት ፡ ሰባኪ ፡ እውነተኛ ፡
እግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ አይደለም ።

በአትሮኖስ ፡ የሚሰብክበት ፡ ቋንቋ ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡
ግርነት ፡ የተቀዳጀ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ለዚህ ፡ ነገር ፡
ታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትልቅ ፡ ምሳሌ ፡ ይሆነናል ፡
ሩ ፡ ተናጋሪዎች ፡ የሚባሉት ፡ ጥልቅና ፡ ከፍተኛ ፡ ሐሳብ
ያዘውን ፡ ጕዳይ ፤ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ በቀላሉ ፡ ሊረዳው
ሚችል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ ጸያፍን ፡ በከተተና ፡ የጕ
ንም ፡ ክብር ፡ በማይቀንስ ፡ አነጋገር ፡ ለመግለጽ ፡ የሚ
ሉት ፡ ናቸው ። የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ስልት ፡ ተጀምሮ
እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። በአትሮኖስ ፡ ላይ
ወጡ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ስልት ፡ የተለወጠ ፡ ልዩ
ይነት ፡ ስልት ፡ ይኖረዋል ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ትልቅ ፡ ስሕ
ት ፡ ነው ። ሕዝቡ ፡ ትርጕሙን ፡ በቀላሉ ፡ ሊረዱት ፡ የሚ



www.ethiopianorthodox.org

ይችሉትን ፡ ቃላት ፡ በፍጹም ፡ አለማስገባት ፡ ነው ። በተ
ቻለ ፡ መጠንም ፡ ቴክኒካዊና ፡ የሊቅነት ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡
አነጋገር ፡ ማስወገድ ፡ ነው ።

የስብከት ፡ ንግግር ፡ ትርጒማቸው ፡ በማይራራቅ ፡
በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃላት ፡ ሊነገር ፡ ይገባዋል ፤ ይህም ፡ ሲባል ፡
ክብደት ፡ የሌለው ፡ እንዲሆን ፡ ማሰብ ፡ አለ ። አንዱ ፡ ቃል፡
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሊደጋገም ፡ አይገባም ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ሐ
ሳቡ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ መደጋገሙ ፡ ሲገባ ፡ የዚህ ፡ ሐሳብ ፡
መግለጫ ፡ ቃላት ፡ ግን ፡ መለዋወጥ ፡ አለባቸው ፡ ማለት ፡
ነው ። የተመሳሰሉ ፡ አዳዲስ ፡ ቃላት ፡ ለማግኘትና ፡ ሐሳብ
ንም ፡ ንቁ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ የመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ድ
ጋፍ ፡ በጣም ፡ ይረዳል ። ግጥምና ፡ ቅኔ ፡ ማጥናት ፡ ለሰው ፡
የቋንቋ ፡ ገዢ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ ያደርገዋል ። በጥሩ ፡
ስልት ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍቶች ፡ የማያነብ ፡ ሰው ፡ እን
ደዚሁ ፡ በጥሩ ፡ ስልት ፡ ሊጽፍ ፡ ወይም ፡ ሊነጋገር ፡ አይች
ልም ።

በአትሮኖስ ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ አነጋገር ፡ ከጓድ ፡
ጋር ፡ እንደሚደረገው ፡ ንግግር ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ፡
እንደ ፡ ንባብ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። በየመንገዱ ፡ የሚዘወ
ተሩ ፡ የብልግና ፡ ቃላት ፤ የቀልድ ፡ አነጋገር ፤ ቃልን ፡ በመ
ቍረጥ ፡ ወይም፡ በማሳጠር ፡ የሚደረግ ፡ አነጋገር ፤ ምንም ፡
ሰንኳ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ የተወደዱና ፡ የሚያስቁ ፡ ቢሆኑ ፤
ለአትሮኖስ ፡ ግን ፡ ምቹ ፡ አይደሉም ። ያለ ፡ ፍንደቃ ፡ ክ
ብር ፤ ያለ ፡ ብልግና ፡ ደግሞ ፡ ገርነት ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል ።

አንድ ፡ ሊቅ ፡ እንዳለው ፡ «ሰባኪው ፡ አደራ ፡ የተ
ባለበትን ፡ መልእክት ፡ ለመፈጸም ፡ ራሱ ፡ ጕዳዩን ፡ በተቀ



ደሰ ፡ መንገድ ፡ ሊይዘውና ፡ እንደ ፡ ሽክላ ፡ ማሰሮ ፡ አደራ
የተሰጡት ፡ አድማጮቹን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ከሰማ
ያዊው ፡ የወንጌል ፡ ሪቅ ፡ ወይም ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ባዶነታቸ
ውን ፡ ሊሞላ ፡ በሚፈልግበት ፡ መንገድ ፡ አትሮኖሱን ፡ ከማ
ሞገስ ፡ በቀር ፡ የተሻለ ፡ የአነጋገር ፡ ሕግ ፡ አልተሰጠም ።»
በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ሰባኪው ፡ ለአትሮኖሱ ፡ የሚገባውን ፡
ቃላት ፡ በቅድስና ፡ መንገድ ፡ አስቦ ፡ አድማጮቹ ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንዲሞሉለት ፡ ከሚያደርገው ፡ የግል ፡ ት
ግል ፡ በተቀር ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ ሌላ ፡ የንግግር ፡ ሕግ ፡ የ
ለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡ አሰራር ፤ የሰዋስውን ፡ መን
ገድ ፡ መከተል ፡ ሲኖርባቸው ፡ ወዲሁም ፡ አሠራራቸው ፡
ገራገር ፡ መሆን ፡ አለበት ። ዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ረጃጅምና ፡
የተያያዙ ፡ ሲሆኑ ፡ ለአድማጮቹ ፡ ስለማይያዙላቸው ፡ ትር
ጓሜውን ፡ ለማስተዋል ፡ እንዲቻል ፡ እጥር ፡ ንጥር ፡ ያሉ ፡
መሆን ፡ ይገባቸዋል ። ምንም ፡ አነጋገሩ ፡ የተጌጠ ፡ ቢሆን ፡
ግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ የንግግር ፡ ስልት ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ።

ንግግሩን ፡ በመልክ ፡ በመልኩ ፡ ለአድማጮች ፡
ማቅረብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ በየ
ዓይነቱ ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ በብዛት ፡ ይገኛል ፤ ለሰባኪው
ም ፡ ትልቅ ፡ መሪ ፡ ነው ። በስብከት ፡ ውስጥ ፡ የመጽሐ
ቶች ፡ ጥቅም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ አስቀድሞ ፡ ተገል
ጾአል ። ነገር ፡ ግን ፡ አገላለጻቸው ፡ ረጃጅም ፡ መሆን፡ የለባ
ቸውም ። ለማስረጃ፡ ተብሎ፡ የሚቀርበው፡ ምሳሌና፡ ትችት፡
ብዙ ፡ ደቂቃዎች ፡ የፈጀ ፡ እንደሆነ ፡ የዋናውን፡ ስብከት ፡
ዓላማን ፡ ስቶ ፡ እራሱ ፡ የዚህን ፡ ቦታ ፡ የሚይዝ ፡ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰባኪው ፡ ጥቅሶቹንና ፡ ሐሳቦቹን ፡ በማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ እንደሚይዝ ፡ ሁሉ ፡ ለማስረጃ ፡ ስለሚያቀርባቸው ፡ መጽሔቶች ፡ ደግሞ ፡ በማስታወሻው ፡ ላይ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ጽፎ ፡ ቢይዝ ፡ እጅግ ፡ እንደሚጠቅመው ፡ ይገነዘበዋል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲባል ፡ ዞትር ፡ ለሚሰብክ ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛ ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ በጣም ፡ አስፈላጊውና ፡ ሊለየው ፡ እንደማይገባ ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ መምህር ፡ ስለ ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ ዓይነተኛ ፡ ጥቅም ፡ ሲገልጽ ፡ «የወንጌል ፡ መልእክተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የማስታወሻ ፡ ደብተሩንና ፡ እርሳሱን ፡ በእጁ ፡ ሳይዝ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ እንኳን ፡ ማንበብ ፡ አይገባውም ፤ ምክንያቱም ፡ ለወደፊት ፡ የሚጠቅመው ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሲያገኝ ፡ ለማስታወስ ፡ ስለሚረዳው ፡ ነው ፡» ይል ፡ ነበር ።

በጽሑፍ ፡ ስለሚዘጋጀው ፡ ስብከት ፡ የመጨረሻ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የሚሰጠው ፡ «ስብከትህን ፡ ስትጨርስ ፡ ጭልምልም ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ ወይም ፡ በተወሳሰበ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አትዝጋ ።»



ምዕራፍ ፡ ስምንት ።

## ጠቅላላ ፡ አሰባበክ ።

የስብከት ፡ አመራር ፡ ፍሬ ፡ እንዲአፈራ ፡ ለማድረግ ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ አለው ። ስለዚሁ ፡ ተብሏልና ፡ «ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ብታነብ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥርት ፡ አድርገህ ፡ ባትገልጻቸው ፡ ድካምህ ፡ ሁሉ ፡ የባከነ ፡ ይሆናል ፤ መናገሩን ፡ ተናገር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በጥቂቱና ፡ ጥርት ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለህ ።» ብዙ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ስብከቶች ፡ ከአመራራቸው ፡ ወይም ፡ ካጣጣላቸው ፡ መጉደል ፡ የተነሳ ፡ ከጋራ ፡ ጋር ፡ ተጋጭቶ ፡ እንደሚበታተን ፡ መርከብ ፡ ሆነው ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ቀርተዋል ። ብዙ ፡ ተራ ፡ ስብከቶች ፡ ደግሞ ፡ የአመራርን ፡ ወይም ፡ የአጣጣልን ፡ ሕግ ፡ በመጠበቃቸው ፡ ብዙ ፡ የደኅንነት ፡ ተግባር ፡ ፈጽመዋል ።

አንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ ሰባኪዎች ፡ ስብከታቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ ካዘጋጁት ፡ ላይ ፡ መደዳውን፡ የማንበብ ፡ ልማድ፡ አላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሰባበክ ፡ ወይም ፡ አመራር ፡ በአብዛኞች ፡ ሰባኪዎችና ፡ በአድማጮች ፡ ዘንድ ፡ የተወደደና ፡ የሚስማማ ፡ አይደለም ። ጽሑፉ ፡ በሰባኪውና ፡ በአድማጮቹ ፡ መካከል ፡ እንደተጋረደ ፡ መጋረጃ ፡ ስለሚሆንና ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣንና ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ የሰባኪው ፡ ዓይን ፡ ከጉባኤው ፡ ሲለይ ፡ ስብከቱን፡ ፈጽሞ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ደካማ ፡ ያደርገዋል ። ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ የንግግር ፡ ጣዕምና ፡
የሰውነት ፡ እንቅስቃሴም ፡ ስለሚጐድልበት ፡ ነገሩ ፡ ስብ
ከት ፡ መሆኑ ፡ ይቀርና ፡ ንባብ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡
«የሰባኪው ፡ ሰውነት ፡ የአድማጮቹን ፡ ሰውነት ፡ ስቦ ፡
የሚያገናኝ ፡ ማግኔት ፡ ነው ፡» ሊባል ፡ ይቻላል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ተባለም ፡ በጽሑፍ ፡ የተዘጋጀው ፡
ስብከት ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ እንዲጠና ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤
አስፈላጊም ፡ አይሆንም ። ይህ ፡ ለሰባኪው ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡
ይሆንበታል ። በሕዝብ ፡ ፊት ፡ የመናገር ፡ ችሎታውንም ፡
ያጠፋበታል ። እንዲሁም ፡ የስብከቱ ፡ አመራርና ፡ አጣ
ጣል ፡ ሕይወት ፡ የሌለው ፡ አርቲፊሲዩል ፡ ሥራ ፡ ይሆንበ
ታል ። በአንዳንድ ፡ የአጋጣሚ ፡ ስብሰባ ፡ ጽሑፉን ፡ ማን
በብ ፡ ግዴታ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡
ዘወትር ፡ ሊሠራበት ፡ አይገባም ።

እንግዲህ ፡ በአብዛኞች ፡ ሰባኪዎች ፡ ዘንድ ፡ የተለ
መደ ፡ የስብከት ፡ ዘዴ ፡ ከማስታወሻው ፡ መስበክ ፡ ነው ።
ሰባኪው ፡ ከማስታወሻው ፡ የመስበክ ፡ ልማድ ፡ እንዲኖ
ረው ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ ለመስበክ ፡ መማር ፡ ያስፈል
ገዋል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ ከመሳትና ፡ በአንዳ
ንድም ፡ አንቀጽ ፡ ረጅም ፡ ንግግር ፡ ከማድረግ ፡ ይታገዳል ።
የዚህን ፡ ትምህርት ፡ በደንብ ፡ የተከታተለው ፡ እንደሆነ ፡
ሌላ ፡ የበለጠ ፡ የአመራር ፡ ዘዴ ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ የሚተች
በት ፡ ጉዳይ ፡ የለም ። አደራው ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።
በደብተር ፡ ላይ ፡ የሚያዘው ፡ ማስታወሻ ፡ የሰባኪውን ፡ ዓ
ይን ፡ እንዲማርክ ፡ ሆኖ ፡ በጉልህ ፡ መጻፍ ፡ እንደሚያስፈ
ልገው ፡ የሚያናግር ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የስ



ብከቱ ፡ አቋም ፡ ሕግን ፡ የተመረኰዘና ፡ የተስተካከለ ፡ ሆኖ ፡
በቃል ፡ የተጠና ፡ ከሆነ ፡ የማስታወሻውን ፡ ደብተር ፡ መ
ያዝ ፡ ግዴታ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እን
ደተባለው ፡ ዘወትር ፡ የስብከት ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡
ቦታ ፡ ለአንድ ፡ ሰባኪ ፡ ይህ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ይሆን
በታል ። አንዱን ፡ ዓይነት ፡ ስብከት ፡ በመደጋገም ፡ በልዩ ፡
ልዩ ፡ አትሮኖስ ፡ በሚያሰሙበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሊሆን ፡ ይች
ላል ። ሰባኪው ፡ ማስታወሻን ፡ ይዞ ፡ በሚሰብክበት ፡ ጊዜ ፡
በማስታወሻው ፡ እንደሚጠቀምበት ፡ ለአድማጮቹ ፡ ም
ልክት ፡ መስጠት ፡ አይገባውም ። ንግግርን ፡ በመሐል ፡
ማቋረጥ ፤ ድንገት ፡ አንገትን ፡ ድፍት ፡ አድርጎ ፡ ማስታወ
ሻውን ፡ አቀርቅሮ ፡ ማየት ፤ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ አድማጭን ፡
የሚያውክ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባም ። በስብ
ከት ፡ መሐከል ፡ የሚነጋገሩባቸውን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡
ጥቅሶች ፡ ሌሎችንም ፡ ሁሉ ፡ ሰባኪው ፡ ጠንቅቆ ፡ የሚያው
ቃቸውና ፡ ያለ ፡ ስህተት ፡ ሊያወሳቸው ፡ የሚችል ፡ መሆ
ኑን ፡ እርግጠኛ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መደባቸው ፡ እየተለየ ፡
በማስታወሻ ፡ ሊጻፍ ፡ ይገባል ። ሰባኪው ፡ በንግግሩ ፡ መሐ
ከል ፡ አንድ ፡ ጥቅስ ፡ ፈልጎ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡን ፡
ማስጠበቅ ፡ እጅግ ፡ የሚያስነቅፍ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ጥ
ቅሱም ፡ ቢቀር ፡ የተሻለና ፡ የማያጐዳም ፡ ነው ። አንድ ፡
ሰው ፡ ለስብከት ፡ ሥራ ፡ በታጨበት ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡
ስብከቱን ፡ ተሞላ ፡ ጐደል ፡ በጽሑፍ ፡ ይዞ ፡ ከዚሁ ፡ ው
ስጥ ፡ በንባብ ፡ ሳይሆን ፡ በንግግር ፡ ዘዴ ፡ ቢሰብክበት ፡
በጣም ፡ ጥሩ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ይህ ፡ ለወደፊቱ ፡ መልካም ፡
እርምጃን ፡ ያዘለ ፡ አመራር ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የሰባኪው
ንም ፡ አእምሮ ፡ በቃል ፡ ጥናት ፡ ከማድከም ፡ ያቀልለታል ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰባኪው ፡ ስብከቱን ፡ በጽሑፍ ፡ ያዘጋጀ ፡ ቢሆን
ም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአትሮኖሱ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ማንበብ ፡ ል
ማድ ፡ እንዳይሆንበት ፡ ቢፈልግ ፤ ጽሑፉን ፡ ወደ ፡ አትሮ
ኖሱ ፡ ከመውሰድ ፡ መታገስና ፡ በማስታወሻው ፡ ላይ ፡
ብቻ ፡ ቢወሰን ፡ የበለጠ ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሰባኪው ፡ የፈለገውንም ፡ የአሰባበክ ፡
ዘዴ ፡ ቢወስድ ፡ በሚሰብክበት ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ የንግግር ፡
ነፃነት ፡ እንዲያገኝ ፡ አስቀድሞ ፡ ስብከቱን ፡ ለራሱ ፡ ማሰ
ማት ፡ ግዴታው ፡ ነው ። ስብከት ፡ በሚመራበት ፡ ጊዜ ፡
ንግግርን ፡ አጥርቶ ፡ ለመናገር ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈ
ልጋል ። በስብከት ፡ ጊዜ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠውን ፡ ሐሳብ ፡
ከሁሉ ፡ በበለጠ ፡ አነጋገር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚቀበለን ፡
አድርገን ፡ ማቅረብ ፡ የሁላችን ፡ ተግባር ፡ ነው ። ዴሞስ
ቴን ፡ የተባለው ፡ ወጣቱ ፡ የግሪክ ፡ ተናጋሪ ፡ የቀድሞውን ፡
የተፈጥሮውን ፡ ጐደሎ ፡ አነጋገር ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ተጋ
ድሎና ፡ ሙከራ ፡ እንዳሸነፈውና ፡ እንደለወጠው ፤ በዓለም፡
ካሉት ፡ ታላላቅ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የበለጠ ፡ ተናጋሪ ፡ እንደሆ
ነም ፡ ስናስብ ፡ በጣም ፡ ይጠቅመናል ። የወንጌል ፡ ሰባኪ ፡
ከአንድ ፡ ትያትር ፡ ተጫዋች ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ተሚጋች ፡
ይልቅ ፡ ስለ ፡ ድምፁ ፡ ሁኔታ ፡ በበለጠ ፡ መንገድ ፡ ማሰብ ፡
አለበት ። የድምፅ ፡ ልምምድ ፡ ማድረግ ፡ በጣም ፡ ይጠቅ
ማል ፤ ድምፅን ፡ ለማረም ፡ ማለት ፡ ድምፅ ፡ የጠራ ፡ እንዲ
ሆን ፡ ለማለማመድ ፡ የሚረዱ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍቶች ፡ አሉ ።
እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ ገዝቶ ፡ በ፩ ፡ ክፍል ፡ ለብቻ ፡ ሆኖ ፡
ዓረፍተ ፡ ነገራቸውን ፡ እየጠነቀቁ ፡ ድምፅን ፡ ከፍ ፡ አድ
ርጎ ፡ ቢያነቡአቸው ፡ ድምፅ ፡ ይጠራል ፤ እንደ ፡ መቃልሕ ፡



ያስተጋባል ፤ አንደበት ፡ ይፍታታል ። በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡
አፍህ ፡ ቢኰላተፍ ፡ አትደንግጥ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የነበ
ረህን ፡ ድምፅና ፡ አንደበት ፡ አስቀድመህ ፡ አስተውለው ፤ በ
ዚህ ፡ መንገድ ፡ ስትከተል ፡ ነው ፡ የንግግርህ ፡ መሻሻል ፡
እርምጃ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ልትረዳው ፡ የምትችል ።
በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ለሚናገር ፡ ለአንድ ፡ ሰባኪ ፡ ጥሩ ፡ ድምፅ ፡
ሲኖረው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ በረከት ፡ ነው ። ተራ ፡ ድምፅም ፡
ቢሆን ፡ አጣጣሉ ፡ በሥርዓት ፡ ከሆነና ፡ ኮልታፋነት ፡ ከሌ
ለበት ፡ እጅግ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮች ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሰባኪውን ፡ ንግግር ፡ በቀላሉ ፡
ሊሰማው ፡ ይገባዋል ። ሰባኪው ፡ ድምፁን ፡ ዝቅ ፡ በማድ
ረጉ ፡ ምክንያት ፡ ከአድማጮቹ ፡ ሲሶው ፡ ሳይሰሙት ፡ በመ
ቅረታቸው ፡ ጥሩው ፡ ስብከት ፡ ተበላሽቶ ፡ እንደቀረ ፡ ብዙ፡
ጊዜ ፡ ሲነገር ፡ ተሰምቶአል ። እውነትም ፡ ስብከትን ፡ ለማዘ
ጋጀት ፡ የተደከመው ፡ ድካም ፡ ሁሉ ፡ የተሰበሰቡትን ፡
ሁሉ ፡ እንዲሰሙ ፡ ለማድረግ ፡ ካልተቻለ ፡ ጥቅሙ ፡ ምን
ድር ፡ ነው ? ሰባኪው ፡ አስቀድሞ ፡ ከለመደበት ፡ የስብከት ፡
ቦታ ፡ ሰፊ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ለመስበክ ፡ ሲቀርብ ፡ ዓይ
ኖቹን ፡ እኋላ ፡ ወደ ፡ ተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ማሳረፍ ፡
አለበት ። ምናልባት ፡ አሁንም ፡ ሊሰሙት ፡ ባይችሉ ፡ ድም
ፁን ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ፡ ግድ ፡ ይሆንበታል ። ከሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ አድማጮቹን ፡ የሚያስቅቅና ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቈ
ርጥ ፡ ደግሞ ፡ ተናጋሪው ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ የዓረፍተ ፡
ነገሮቹን ፡ መቆሚያ ፡ ቃላት ፡ በላላ ፡ ድምፅ ፡ የዘጋና ፡
ሳይሰሙት ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ስለተባለም ፡ ሰባኪው ፡ አድማጮቹ ፡ እንዲሰሙት ፡ ሲል ፡ መጮህ ፡ የለበትም ። አንድ ፡ ሊቅ ፡ እንዳለ ፡ «በጣም ፡ ጮኸው ፡ ቢናገሩት ፡ በቀላሉ ፡ ተሰሚነት ፡ አያገኝም ፤ ሰባኪው ፡ ጮኾ ፡ የተናገረ ፡ እንደሆነ ፣ ጉሮሮውን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የሚጎዳው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአድማጮቹ ፡ ሕዋሳት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ገብቶ ፡ ያጋጫቸዋል ፡ ያበሳጫቸዋል ።» አጥርቶ ፡ መናገር ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደማንበብ ፡ ይቈጠራል ፡ ቢባል ፣ ሐሰት ፡ አያሰኝም ። ጥርት ፡ አድርጎ ፡ መናገር ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ እንደማሰብ ፡ ያህል ፡ ነው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ መጠንቀቅ ፡ የተናጋሪው ፡ ተግባር ፡ ነው ።

የንብ ፡ ድምፅን ፡ አስወግድ ፣ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምፅ ፡ በመለማመድ ፡ ይገኛል ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰባኪ ፡ ስለዚህ ፡ ክፍል ፡ ሲያስረዳ ፡ «ድምፅህን ፡ ለጉዳይህ ፡ እንዲስማማ ፡ አድርገው ፤ ያምርብኛል ፡ ብለህ ፡ አርቲፊሲዬል ፡ ድምፅ ፡ አታድርግ ፤ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በተፈጥሮህ ፡ ቀጥተኛ ፡ ሁን፡ እንጂ ። ድምፅህን ፡ በየጊዜው ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ እያደረግህ ፡ ለዋውጠው ፣ እንደ ፡ አየራት ፡ ሁን ፤ ፀሐይ ፣ በረዶ ፣ ዝናብ ፡ ይኑርብህ ፤ ወዲያውም ፡ ብራ ፡ ይሁን ፤ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ይኑርብህ ፡ ከጉም ፡ በተቀር ፡» ይል ፡ ነበር ።

የሰባኪው ፡ አነጋገር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ፍጥነት ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ? ችኩል ፡ አነጋገር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከወጣቶች ፡ ነው ፡ የሚሰማው ። ሆኖም ፣ በእነርሱ ፡ ብቻ ፡ አልተወሰነም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ችኩልነት ፡ የሚደርሰው፡ በግልፍተኛነት ፡ ነው ። መሪው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፣ ተናጋሪው ፡ አጥርቶ፡ ለመናገር ፡ እቻለ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ንግግ



ሩን ፡ ማፍጠን ፡ ይገባዋል ። ሰባኪው ፡ አንዳንድ ፡ ቃል ፡ ሲያመልጠውና ፡ ተመልሶ ፡ ሲደግመው ፡ የተሰማ ፡ እንደሆነ ፤ ችኩሎ ፡ የመናገሩ ፡ ምልክት ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰባኪ ፡ ሊታሰብባቸው ፡ የሚገባቸውን ፡ ሐሳቦች ፡ አቅርቦ ፡ እንደሆነ ፡ ችኩሎ ፡ መናገር ፡ አይገባውም ። ችኩሎ ፡ ቢናገር ፡ ግን ፡ የራሱን ፡ ዓላማ ፡ እንደማፍረስ ፡ ይሆንበታል ። ወይም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ምግቡን ፡ ሲበላ ፡ አንዳንዱን ፡ ጉርሻ ፡ እያኘከ ፡ እንዲውጥ ፡ ከማድረግ ፡ ፈንታ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰለቅጠው ፡ ማስገደድና ፡ መጨረሻው ፡ ከጉሮሮው ፡ እንደማይወርድለት ፡ ያህል ፡ ነው ።

ስለ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጉዳይ ፣ ዋናው ፡ ነገር ፡ የራስን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሁኔታ ፡ መከተል ፡ ነው ። እንቅስቃሴና ፡ ውዝዋዜ ፡ አስገዳጅ ፡ ጉዳዮች ፡ አይደሉም ። እንዲያውም ፡ አንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ ሰባኪዎች ፡ ጨርሰው ፡ ትተውታል ። ሰውነትን ፡ ማወዛወዝ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ደንበኛ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፤ በተቀረስ ፡ አጉል ፡ ሳቅን ፡ ያስከትላል ። ለምሳሌ ፡ ለስላሳ ፡ ሰሞታ ፡ ወይም ፡ ምክር ፡ በማቅረብ ፡ ጊዜ ፡ ጡጫ ፡ በማሳየት ፡ ኃይል ፡ እንዲያገኝ ፡ ማድረግ ፡ አግባብ ፡ አይደለም ። የሰባኪው ፡ ባሕርይ ፡ የተቀደሰና ፡ ተስማሚ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የአንድ ፡ ሊቅ፡ ንግግር ፡ ለሰባኪዎች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማቸዋል ። «በስብከት ፡ ጊዜ ፡ ራስን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ማንጋጠጥ ፡ አይገባም ፤ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መደፋት ፡ በደረት ፡ ላይ ፡ እንደተተከለ ፡ አቀርቅሮ ፡ ማጐንበስ ፤ ወደ ፡ ግራ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ማጋደል ፡ ከቶ ፡ አይገባም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደንበኛውን ፡ አቀማመጥ ፡ እንደያዘ ፣ በትክክልና ፡ በየዋህ ፡ አቋ



www.ethiopianorthodox.org

ቋም ፡ መሆን ፡ ነው ። ደግሞም ፡ ሰውነትን ፡ እንደ ፡ ሐውልት ፡ እንዳይንቀሳቀስ ፡ ማድረግና ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሰዓት ፡ ማንቀሳቀሻ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ማወዛወዝ ፡ አይገባም ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለማስወገድ ፡ አንድ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ በዝግታ ፡ ሰውነትን ፡ ማጋደል ፡ (ማዘንበል ፡) አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ጉባኤው ፡ መሐል ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቀጥ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።»

የዕለት ፡ ጥቅሶችን ፡ በመፈለግ ፡ ጊዜ ፡ እንዳያልፍ ፡ በተፈላጊው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ደማቅ ፡ ምልክቶች ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የመጽሐፉን ፡ ቅጠሎች ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፡ ማገላበጥ ፡ ወይም ፡ ጣትን ፡ ምራቅ ፡ እያስነኩ፡ መግለጥ ፡ አድማጮችን ፡ እጅግ ፡ ያሰቅቃቸዋል ። የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ አያያዝና ፡ አገላለጥ ፡ ማሳመር ፡ ለስብከቱ ፡ ውበት ፡ ይጨምርለታል ።

በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ ተናጋሪ ፡ ወደ ፡ ጉባኤው ፡ ፊት ፡ መመልከት ፡ አለበት ። ልማድ ፡ ያለው ፡ ተናጋሪ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ኃይል ፡ እንዳለው ፡ ያውቃል ። ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተነገረው ፡ ማስታወሻ ፡ የሚይዝ ፡ ሰባኪ፡ በእርሱና ፡ በአድማጮቹ፡ መካከል፡ ማስታወሻው ፡ አንድ ፡ ግርዶሽ ፡ እንዳይሆን ፡ በማሰብ ፡ በቅጽበት ፡ አየት፡ አድርጎ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ለማንበብ ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፡ ከማስታወሻው ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ መዛመድ ፡ ያስፈልገዋል ።

አንድ ፡ ሰባኪ ፡ በአንድ ፡ ስብሰባ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በሚነጋገርበት ፡ ጉዳይ ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ መታየት ፡ አለበት ።



ምዕራፍ ፡ ዘጠኝ ።

# ሰባኪው ፡ እንደ ፡ ተማሪ ።

ለማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ ጥብቅ ፡ ዝግጅት ፡ ካልተደረገለትና ፡ በብዙ ፡ ካልተደከመበት ፡ ነዋሪና ፡ ዘላቂ ፡ ክንውን ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ የሚቻለው ፡ በወንጌል ፡ መልእክተኞች ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ሥራ ፡ ባለበት ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛነት ፡ መልእክተኛው ፡ አብዛኛው ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ ሕዝቦቹን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ጉብኝት ፡ በመጐብኘት ፡ ነው ። ይህ ፡ የመጐብኘት ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ በአነስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ልንዘረዝረው ፡ አንችልም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግረ ፡ መንገዳችንን ፡ ልንጠቅሰው ፡ የሚያሳስበን ፡ ከአሁኑ ፡ ክፍላችን ፡ ጋር ፡ የተያያዘውን ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ በታማኝነት ፡ የሚሆን ፡ መንፈሣዊ ፡ ጉብኝት ፡ ከመልእክቱ ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ፍሬ ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለወንጌል ፡ መልእክተኛው ፡ በዚህ ፡ በጉብኝቱ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ለስብከት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ሊገጥሙት ፡ እንደሚችል ፡ ለመግለጽ ፡ ያህል ፡ ነው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ለማመልከት ፡ የፈለግነው ፡ ዓይነተኛው ፡ ጉዳይ ፡ ጊዜን ፤ ለጥናት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ያህል ፡ እንዲሁም ፡ ለቤት ፡ ማለት ፡ ለትዳር ፡ ለሌላም ፡ ለልዩ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ልዩ ፡ ቀጠሮዎች ፡ እንደሚበቃ ፡ አድርጎ ፡ በጥንቃቄ ፡ መከፋፈልና ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ማካሄድ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ለማሳሰብ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሊቅ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሲናገር ፡ «በቀን ፡ ውስጥ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ለንባብ ፤ ለጥናትና ፡ ለጽሕፈት ፡ ሥራ ፡ የተቀደሰ ፡ አድርጎ ፡ መወሰን ፡ ያስፈልጋል ፡» ይላል ። ይህ ፡ በተለይ ፡ የሚጠቅመው ፡ በየሰንበት ፡ ቀን፡ ሁለት ፡ ስብከቶችና ፡ በሳምንትም ፡ ሌሎች ፡ ንግግሮችን ፡ ለሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ለሚደረጉት ፡ ስብከቶችና ፡ ንግግሮች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ለንባብና ፡ ለጥናት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጊዜ ፡ መመደብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ።

መቸም ፡ ቢሆን ፡ የሰባኪው ፡ ታላቁ ፡ መጽሐፍ ፡ «መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡» ነው ። ሆኖም ፤ ይህንን ፡ በሙሉ ፡ መርምሮ ፡ ሊያጠናው ፡ ከቶ ፡ አይችልም ። ይህም ፡ ስለተባለ ፡ ደግሞ ፡ ሕዝቦቹ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲያውቁት ፡ ማስተማር ፡ ተግባሩ፡ ነው ። በውስጧ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምርመራ ፡ ትምህርት ፡ ያለባት ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛነት ፡ ዘወትር ፡ ብርቱና ፡ ፍሬያማ ፡ እንደሆነች ፡ ትኖራለች። የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ትምህርት ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ እንዲሆን ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ለጸሎት ፡ ጉዳይ ፡ አዘውትሮ ፡ በማንበብ ፡ ከሚደረገው ፡ ድካም ፡ ሌላ ፤ አንድ ፡ የወንጌል፡ መልእክተኛ፡ በጥሩ፡ ጥሩ ፡ ታሪኮች ፡ እየተረዳ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ቢያጠና ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ይጠቀምበታል ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጥናት ፡ ለአትሮኖስ ፡ የሚገቡ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ስብከቶች ፡ ለማፍ



ራት ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ በተቀር ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀት ፡ ለመመስረት ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ አገላብጦ ፡ ከማጥናት ፡ የበለጠ ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የለም ።

መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በመደዳ ፡ ማንበብና ፡ መመርመሩ ፡ በተለይ ፡ ለስብከት ፡ ጉዳይና ፡ አእምሮን ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እውቀት ፡ ለመሙላት ፡ በጣም ፡ ይረዳል ። አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ከዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በቀን ፡ ፲፬ ፡ ምዕራፎች ፡ እያነበበ ፡ በዓመት ፡ ከአራት ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ይዘልቀው ፡ እንደነበረ ፡ ይነገራል ።

እንዲሁም ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛው ፡ በታማኝነት ፡ ያጠና ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ በስብከቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ አዲስ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ብርቱዎች ፡ ምዕመናኖች ፡ በማግኘት ፡ ጠንካራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሥራት ፡ የሚቻል ። ብዙ ፡ ሰባኪዎች ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊነታቸውን ፡ ችላ ፡ ስለሚሉት ፡ የመልእክተኛነታቸው ፡ ውጤት ፡ በጣም ፡ አሣዛኝ ፡ ይሆንባቸዋል ። ብዙ ፡ ሰባኪዎች ፡ በረጃጅምና ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዞአቸው ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ሕይወታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በማጥናት ፡ ያለፉ ፡ አሉ ። እንዲሁም ፡ ብዙዎቹ ፡ በተደራቢ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ሳያነቡ ፡ የማይውሉ ፡ አሉ ። ይህ ፡ ሲሆን ፤ ታላላቅ ፡ ሰባኪዎች ፡ የተባሉ ፡ ሁሉ ፡ ታላላቅ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አዋቂዎች ፡ እንደሆኑ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ መጻሕፍቶችና፡ ብራናዎችን ፡ እንዲያመጣለት ፡ ይለምነዋል ። (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ፡) ያያቸው ፡ የሚያስደንቁት ፡ ራእዮችና ፡ የተቀበ



www.ethiopianorthodox.org

ለው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ቦታ ፡ ሊወስዱ ፡ አልቻሉም ። ስለዚህ ፡ ለክርስቲያን ፡ መልእክተኞች ፡ ሁሉ፡ ታላቅ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ። እግዚአብሔር ፡ የሚባርከው ፡ መልእክተኛነት ፡ በትጋትና ፡ በጥንካሬ ፡ የሚሠራውን ፡ ሰው ፡ አገልግሎት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ።

በተቻለ ፡ መጠን ፡ ከመበሳጨትና ፡ ከመታወክ ፡ ራስህን ፡ መጠበቅ ፡ ያስፈልግሃል ። ለምሳሌ ፡ ለንባብና ፡ ለጥናት ፡ በወሰንከው ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ባለ ፡ ጉዳዮች ፡ ቢመጡብህ ፡ አትፍቀድላቸው ። የወንጌል ፡ መልእክተኛው ፡ ሚስት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የማጥኛ ፡ ክፍሉን ፡ መዝጊያ ፡ በመጠበቅ ፡ በጣም ፡ ልትረዳው ፡ ትችላለች ። ባለ ፡ ጉዳዮችም ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኛው ፡ ጊዜውን ፡ ለታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያውለው ፡ እንደሆነ ፡ ሲያውቁ ፡ እነርሱም ፡ ጊዜያቸውን ፡ እንደዚሁ ፡ ለታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ለማዋል ፡ ይማራሉ ።

---



ምዕራፍ ፡ አሥር ።

## የአደባባይ ፡ ስብከት ።

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ስናስብበት ፡ የቆየነው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ወይም ፡ በትምህርት ፡ ቤቶች ፤ ይኸውም ፡ በሙሉም ፡ ቢሆን ፡ በከፊል ፤ የክርስቲያን ፡ ስብሰባ ፡ በሚሆንበት ፡ ቦታ ፡ ለሚደረገው ፡ ስብከት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ በውጭ ፡ በአደባባይ ፡ ለሚደረገው ፡ ስብከት ፡ የተመደቡ ፡ አሉ ። ይህም ፡ በክርስቲያኖች ፡ መሰብሰቢያ ፡ ከሚደረገው ፡ ስብከት ፡ በጉዳዩና ፡ በአቀራረቡ ፡ እጅግ ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ ምዕራፍ ፡ ስለዚሁ ፡ በመግለጽ ፡ እንነጋገርበታለን ።

በአደባባዮች ፡ የሚደረጉ ፡ ስብሰባዎች ፡ በታላላቅ ፡ መንገዶችና ፡ በሜዳዎችም ፡ ቢሆኑ ፡ ክርስትና ፡ ላልተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ስለሆነ ፡ የስብከቱ ፡ አቀራረብ ፡ በሰፊው ፡ የሚለያይበት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ከክርስቲያኑ ፡ ሰባኪ ፡ አስተያየት ፡ የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ሊጠቃለል ፡ ይቻላል ።

፩ ፡ በአደባባይ ፡ የሚሰበሰቡ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለማየት ፡ ከመንገዳቸው ፡ ጐራ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ከቤታቸው ፡ አስበውበት ፡ የሚመጡ ፡ አይደሉም ። ስለ ፡ ሰባኪውና ፡ ወይም ፡ ስብከቱን ፡ ስለሚጀምርበት ፡ መግቢያ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ምን ፡ ይሆን ፤ በማለት ፡ የሚገደዱበት ፡ አንድም ፡ ሐሳብ ፡ የላቸውም ። ክርስትናንም ፡ ይቃወሙ ፡ ይሆናል ፤ አብዛኞቹም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያላቸው ፡ ግዳጅ ፡ እምብዛም ፡ ነው ። በእነርሱ ፡ ፊት ፡ የሚታየው ፡ ሕዝቡ ፡ ለምን ፡ ተሰብስቦ ፤ እኔስ ፡ ለምን ፡ ይቀርብኛል ፡ በማለት ፡ ለረጅም ፡ ቢሆን ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ቆሞ ፡ ሁኔታውን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ደራሽ ፡ ጐርፍ ፡ ያልፉል ።

፪ ፤ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ትንሽ ፡ እውቀት ፡ ይኖራቸው ፡ ይሆናል ። አንዳንዶቹም ፡ በክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ያገኙት ፡ ትንሽ ፡ ብልጭታ ፡ ይኖራቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰባኪው ፡ በአደባባይ ፡ ለሚያደርገው ፡ ስብከቱ ፡ ለዚህ ፡ ለጥቃቅን ፡ ነገር ፡ ማሰብ ፡ የለበትም ።

፫ ፤ ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ስለ ፡ ቴዎሎጊ ፡ ቃላት ፡ ትንሽ ፡ ማስተዋል ፡ ይኖራቸዋል ። እንዲሁም ፡ ያንዳንዱን ፡ ትርጓሜ ፡ በተሳሳተ ፡ በራሳቸው ፡ መንገድ ፡ ያስኬዱታል ። ለምሳሌ ፤ ቅድስናን ፡ ከቅዳሴ ፤ መልካምን ፡ ከባለ ፡ ሙያ ፤ ክፋትን ፡ ከስሕህተት ፡ ጋር ፡ በማቀናበር ፡ ያቀላቅሉታል ። ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ስሕተት ፡ እንዳይሆን ፡ መጠበቅ ፡ ያስፈልጋል ።

፬ ፤ ብዙዎች ፡ በኃጢአት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለእነርሱ ፡ ትንሽ ፡ ስሕተት ፡ ይመስላቸዋል ። ይህም ፡ በእነርሰው ፡ ሃይማኖት ፡ ይፈቀድ ፡ ወይም ፡ አይፈቀድ ፡ ይሆናል ። ሁሉም ፡ በከንቱ ፡ አምልኮና ፡ በስሕተት ፡ የተቀበ ፡ ናቸው ።



፭ ፤ ጥቂቶቹም ፡ ስለ ፡ ራሳቸው ፡ ሃይማኖት ፡ ጥሩ ፡ እውቀት ፡ ይኖራቸዋል ። ክርስቲያኖች ፡ ያልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በተሰበሰቡበት ፡ መሐል ፡ እነዚህ ፡ ጥቂቶች ፡ እንደሚገኙ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰባኪው ፡ ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ የየትኛው ፡ ወገን ፡ እንደሆኑ ፡ ቢያውቅ ፡ ለስብከቱ፡ የሚሆን ፡ ትልቅ ፡ መረማመጃ ፡ ያገኛል ።

አሁን ፡ በአደባባይ ፡ ስለሚደረገው ፡ ስብከት ፡ አጥብቀን ፡ ልናስብበት ፡ የምንፈልገው ፡ ዋና ፡ ነገር ፤ ይህ ፡ የአደባባይ ፡ ስብከት ፡ የታመነ ፡ እውነተኛ ፡ ድካምና ፡ ምርመራ ፡ በማድረግ ፡ በታላቅ ፡ ጸሎት ፡ መዘጋጀት ፡ እንደሚገባው ፡ ነው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ነው ፡ ብዙዎች ፡ ሰባኪዎች ፡ ቸል ፡ የሚሉት ። ሰባኪዎች ፡ ሁሉ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሚያደርጉት ፡ ስብከታቸው ፡ ይብዛም ፡ ይነስም ፡ ሳይዘጋጁ ፡ አይቀሩም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙዎች ፡ ለአደባባይ ፡ ስብከታቸው ፡ እጅግም ፡ አይዘጋጁለትም ። የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ውጤት ፡ ብዙ ፡ ነገርና ፡ ስሞታም ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፤ የሚመነጥቁ ፡ ንግግሮች ፡ ግን ፡ አስቀድመው ፡ ባለመዘጋጀታቸው ፤ በመጨረሻው ፡ ድካማቸው ፡ ሁሉ ፡ ውጤቱ ፡ እጅግ፡ ያነሰ ፡ ወይም ፡ ያለአንዳች ፡ ፍሬ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

ሰባኪዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ እንደሚበዛባቸውና ፡ ስብከታቸውን ፡ የሚያዘጋጁበት ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ እንደሚቸገሩ ፡ አይካድም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ዋናውን ፡ ጊዜ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ሳንዘነጋና ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑንም ፡ ብናስብበት ፤ እንዲሁም ፡ የአደባባይ ፡ ስብከት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሚደረገው ፡ የቀለለና ፡ ነገሩም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ አድ



www.ethiopianorthodox.org

ማጬች ፡ የሚደረግ ፡ በመሆኑ ፡ በማናቸውም ፡ አቋሙና ፡ አመራሩ ፡ የጠበቀ ፡ ስለማይሆን ፡ ለዚህ ፡ ለገራገር ፡ ተግባር ፡ እጅግ ፡ መጠበብ ፡ አያስፈልግም ፡ የሚሉት ፡ ሐሳብ ፤ የአደባባይ ፡ ስብከትን ፡ ፍሬ ፡ ከሚቀንሱት ፡ ዓይነተኛ ፡ ምክንያቶች ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። ሰባኪው ፡ በሚገምተው ፡ መጠን ፡ ከፍተኛውን ፡ ቦታ ፡ መያዝ ፡ አለበት ። በአደባባይም ፡ ቢሆን ፡ በአትሮኖስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከምናቀርበው ፡ የበለጠ ፡ ስጦታ ፡ ላይ ፡ መቀነስ ፡ አይገባንም ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ በሥርዓቱ ፡ እንዲከናወን ፡ ማድረግ ፡ ነው ። አለዚያስ ፡ ጨርሶ ፡ ያለመሞከሩ ፡ ይሻላል ።

ለዚህ ፡ ለልዩ ፡ ሥራ ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ስብከትን ፡ ማዘጋጀት ፡ ያስፈልጋል ። ይኸውም ፡ ፩ ፤ በተለይ ፡ ሊሰበክበት ፡ ለተፈለገ ፡ ጉዳይ ፡ ማለት ፡ ለደንበኛ ፡ ስብከት ፡ በሚደረገው ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ ዝግጅት ። ፪ ፤ ሰባኪው ፡ አከታትሎ ፡ ስብከቱን ፡ የሚያሰማቸው ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖታቸው ፡ እውቀት ፡ እያደገ ፡ በሚሄድበት ፡ መጠን ፡ ተከታታይና ፡ ጠቅላላ ፡ ዝግጅት ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ዓይነተኛ ፡ ነጥቦችን ፡ ሰፋ ፡ አድርገን ፡ በመዘርዘር ፡ እንመልከታቸው ።

፩ ፤ ለአደባባይ ፡ ስብከት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዝግጅት ፡ በጣም ፡ መመራመር ፡ ያስፈልገዋል ፡ ስንል ፡ ለደንበኛው ፡ አትሮኖስ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ ስብከትን ፡ በጽሑፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለታችን ፡ አይደለም ። ሰባኪው ፡ ለሐሳቡ ፡ ድጋፍ ፡ እንዲሆንለት ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ማስታወሻዎችን ፡ ቢይዝ ፡ ስንኳ ፡ እነርሱን ፡ በመመልከት ፡ ንግግሩን ፡ ማቆም ፡ እንደማያስፈልገው ፡ አድርጎ ፡



ሊያስታውሰው ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፡ ካላጠናው ፡ በቀር ፡ በአደባባዩ ፡ ማስታወሻውን ፡ ሊይዝ ፡ አይገባም ።

የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ክፍል ፡ መርጦ ፡ መስበክ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ለሌሉበት ፡ ስብሰባ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ታሪክ ፤ የምሳሌ ፡ ትምህርት ፤ ስለ ፡ ተአምራት ፤ ስለ ፡ ድንገተኛ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስረዱ ፡ ትምህርቶች ፡ የበለጡ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ክፍል ፡ ለማብራራት ፡ ሲፈለግ ፡ ለትምህርቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጉዳይ ፡ ለሰሚው ፡ እንዲገባው ፡ በክፍል ፡ በክፍሉ ፡ መመደብ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ በአደባባይ ፡ ስብከት ፡ ደግሞ ፡ ሰባኪው ፡ አድማጮቹ ፡ እንዲያስታውሱለት ፡ ወይም ፡ በአእምሮአቸው ፡ እንዲቀረጽ ፡ አድርጎ ፡ ለመስበክ ፡ እንዲቻለው ፡ በጥንቃቄና ፡ በማስተዋል ፡ አስቦ ፡ ሊወጋበት ፡ የሚፈልገውን ፡ ነጥብና ፡ አቀራረቡን ፡ በበለጠ ፡ ሁኔታ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለበት ። እንደዚሁም ፡ ለአንድ ፡ ደንበኛ ፡ ስብከት ፡ እንደሚደረገው ፡ ስሞታ ፡ ወይም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በተለየ ፡ ሰባኪው ፡ ሲነጋገርበት ፡ ስለቆየው ፡ ስለ ፡ ዓይነተኛው ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉዳይ ፡ መሆን ፡ አይገባውም ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ ችላ ፡ እየተባለ ፡ የሚታለፍ ፡ ግልጽ ፡ ነገር ፡ መሆኑንም ፡ ለመሰወር ፡ አይቻልም ። ይህን ፡ በብዙ ፡ ስብሰባና ፡ ስብከት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ያስከተለውን ፡ ስህተት ፡ እንደገና ፡ መደጋገሙ ፡ ደግሞ ፡ እባስ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መውደቅ ፡ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

በአደባባይ ፡ ለሚደረገው ፡ ስብከት ፡ መግቢያው ፡ ቀደምትነት ፡ ያለው ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠብ ፡ ስለሚነሣ ፡ ይህንን ፡ በግልጽ ፡ በማስረዳት፡ ወይም ፡ ነገሩን ፡ በመተው ፡ ማሸነፍ ፡ ያስፈልጋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መጠራጠር ፡ አለ ። ሰባኪውም ፡ ሁልጊዜ ፡ ራሱን ፡ እንደሚመለከትና ፡ ለስብሰባውም ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንደሚያስብ ፡ በአድማጮቹ ፡ ዘንድ ፡ እንደዚሁ ፡ አይደለም ።

በፈገግታና ፡ ፊትን ፡ አብርቶ ፡ መቅረብ ፡ አስፈላጊ፡ ነው ። የምንሰብከውም ፡ ወንጌል ፡ ይህን ፡ ይጠይቃል ። በሌላ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃይማኖት ፡ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ ህንዶችን ፧ እስላሞችን ፡ ስናገኝ ፡ ሃይማኖታችሁን ፡ እናከብራለን ፡ ብንላቸው ፡ አንድም ፡ ጉዳት ፡ አያመጣብንም ። በስብከት ፡ ጊዜ ፡ የሰባኪው ፡ ሃይማኖት ፡ ኃይል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የነፍስ ፡ ደህንነት ፡ እንደሚያስገኝ ፡ ብቻ ፡ ማስረዳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማንንም ፡ ሃይማኖት ፡ መስደብ ፡ አይገባም ። የወንጌል ፡ ሰባኪ ፡ ሁልጊዜና ፡ ሁለመናው ፡ የሕዝብ ፡ ወዳጅ ፡ ነው ፧ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ ወዳጅነትም ፡ አሸናፊ ፡ የለም ። ክርስቲያኖች ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥንቁቅና ፡ ታማኞች ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። በድሮ ፡ ዘመን ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገባ ፡ ይታዩ ፡ እንዳልነበረ ፡ መሰወር ፡ አይቻልም ። አንድ ፡ ሊቅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል፡ ጽፎአል ፡ «ያላመኑትን፡ ለማሳመን ፡ ከቅንዓት ፡ የበለጠ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ያስፈልጋል ። ፈሪሳውያን ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ቅንዓት ፡ ነበራቸው ። ከሃይማኖቱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ የገባውን ፡ አንዱን ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ቀር



በን ፡ ለማነጋገር ፡ የምንችልበት ፡ መንገድ ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ በእርሱ፡ቦታ ፡ ስንገኝ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ሃይማኖታችንን ፡ ለመለወጥ ፡ ደስ ፡ አይለንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እውነትን ፡ ለመቀበል ፡ ደግሞ ፡ ዝግጁዎች ፡ ነን ። ሆኖም ፧ እኔ ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አውቃለሁ ፧ እናንተ ፡ የተናገራችሁትም ፡ ሁሉ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ በግልጽና ፡ በድፍረት ፡ የሚናገረን ፡ ደግሞ ፡ ከእኛ ፡ ጥቅም ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። የራሱን ፡ ታላቅነት ፡ በማጋነንና ፡ የቀድሞ ፡ አያቶቻችንን ፡ በመናቅና ፡ በመንቀፍ ፡ የሚቀርበን ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ለመግባባት ፡ ከተፈለገ ፡ ሁኔታውን ፡ ጨርሶ ፡ መለወጥ ፡ አለበት ፤ ከእኛም ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ የወንድማማችነት ፡ መደብ ፡ መቆም ፡ አለበት ፤ ያደረግነውን ፡ ሁሉ ፡ ለማወቅ ፡ ተጨንቆ ፡ መመራመር ፡ አለበት ፤ ቋንቋችንን ፡ መናገር ፧ ዜማችንን ፡ ማስተዋል ፧ ጥሩ ፡ ጥሩዎቹን ፡ መዝሙሮቻችንን ፡ ማዜም ፤ ታላላቅ ፡ መጻሕፍቶቻችንን ፡ ማንበብ ፤ ያለፈውን ፡ ሁኔታችንን ፡ ማክበር ፤ ፍልስፍናችንን ፡ ማስተዋል ፤ በመሠረተ ፡ ሐሳባችን ፡ መደሰት ፤ የኑሮዋችን ፡ መቋቋሚያ ፡ የሆኑትን ፡ መሠረታዊያን ፡ ፍጥረቶቻችንን ፡ መውደድ ፤ አለበት ። እኛንም ፡ ማክበርና ፡ ማፍቀር ፡ አለበት ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከእኛ ፡ የበለጠ ፡ ታላቅነት ፡ ካለው ፤ የሚያስተጋባው ፡ አዲስ ፡ እውነት ፡ ካለው ፧ ወይም የሚያስተላልፈው ፡ አዲስ ፡ ኃይል ፡ ካለው ፤ መሪያችን ፡ እንዲሆን ፡ በደስታ፡ እንቀበለዋለን ። እርሱም፡ የሕይወትን፡ ሥር ፡ የሚያረጥብና ፡ የሚያረካ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያና ፡ እንደ ፡ መጨረሻ ፡ ዝናብ ፡ ይሆናል ። እርሱም፡ ሕዝቡን ፡ በእርሾው ፡ የሚለውጥ ፡ በጣም ፡ ብርታት ፡ ያለውን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ኃይል ፡ ሊያንቀሳቅስ ፡ ይጀምራል ። በአንድ ፡ ቀንም ፡
አንድ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ እንደሚፈጠር ፡ ይመስላል ።»
ሊቁ ፡ ጽሑፉን ፡ በመቀጠል ፡ «ክርስትና ፡ ያልተቀበሉ
ትን ፡ ሕዝብ ፡ ሃይማኖት ፡ በትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ እስከምን
መለከትላቸው ፡ ድረስና ፡ እንዲሁም ፡ መሠረቱ ፡ ከድን
ቁርና ፡ ብዛት ፡ በሆነው ፡ አሁን ፡ ነግሦ ፡ በሚታየው ፡ የን
ቀት ፡ መንፈስ ፡ ፋንታ ፤ መልካም ፡ አስተያየትና ፡ አክብ
ሮት ፡ ፍቅርም ፡ በቦታው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፤ እነዚህን ፡
ሰዎች ፡ ልንጠቀምባቸው ፡ ከቶ ፡ አንችልም ፡» ይላል ።

ክርስቲያን ፡ ሰባኪ ፡ ለእርሱ ፡ ለራሱ ፡ ሊያደርጉ
ለት ፡ እንደሚወድ ፡ እርሱም ፡ ለሌሎች ፡ እንደዚሁ ፡ ማድ
ረግ ፡ ይገባዋል ። ይህም ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡
በሃይማኖትም ፡ ጭምር ፡ ነው ። የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ ከሁሉ ፡
የበለጠና ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ በግብር ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡
ሕጋዊ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

፪ ፤ ክርስትና ፡ ከሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ እንደ ፡
ልብ ፡ ለመነጋገር ፡ እንዲችል ፡ አንድ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰባኪ ፡
ከዚያው ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡ በጣም ፡
መተዋወቅ ፡ ያስፈልገዋል ። ክርስትና ፡ ላልተቀበለ ፡ ሰው ፡
የክርስትና ፡ ወንጌል ፡ እንዲገባውና ፡ እንዲቀበል ፡ አድር
ገህ ፡ ልታቀርብለት ፡ ስትፈልግ ፤ ቋንቋውን ፡ ለማወቅ ፡
እንዳስፈለገህ ፡ ሁሉ ፤ እንደዚሁም ፡ ሃይማኖቱንና ፡ ልዩ ፡
እምነቱን ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ዘመን ፡
ያሉት ፡ የክርስቲያን ፡ ሰባኪዎች ፡ ክርስትና ፡ የሌላቸው ፡
ሰዎች ፡ መንፈሳዊ ፡ እምነት ፡ የሚያስተውሉበት ፡ እውቀ
ታቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ስብከታ



ቸውን ፡ በመስቀልኛ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ በማቅረባቸው
ለድካማቸው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ መልስ ፡ አያገኙበትም
ወይም ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ይሆናል ። ለዚህ ፡ መሪ ፡ የሚሆ
ነው ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ ወደ ፡ አሕ
ዛብ ፡ በጻፉቸው ፡ ቃላት ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ ነው ፤ አይሁ
ድንም ፡ እጠቅም ፡ ዘንድ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ አይ
ሁዳዊ ፡ ሆንኩ ፡ . . . . . . . . . . . በሁሉ ፡ መንገድ ፡
አንዳንዶቹን ፡ አድን ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉ ፡ ጋር ፡ በሁሉ ፡ ነገር ፡
እንደ ፡ እነርሱ ፡ ሆንኩ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፳-፳፪ ፡) ቅዱስ ፡
ጳውሎስ ፡ ከክርስቲያን ፡ መሠረተ ፡ ትምህርቱ ፡ አንዳችም ፡
አላጐደለም ፡ ወይም ፡ ወደየትም ፡ አላዘነበለም ፤ ነገር ፡
ግን ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ እንዲግባባና ፡ ለመስበክም ፡ እንዲ
መቸው ፡ ሲል ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ ወዳለው ፡ ሰውና ፡ ሕግ ፡
ወደ ፡ ሌለው ፡ ሰው ፡ ስፍራ ፡ በደስታ ፡ ራሱን ፡ አኖረ ።
እርሱም ፡ የነዚያን ፡ አቋም ፡ ለማስተዋል ፡ ፈለገ ። ምክን
ያቱም ፡ የክርስቶስን ፡ መሠረትነትና ፡ አቅዋምን ፡ ከእነር
ሱው ፡ አቅዋም ፡ ጋር ፡ እያስተያየ ፡ በበለጠ ፡ መንገድ ፡
እንዲያሳያቸው ፡ በማለት ፡ ነው ።

ክርስቲያን ፡ ላልሆኑት ፡ በምንሰብክበት ፡ ጊዜ ፡
ቶሎ ፡ በሚያስተውሉት ፡ በቀላል ፡ ነገር ፡ መጀመር ፡ አለ
ብን ። ቀስ ፡ በቀስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ማለፍ ፡ ይገባናል ።

ሃይማኖቶች ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ደኅንነት ፡ እን
ደሚሰጡ ፡ ይናገራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አነጋገሩ ፡ ያው ፡ ሆኖ ፡
ስጦታው ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነው ። ለማመዛዘን ፡
ያህል ፡ የባዕድ ፡ ሃይማኖቶችን ፡ ትምህርት ፡ ትንሽ ፡ ብንመ
ለከት ፡ አይከፋም ፤ «ኒርቫና ፡» የተባለውን ፡ የጋውታማ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ቡድሃ ፡ እምነት ፡ ውስጣዊን ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉ ፡ በመግደል ፡
አእምሮን ፡ ከመሰወር ፡ በማይለይ ፡ በስቃይ ፡ ኑሮ ፡ የመ
ኖር ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። ሰውነት ፡ ይሰወራል ፤ ከቀድሞውም ፡
አንድነት ፡ እንዳለው ፡ አይታወቅም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚ
ያም ፡ ከዚያም ፡ የተሰበሰበ ፡ ሆኖ ፡ በሞት ፡ ጊዜ ፡ ሁ
ሉም ፡ በየመንገዱ ፡ ለየብቻው ፡ ይለያያል ፡ ይላል ። ከዚ
ህም ፡ በተቀር ፡ ቡድሃውያን ፡ ወይም ፡ ቡዲስቶች ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ የነፍስን ፡ ደኅንነት ፡ ለማግኘት ፡
በሚያደርገው ፡ ድካም ፡ ተስፋ ፡ አያደርጉም ። ይህም ፡
በቡዲስቶች ፡ የቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ የሚታየው ፡
ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ሐዘን ፡ ቀቢጸ ፡ ተስፋነቱን ፡ ይገልጻል ።
እስልምናና ፡ ህንዲም ፡ ከመሞት ፡ በፊት ፡ ስላለው ፡ የነ
ፍስ ፡ ደኅንነት ፡ አንዳችም ፡ አያውቁም ።

እንደዚሁም ፡ ከክርስትና ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ በስ
ሩት ፡ የሚገኙት ፡ ሃይማኖቶች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ይስማማሉ ፤
ማለት ፡ የነፍስ ፡ ደኅንነት ፡ በሥራ ፡ ድካም ፡ ይገባል ፡
ወይም ፡ ዋጋው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
የጋው ፡ ታማ ፡ ቡድሃ ፡ የመጨረሻ ፡ ንግግር ፡ «በሥራህ ፡
የነፍስህን ፡ ደኅንነት ፡ ማግኘት ፡ አለብህ ፡ »ወይም ፡ «የነ
ፍስህን ፡ ደኅንነት ፡ ለማግኘት ፡ መሥራት ፡ አለብህ ፡» ይ
ላል ። ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ቃላት ፡ በክርስቲያን ፡ መጽሐፍ ፡
ቅዱስ ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆኑ ፤ ነገር፡ ግን ፡ ከክርስትና ፡ ውጭ፡
የሆኑ ፡ ሃይማኖቶች ፡ አንዳችም ፡ ከዚህ ፡ የሚቀጥለውን ፡
የመሰለ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ሊወዳደረው ፡ የሚችል ፡
ታላቅ ፡ መግለጫ ፡ የያዘ ፡ በጭራሽ ፡ አይገኝባቸውም ፡



ስለ ፡ በጎ ፡ ፈቃዱ ፡ መፈለግንም ፡ ማድረግንም ፡ በእናንተ
የሚሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ። (ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።)

ከክርስትና ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ሁሉ
የግብረ ፡ ገብነትን ፡ (ሞራል ፡) ግዴታ ፡ በልዩ ፡ ልዩ
ደረጃ ፡ ያውቃሉ ። ሁሉም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆኑ
አንዳንድ ፡ የግብረ ፡ ገብነት ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ
አላቸው ። የሚጐድልባቸው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እ
ሱም ፡ የግብረ ፡ ገብነት ፡ ዲናሞ ፡ (ኃይል ፡) ነው ። እምነታ
ቸው ፡ «ራስህን ፡ አድን ፡» በሚል ፡ ነው ፡ ተመስርቶ ፡ የ
ወሰነው ። ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በፍጹም ፡ የማይቻል
መሆኑን ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቃል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አይሁ
ዳዊና ፡ አረማዊ ፡ በየራሳቸው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ለመዳን
ሲሞክሩ ፡ አየ ፤ ግን ፡ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ከንቱ ፡ ድካም
ሆኖ ፡ አገኘው ። የክርስቲያን ፡ ወንጌል ፡ ብቻውን ፡ ብቻ
የነፍስ ፡ ደኅንነት ፡ በተሰቀለውና ፡ሙቶ፡ በተነሣው ፡ መድ
ኀን ፡ አማካይነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በከንቱ ፡ ያለ
ዋጋና ፡ ድካም ፡ የተሰጠ ፡ ስጦታ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ።

ቀጥሎም ፡ የሰው ፡ ሞራል ፡ ሁኔታን ፡ በእውነቱ ፡
መርምሮ ፡ ሕመሙን ፡ ያገኘው ፡ ክርስትና ፡ ብቻ ፡ ነው ።
መሐመድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ ወይም ፡ ለዓለማዊ
ነት ፡ መንገድ ፡ ከመክፈቱም ፡ በላይ ፡ በገነት ፡ ደግሞ ፡
ሃይማኖተኞች፡ የሆኑት ፡ ሲገቡበት ፡ በፍትወት ፡ እንደሚደ
ስቱ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶአቸዋል ። ሒንዱ ፡ (ሒንዱዊዝም ፡)
ደግሞ ፡ የግብረ ፡ ገብነት ፡ ትልቅ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆኑ ፡ አንዳ
ንድ ፡ ስሕተቶችን ፡ ያደፋፍራል ። የቡድሃ ፡ ሃይማኖት ፡ (ቡ
ዲዊዝም ፡) በከፍተኛው ፡ አስተያየትዋ ፡ የነፍስን ፡ ደኅን



www.ethiopianorthodox.org

ነት ፡ ከሥቃይ ፡ (ሥጋን ፡ ከማሰቃየት ፡) ታስገኘዋለች ፡ «ሥ
ቃይ ፡» ትላለች ፡ «ከፍላጎት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ የነ
ፍስ ፡ ደኅንነት ፡ እንዲገኝ ፡ ከተፈለገ ፡ የሥጋ ፡ ፍላጎት ፡
ሁሉ ፡ እራሱ ፡ ከሰው ፡ ተፈጥሮ ፡ ጨርሶ ፡ ሊነቀል ፡ ይገ
ባል ።» የክርስትና ፡ መግለጫ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የሰው ፡
ልጆች ፡ ትልቁና ፡ ክፉው ፡ ጠላት ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። የነ
ፍስም ፡ ደኅንነት ፡ የሚገኘው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ታሪክ ፡ ው
ስጥ ፡ እራሱን ፡ በመሰዋት ፡ ለብቻው ፡ ኃጢአትን ፡ ድል ፡ ባ
ደረገው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ መግ
ለጫው ፡ ሲቀጥል ፥ ሰው ፡ አዲስ ፡ ልብ ፥ እውነተኛ ፡ ልብ ፡
ያስፈልገዋል ፥ ይህን ፡ ሲል ፡ ፍላጎቱ ፡ ሁሉ ፡ ከውስጡ ፡
ተነቅሎ ፡ እንዲጠፋ ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ። ይህስ ፡ ከሆነ ፥
ሰው ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ፥ መላ ፡ ሰውነቱን ፡ ጨርሶ ፡ ከማ
ጥፋትና ፡ ከማውደምም ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡
ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ክርስትና ፡ የሚለው ፡ ፍላጎት ፡ ከፍተ
ኛና ፡ ንጹሕ ፡ እንዲሆንና ፡ ክርስቶስን ፡ እንዲመስል ፡ ይኸ
ውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲመስል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ከክርስትና ፡
ውጭ ፡ በሆኑ ፡ ሃይማኖቶችና ፡ በክርስትና ፡ መካከል ፡ ያለ
ውን ፡ ዓይነተኛ ፡ ልዩነት ፡ ለማስተያየት ፡ ለመጽሔትነት ፡
ያህል ፡ በአጭሩ ፡ ተመልክቶአል ። የቀረው ፡ ዝርዝር ፡ ስለ ፡
«ስብከት ፡» በተጻፈው ፡ በዚህ ፡ በአነስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡
ውስጥ ፡ የሚጨመር ፡ አይደለም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፥ ወንጌልን ፡
ለመስበክ ፡ ለሚነሳው ፡ ለክርስቲያን ፡ ሰባኪ ፡ መልካም ፡
ፈቃዱን ፡ ለመርዳት ፡ ለሥራው ፡ የሚያስፈልገውን ፡
ያህል ፡ ማበርከታችን ፡ የአድማጮቹን ፡ ሃይማኖት ፡ በተ



ቻለ ፡ መጠን ፡ ማወቅና ፡ ልዩነታቸውም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡
ለመረዳት ፡ የሚያበቃውን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ጠቀስንለት ፡
እናምናለን ። ይህ ፡ ተግባር ፡ ከመጻሕፍትም ፡ ከሕዝብም ፡
እንደበት ፡ ለማጥናት ፡ ይቻላል ። ጕዳዩ ፡ በጣም ፡ አስፈ
ላጊ ፡ መሆኑን ፡ የሚረዱ ፡ ሰባኪዎች ፡ ብዙ ፡ ችግርም ፡
ቢገጥማቸው ፡ ስንኳ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለው ፡ ጊዜ ፡ ሊያ
ገኙለት ፡ በደስታ ፡ እንደሚጥሩ ፡ እናምናለን ።

ቅዱስ ፡ ሥራ ፡ በሆነው ፡ ዓለምን ፡ በክርስቶስ ፡ ወን
ጌል ፡ ለማልበስ ፡ በሚደረገው ፡ «የእግዚአብሔር ፡ የሥራ ፡
ጓደኛ ፡» መሆን ፡ ትልቅ ፡ ዕድል ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ራሱ ፡
አንድ ፡ ሌላ ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ መሆኑን ፡ ክርስቲያን ፡ ሊረ
ዳው ፡ ይገባዋል ። ስለዚህም ፡ ሐዋርያው ፡ ያዘዘውን ፡ ልብ
ን ፡ የሚወጋውን ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፡ ኃይላችን ፡ እንታዘዝ ፤
የእውነትን ፡ ቃል ፡ በቅንነት ፡ የሚናገር ፡ የማያሳፍርም ፡
ሠራተኛ ፡ ሆነህ ፡ የተፈተነውን ፡ ራስህን ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ልታቀርብ ፡ ትጋ ። (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፥ ፲፭ ።)

---



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ አሥራ ፡ አንድ ።

# ሰባኪው ፡ እንደ ፡ ጸሎት ፡ ሰው ።

በዚህ ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ የሚደረገውን ፡ ጸሎት ፡ አስቀድመው ፡ ሳይዘጋጁበት ፡ በድንገት ፡ የመጀመር ፡ ልማድ ፡ ላላቸውና ፡ እንዲሁም ፡ የወንጌል ፡ ሰባኪዎች ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ የሚያገድ ፡ «የግል ፡ ጸሎት ፡» የተባለውን ፡ ተግባር ፡ በዝርዝር ፡ ለማሳሰብ ፡ እንፈቅዳለን ።

በሕዝብ ፡ ፊት ፡ የሚደረግ ፡ ጸሎት ፡ በጣም ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአብዛኞቹ ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኞች ፡ ዘንድ ፡ ተገቢው ፡ ጥንቃቄ ፡ ሳይደረግለት ፡ ይኖራል ። አንድ ፡ ሰው ፡ የብዙዎችን ፡ ሰዎች ፡ ምስጋናና ፡ ልመና ፡ የሚያቀርብ ፡ ሲሆን ፣ የነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረቶች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምስጋናና ፡ የሚፈልጉትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ሁኔታቸውንና ፡ ስሜታቸውን ፡ በመገመት ፡ አስቀድሞ ፡ በጽሞና ፡ ተጠንቅቆ ፡ በማሰብ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለበት ። አንድ ፡ ብርቱ ፡ ሰባኪ ፡ ስለዚህ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ሲያስረዳ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ የሚደረገውን ፡ እያንዳንዱን ፡ ጸሎት ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በጽሑፍ ፡ እያዘጋጀ ፡ በመቅረብ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ መሥራቱን ፡ ገለጸላቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ስለሚደረገው ፡ የጸሎት ፡ ዝግጅት፡
«የጽሞና ፡ ጸሎት ፡» ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡
ሊቁ ፡ በመጽሐፉ ፡ ሲያስተምር ፡ «ከአድማጮቹ ፡ ዘንድ ፡
የወንጌል ፡ ልኡካችን ፡ ስብከት ፡ ከጸሎቱ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡
ይበልጣል ፡» የሚለው ፡ ግምትና ፡ ድምፅ ፡ ሲወድቅ ፡
በጣም ፡ ያሳዝናል ። ይህ ፡ ጌታችን ፡ የሰጠውን ፡ የምሳሌ ፡
መልክ ፡ አልተከተለም ፡ ማለት ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ሌላ ፡
ሰው ፡ ተናግሮት ፡ በማያውቅ ፡ አመላለስ ፡ ተናግሯል ፤ ስለ ፡
ጸሎቱም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እጅግ ፡ ተደንቀው ፤ ጌታ ፡
ሆይ ፡ መጸለይ ፡ አስተምረን ፡ እስቲሉት ፡ ድረስ ፡ በዚህም ፡
የአድናቆት ፡ ጥያቄ ፡ የተነሣ ፡ «የጌታችን ፡ ጸሎት ፡ »በአ
ጭርና ፡ ይህ ፡ ይጐድለዋል ፡ በማይባል ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ በ
ተሟላ ፡ ሳለፈው ፡ ምስጋናን ፡ ለአሁኑም ፡ የፍላጎት ፡ ልመ
ናን ፡ የያዘ ፡ የማይሰለች ፡ ቀልጣፋ ፡ ጸሎት ፡ ሊሰማበትና ፡
ሊመሠረትበት ፡ ተቻለ ። የጌታችን ፡ ጸሎት ፡ የዕለት ፡ ጸ
ሎት ፡ ወይም ፡ የምስጋናና ፡ የልመና ፡ መደምደሚያ ፡ ሆኖ ፡
ቀርቶአል ። እውነተኛ ፡ ጸሎት ፡ ኃይሏ ፡ ከሌላ ፡ ዓለማ
ዊና ፡ የሳይንስ ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ የበለጠ ፡ ነው ።
የቁመት ፡ አጭር ፡ የወርድ ፡ ጠባብ ፡ ጸሎትን ፡ መሣሪያው ፡
ካደረገ ፡ ቁመተ ፡ ረዥምን ፡ ወርደ ፡ ሰፊውን ፡ በቅጽበት ፡
ድል ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ዳዊትንና ፡ ጐልያ
ድን ፡ ስንመለከት ፡ እምነት ፡ በተባለው ፡ መሣሪያ ፡ ብቻ ፡
ዳዊት ፡ ድልን ፡ እንደ ፡ ተጐናጸፈ ፡ እናያለን ፤ በዳዊት ፡
እጅም ፡ ሰይፍ ፡ አልነበረም ። (፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፶ ፡) ጸሎት ፡
የአምልኮትን ፡ መሠረት ፡ የያዘ ፡ ታላቅ ፡ መታመኛ ፡ ነው ።
ለማናቸውም ፡ አምልኮት ፡ ሁሉ ፡ ጸሎት ፡ ተቀዳሚ ፡ መ
ሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። ጸሎት ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብ



ሔር ፡ ጋር ፡ የሚገናኝበትና ፡ የሚነጋገርበት ፡ የነፋስ ፡ ስ
ልክ ፡ ማለት ፡ ነው ። «ለምኑ ፡ ታገኛላችሁ ፡ »ሲሆን ፡ ተ
ቃራኒው ፡ «ያልለመነ ፡ ምንም ፡ አያገኝም ፡ በሥጋዊ ፡ ም
በመንፈሳዊውም ፡ ኑሮው ፡ ምስኪን ፡ ድሀ ፡ ሆኖ ፡ ይቀ
ራል ፤ ከሚያስበው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ አይከና
ወንለትም ፡» ማለት ፡ ነው ። ጸሎት ፡ የሥጋን ፡ ፍላጎት ፡ የ
ነፍስን ፡ ደኅንነት ፡ የሚያስገኝ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ለሰ
ው ፡ ልጆች ፡ የተሰጠ ፡ ታላቅ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሲሆ
ን ፡ በጥንቃቄ ፡ የምናቀርበው ፡ ጸሎት ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡
አምላካዊ ፡ መልስ ፡ እንደሚያገኝ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

ርኵስ ፡ መንፈስን ፡ የሚያባርር ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡
ቅዱስ ፡ መንፈስን ፡ በባዶነታችን ፡ የሚተካ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡
በደንበኛም ፡ ስብሰባ ፡ ቢሆን ፡ በአደባባይ ፡ ስብከት ፡ አድ
ማጮችንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያቀራርብ ፡ የመጀመሪያ ፡
እርምጃ ፡ የተሟላ ፡ ጸሎት ፡ ነው ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ ጸሎት ፡
አድራጊው ፡ ወይም ፡ ሰባኪው ፡ የጸሎትን ፡ ተግባር ፡ በያ
ዘበት ፡ ጊዜ ፡ አድማጮቹን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ የሚ
ያገናኝ ፡ የስልክ ፡ ሽቦ ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰባ
ኪው ፡ እንደ ፡ ጸሎት ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
የሚያቀርብ ፡ የአደማጮቹ ፡ እንደራሴ ፡ ማለት ፡ ስለሆነ ፡
በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛውን ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ መዘ
ንጋት ፡ የለበትም ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለማለት ፡ ያሰኘን ፡
ቀደም ፡ ብሎ ፡ ጸሎቱን ፡ ማዘጋጀት ፡ ቀዳሚ ፡ ተግባሩ ፡
መሆኑን ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ ነው ። ከሰባኪው ፡ የሚሰማውን ፡
ጸሎት ፡ በማድመጥ ፡ ሕዝቡ ፡ አዲስ ፡ ሕይወትና ፡ አዲስ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ንን ፡ በማሳነስ ፡ ወይም ፡ በመቆጠብ ፡ ብናደርግ ፡ ግን ፡ ም ንም ፡ ያህል ፡ የተከናወነ ፡ አገልግሎት ፡ ለማድረግ ፡ ከቶ ፡ አንችልም ።

አንድ ፡ ትልቅ ፡ የወንጌል ፡ አርበኛ ፡ በተጋድሎቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ በቀን ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ለጸሎትና ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ለማንበብ፡ ያውል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከደንበኛው ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ እንደሚሆንበት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ከንጋቱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ይነሣና ፡ ለዚሁ ፡ ለጸሎቱና ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሱን ፡ ለማንበብ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያጠፋ ፡ ነበር ። «ይህን ፡ ባላደ ርግ ፡ ግን ፡» ይል ፡ ነበር ፡ የወንጌል ፡ አርበኛው ፡ «የዕለቱ ፡ ሥራዬም ፡ በፍጹም ፡ አይከናወንልኝም ።»

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙር ቱን ፡ ከአብ ፡ የሚላክላቸውን ፡ ተስፋ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ያሳ ስባቸው ፡ ነበር ። (የሐዋ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡) ይህንንም ፡ ማ ለቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚላክላቸውን ፡ የመንፈስ ፡ ቅ ዱስ ፡ ኃይል ፡ እስኪቀበሉ ፡ ድረስ ፡ በጸሎትና ፡ በትዕግ ሥት ፡ እንዲጠብቁ ፡ ማለቱ ፡ ነው ። መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ የ ሚል ፡ የለም ።

የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ የሚሰብክ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ኑሮው ፡ ሁሉ ፡ የጸሎት ፡ ኑሮ ፡ እንዲሆን ፡ ይገባል ። በእውነቱ ፡ ጸሎተኞች ፡ ብንሆን ፡ ቃላችንና ፡ ነገራችን ፡ ሁሉ ፡ የታመነና ፡ ፍሬያማ ፡ ይሆናል ። ይህንን ፡ ስናደርግ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የእውነትን ፡ ቃል ፡ በቅንነት ፡ የሚናገር ፡



የማያሳፍርም ፡ ሠራተኛ ፡ ሆነን ፡ የምንገኘው ። (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ፡) ቀጥሎም ፡ ለአሕዛብ ፡ በተላከው ፡ በትልቁ ፡ ሐዋ ርያ ፡ የተነገረውን ፡ ወንጌልን ፡ ባልሰብክ ፡ ወዮልኝ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፮ ፡)

ተ ፈ ጸ መ ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111271609
D.N Solomon Yohannes



www.ethiopianorthodox.org